# በኢትዮጵያ የአራት ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት የሕዝብ መዝሙሮች ይዘት ትንተና

መስፍን መሰለ

## አኅጽሮተ ጽሑፍ

“የኢትዮጵያን ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመሠረቱት” ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት በየሕገ መንግሥታቸው የየራሳቸው የሕዝብ መዝሙር እንደሚኖራቸውና በሕዝብ መዝሙሮቻቸው ሊንፀባረቁ የሚገባቸውን ይዘቶች ደንግገዋል፡፡ ድንጋጌያቸውን ተግባራዊ በማድረግ የራሳቸው ክልል ሕዝብ መዝሙር ያላቸው የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ የዐማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትና የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ብቻ ናቸው፡፡ የዚኽ ጥናት ትኩረትም በተጠቀሱት ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት የሕዝብ መዝሙሮች ላይ ነው፡፡ ይኽን ጥናት ማካኼድ ያስፈለገበት ምክንያት፣ በብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት የሕዝብ መዝሙሮች ላይ የተደረገ ጥናት አለመኖርና ክፍተቱን ለመሙላት ምርምር ማድረግ አስፈላጊ በመኾኑ ነው፡፡ የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ የአራት ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት የሕዝብ መዝሙሮች የሀገራችንን ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ኹኔታዎች ምን ያኽል እንዳንጸባረቁና በኅብረተ ሰቡ ውስጥ ለማስረጽ የተደረገውን ጥረት መመርመርና ይዘቶቹን መተንተን ነው፡፡ ከዚኽ ዐቢይ ዓላማ የሚመነጩ ዝርዝር ዓላማዎችም፣ ብሔራውያን ክልላውያን መዝሙራቱን ለመድረስ ያነሣሡ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶችን መመርመር፣ ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት በየሕገ መንግሥታቸው ስለብሔራዊ ክልላቸው የሕዝብ መዝሙር የደነገጓቸው ይዘቶች ምን ያኽል በየመዝሙሮቹ እንደተንጸባረቁ መመርመር፣ መተንተን፣ የሕዝብ መዝሙሮቹ ብሔራዊ ማንነትን ለመገንባት (ለማጠናከር) (national identity building and strengthening) እንዲሁም ሀገራዊ አንድነትን ለማጎልበልበት ያላቸውን ጠቀሜታ፣ ብሔራውያን ክልላውያን የሕዝብ መዝሙራቱ ከፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር ጋር እንዴት ተጣጥመው አገልግሎት እንደሚሰጡ መፈተሸና የሕዝብ መዝሙሮቹ የሚገልጹዋቸውን ርዕዮተ ዓለሞች መመርመር የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚኽን ዓላማዎች ለማሳካት ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፡- ብሔራውያን ክልላውያን መዝሙሮቹን ለመድረስ ያነሣሡ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው? ብሔራዊ ክልላዊ መዝሙሮቹ የተደረሱበትን ፖለቲካዊ፣ ታሪካዊና ማኅበራዊ እውነታ ምን ያኽል አንጸባርቀዋል? በብሔራውያን ክልላውያን ሕገ መንግሥታት ስለሕዝብ መዝሙሮች የተደነገጉት ይዘቶች በሕዝብ መዝሙሮቻቸው እንዴት ተንጸባረቁ? በብሔራውያን ክልላውያን የሕዝብ መዝሙሮች አማካይነት በወጣቶች አዕምሮ እንዲሰርፁ የተደረጉትን ርዕዮተ ዓለሞች ብሔራዊና ሀገራዊ ጠቀሜታ ምን ያኽል ነው? የሚሉት ናቸው፡፡ ጥናቱ፣ በተጠቀሱት ብሔራውያን ክልላውያን የሕዝብ መዝሙሮች ላይ ማተኰሩ የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ የብሔራውያን ክልላውያን መዝሙራቱ ታሪክ ምን እንደሚመስል ለመገንዘብ፣ የብሔራውያን ክልላውያን መዝሙራቱን ተግባርና አገልግሎት ለመረዳት በተለይም የብሔራዊ ማንነትን ለመገንባት (national identity building and strengthening) ያላቸውን ሚና፣ (በብሔራውያን ክልላውያን የሕዝብ መዝሙሮች አማካይነት በወጣቶች አዕምሮ እንዲሰርፁ የተደረጉትን ርዕዮተ ዓለሞች ለመረዳት ያስችላል፡፡) ሀገራዊ አንድነትን ለማጠናከርና ለማጎልበት ያላቸውን ጠቀሜታ፣ እንዲሁም ብሔራዊ ክልላዊ መዝሙራቱ ከፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር ጋር እንዴት ተጣጥመው አገልግሎት እንደሚሰጡና በየሕገ መንግሥታቸው የሕዝብ መዝሙሮቻቸው እንዲንጸባረቁ የተደነገጉት ይዘቶች እንዴት እንደተንጸባረቁ ለመረዳት ያስችላል፡፡ እንዲሁም፣ ወደ ፊት ለሚደረጉ ተመሳሳይ ጥናቶች መነሻነት ያገለግል፡፡ የዚኽ ጥናት የመረጃ ምንጮች ጥናቱ ትኩረት ያደረገባቸው ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ሕገ መንንግሥቶች፣ የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የሕዝብ መዝሙሮች፣ ዐዋጆች፣ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱን የሚመሩት የፖለቲካ

ድርጅቶች የፖለቲካ ፕሮግራሞችና በራሪ ጽሑፎች፣ የታሪክ ሰነዶች፣ መጽሔቶችና ጋዜጦች ናቸው፡፡ የትግራይ፣ የሶማሌና የኦሮሚያ ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት የሕዝብ መዝሙሮችን በመረጃነት ለመጠቀም የተቻለው ቋንቋዎቹን በሚችሉ ሰዎች ወደ ዐማርኛ በማስተርጐም ነው፡፡ በትርጉም ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን ክፍተት በማሰብ በሌሎች የየቋንቋዎቹ ተናጋሪዎች ትርጉማቸው እንዲመረመር ተደርጓል፡፡ በመገኛ ቋንቋዎቹ የተገለጸውን ይዘት ለመረዳት የሚችሉትን አንባቢዎች በማሰብና የመረጃዎቹን ትክክለኛነት ለመግለጽ በመገኛ ቋንቋዎቹ የተጻፉትን በማስቀደምና ትርጉማቸውን ከጎን በማስቀመጥ ተተንትነዋል፡፡ ትንተናው በአብዛኛው ትርጉምን መሠረት በማድረጉ ቅርጻቸውን መመርመር አልተቻለም፡፡ በመዝሙሮቹ የተንጸባረቁት ይዘቶች የተተነተኑት የሕዝብ መዝሙሮቹን ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ዐውዶች መሠረት በማድረግ ነው፡፡

<u>ቁልፍ ቃላት</u>፡- የብሔራዊ ክልላዊ ሕገ መንግሥት ዓላማዎች፣ መዝሙር፣ ባህል፣ ጀግንነት፣ ታሪክ፣ ብሩኅ ተስፋ፣ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ የመኖር እምነት፡፡

## ፩. መግቢያ

በ1983 ዓ. ም. የመንግሥት ሥልጣን ለውጥ ከተካኼደ በኋላ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስተዳደር በአብዛኛው ቋንቋን መሠረት በማድረግ ተዋቀሩ፡፡[1] ከለውጥ በፊት የነበሩት ክፍላተ ሀገሮችና ራስ ገዝ አስተዳደሮች በዐዲሱ አከፋፈል ተተኩ፡፡ መንግሥት ይገለገልባቸው የነበሩ መዋቅሮችና መንግሥታዊ ተቋሞች በሌላ ተተኩ፡፡ ቀደም ሲል የነበረው ከተለወጡት መካከልም የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር አንዱ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙርም ከሕገ መንግሥቱ ቀድሞ በ1984 ዓ. ም. እንዲወጣ ተደረገ፡፡ ቀድሞ የመውጣቱ ምክንያትም በ1992 (እ.ኤ.አ) በባርሴሎና በሚዘጋጀው የኦሎምፒክ ውድርድር ኢትዮጵያን ወክሎ የሚሳተፈው የስፖርት ቡድን የኢትዮጵያን ብሔራዊ መዝሙር ይዞ መቅረብ ስለ ነበረበት ነው፡፡ የኦሎፒክ ቡድኑ እንዲገለገልበት የተዘጋጀው ዐዲሱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉሞ በሕዝብ መገናኛዎች እንዲተላለፍ የኢትዮጵያ የሽሽግግር መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤት ወስኖ ይኽንን እንዲያስፈጽም የማስታወቂያ ሚኒስቴር ቢታዘዝም፣ ለመፈጸም እንደሚያስቸግረው ለኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ተወካዮች ምክር ቤት ገለጸ፡፡ በጊዜው ብሔራዊ መዝሙሩ ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች የመተርጎም ሥራ ሳይተገበረ ቀረ፡፡

በሽግግሩ መንግሥት የወጣው ብሔራዊ መዝሙርም የሕግ ማዕቀፍ ሳይኖረው ለ19 ዓመታት አገልግሎት ሰጠ፡፡ ይሁን እንጂ፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፬ ላይ "የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር የሕገ መንግሥቱን ዓላማዎችና የኢትዮጵያ ሕዝቦች በዲሞክራሲያዊ ስርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን እምነት፣ እንዲሁም የወደፊት የጋራ ዕድላቸውን የሚያንጸባርቅ ሆኖ በሕግ ይወሰናል" በማለት ተደነገገ፡፡ በዚኹ መሠረትም የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር በአዋጅ ቁጥር <u>፯፻፸፫</u>/<u>፪ሺ፪</u> የሕግ ማዕቀፍ ተሰጠው፡፡

[1] የትግራይ፣ የአፋር፣ የአማራ፣ የኦሮሞና የሶማሊያ ብሔራውያ ክልላውያን መንግሥታት አንድን ዋና ቋንቋ መሠረት በማድረግ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ የጋምቤላና የቤንሻንጉል-ጉሙዝ ብሔራዉያን ክልላውያን መንግሥታት መልክዓ ምድራዊ ቅርርብነትንና ለአስተዳደር ያላቸውን አመችነት መሠረት በማድረግ የተመሠረቱ ሲኾኑ የሐረሪ ሕዝብ ከኦሮሚያ ሁንደኔ ወረዳ ጋር በመጣመር አንድ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት እንዲኾን ተደርጓል፡፡ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮች ተጠሪነታቸው ለሚኒስትሩ ኾኖ በፌዴሬሽን ምክርቤት ውክልና የላቸውም፡፡ የብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታቱም የከተሞች አስተዳደሮቹም አወቃቀር የተለያዩ ቅሬታዎች ይቀርብባቸዋል፡፡

ብሔራዊ መዝሙሩም በአንቀጽ ፫፡- ፩) የሕገ መንግሥት የበላይነትን፤ ፪) የኢትዮጵያ ሕዝቦች ረጅም የታሪክ ባለቤትነትን፤ ፫) የኢትዮጵያ ሕዝቦች በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን ፅኑ እምነት፤ ፬) የኢትዮጵያ ሕዝቦች የወደፊት የጋራ እድላቸው ብሩህ መሆኑን፤ የሚገልጽ ምልክት መሆኑ ተደነገገ።

በብሔራዊ መዝሙሩ ዐዋጅ (አዋጅ ቁጥር ፮፻፸፫/፪ሺ፪) አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተደነገገው መሠረት ማንኛውም ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ብሔራዊ መዝሙሩ እንዲዘመር ያደርጋል። በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፪ እንደ ተደነገገው፣ "በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ክልሎች በህግ በወሰኑት የሥራ ቋንቋ የብሔራዊ መዝሙሩ የግጥም ይዘትና ዜማ እንደተጠበቀ ሆኖ ብሔራዊ መዝሙሩን ዜማና ግጥም በባለሙያ በማስተርጎም መጠቀም ይችላሉ፤ ይህም በሥራ ላይ የሚውለው በየምክር ቤቶቻቸው በሚያፀድቁት የብሔራዊ መዝሙሩ የተረጋገጠ ትርጉም ይሆናል።" በአንቀጽ ፯ በተደነገገው መሠረት "በሕግ በሚወሰነው መሠረት ብሔራዊ መዝሙሩ በብሔራዊ በዓላት ሥነ- ሥርዓት ላይ ይዘመራል።" እንደዚሁም፣ በአንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ ፩ "በሰንደቅ ዓላማ አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፬/፪ሺ፩ አንቀጽ ፲፭/፪/ መሠረት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ በትምህርት ቤቶች የሚሰቀለው ብሔራዊ መዝሙርን በመዘመር ይሆናል።" በአንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ ፩ እንደ ተደነገገው "...ማንኛውም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ብሔራዊ መዝሙሩ እንዳይዘመር ያደረገ እንደሆነ፣ እንደአግባብነቱ የትምህርት ቤቱ የበላይ ሀላፊ ወይም ትምህርት ቤቱ በቀላል እስራት ወይም እስከ ፭ሺ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

ይኸ የብሔራዊ መዝሙር ዐዋጅ ከመውጣቱ በፊት፣ "ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያን የመሠረቱት" ዘጠኙ ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት በየሕገ መንግሥታቸው የየራሳቸው የሕዝብ መዝሙር[2] እንደሚኖራቸውና በሕዝብ መዝሙሩ የሚያንጸባረቀውን ይዘት በየሕገ መንግሥታቸው ደንግገዋል፤ ዝርዝሩ በሕግ እንደሚወሰን ጭምር። በየብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታቱ ሕግጋተ መንግሥታት በሕዝብ መዝሙሮቻቸው እንዲያንጸባርቁ የተደነገጉት ይዘቶች ተመሳሳይነትምና ልዩነትም አላቸው። ምንም እንኳ ዘጠኙም ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት የሕዝብ መዝሙር እንደሚኖራቸው በየሕገ መንግሥታቸው ቢደነግጉም ዐምሥቱ (የአፋር፣ የሐረሪ ሕዝብ፣ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ የጋምቤላ ሕዝቦችና የቤንሳንጉል-ጉሙዝ) ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት የሕዝብ መዝሙር የላቸውም። አራቱ (የትግራይ፣ የዐማራ፣ የኦሮሞና የሶማሌ) ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት ግን የሕዝብ መዝሙሮቻቸውን አወጥተዋል። ኾኖ የሕዝብ መዝሙሮቻቸውን በዐዋጅ የደነገጉት የሶማሌና የኦሮሚያ ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት ብቻ ናቸው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙርና የብሔራውያን ክልላውያን

---

[2] ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታቱ መዝሙሮቻቸውን በተለያዩ ስሞች እንደጠሩ ከየሕገ መንግሥታቸውና ከሌሎችም ሰነዶች (የሕዝብ መዝሙር ዐዋጅና ውሳኔ) መረዳት ይቻላል። ስሞቹም "የትግራይ ብሄራዊ ክልል መዝሙር" (ትግራይ)፣ "የብሔራዊ ክልሉ መዝሙር" (የዐማራ)፣ "የክልሉ ሕዝብ መዝሙር/ብሔራዊ መዝሙር" (የቤኒሻንጉል-ጉሙዝ)፣ "የክልሉ ብሔራዊ መዝሙር" (የጋምቤላ ሕዝቦች)፣ "የክልሉ መዝሙር" (የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች)፣ "የብሔራዊ ክልሉ መዝሙር" (የአፋር)፣ "የክልሉ መዝሙር" (የሐረሪ ሕዝብ)፣ "የክልሉ መዝሙር" (የሶማሌ) የሚሉት ናቸው። በዚኽ ጥናት በየብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት ወይም ሌላ ሰነድ የተጠሩበትን መጠሪያ ተጠቅሜአለሁ።

መዝሙሮች በአንድ አጋጣሚ ላይ፣ ለምሳሌ በትምህርት ቤቶች በሚዘመሩበት ጊዜ ማንኛው እንደሚቀድም በሕግ ባለመደንገጉ ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት የፈለጉትን በማስቀደም ይዘምራል፡፡ በአንዳንድ ክልሎች ትምህርት ቤቶች በመጀመሪያ የኢትዮጵያን ብሔራዊ መዝሙርን ቀጥሎም ብሔራዊ ክልላቸውን የሕዝብ መዝሙር ሲያዘምሩ፣ ሌሎቹ ደግሞ ከዚኽ በተቃራኒው ያዘምራሉ፡፡

ጥናቱን ማካኼድ ያስፈለገበት ምክንያት፣ በብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት (የትግራይ፣ የኦሮሞ፣ የአማራና የሶማሌ) የሕዝብ መዝሙሮች ላይ የተደረገ ጥናት አለመኖርና ክፍተቱን ለመሙላት ምርምር ማድረግ አስፈላጊ በመኾኑ ነው፡፡ ይኽን ጥናት ማካኼድ ያስፈለገበት ምክንያት፣ በብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት የሕዝብ መዝሙሮች ላይ የተደረገ ጥናት አለመኖርና ክፍተቱን ለመሙላት ምርምር ማድረግ አስፈላጊ በመኾኑ ነው፡፡

የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ የአራት ብሔራውያንዊ ክልላውያን መንግሥታት የሕዝብ መዝሙሮች የሀገራችንን ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ኹኔታዎች ምን ያኽል እንዳንጸባረቁና በኅብረተ ሰቡ ውስጥ ለማስረጽ የተደረገውን ጥረት መመርመር ነው፡፡ ከዚኽ ዐቢይ ዓላማ የሚመነጩ ዝርዝር ዓላማዎችም፣ ብሔራውያን ክልላውያን መዝሙራቱን ለመድረስ ያነሣሡ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶችን መመርመር፣ ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት በየሕገ መንግሥታቸው ስለብሔራዊ ክልላቸው የሕዝብ መዝሙር የደነገጓቸው ይዘቶች ምን ያኽል በየመዝሙሮቹ እንደተንጸባረቁ መመርመር፣ መተንተን፣ የሕዝብ መዝሙሮቹ ብሔራዊ ማንነትን ለመገንባት (ለማጠናከር) (national identity building and strengthening) እንዲሁም ሀገራዊ አንድነትን ለማጎልበልበት ያላቸውን ጠቀሜታ፣ ብሔራውያን ክልላውያን የሕዝብ መዝሙራቱ ከፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር ጋር እንዴት ተጣጥመው አገልግሎት እንደሚሰጡ መፈተሽና የሕዝብ መዝሙሮቹ የሚገልጹዋቸውን ርዕዮተ ዓለሞች መመርመር የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚኽን ዓላማዎች ለማሳካት ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፡- ብሔራውያን ክልላውያን መዝሙሮቹን ለመድረስ ያነሣሡ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው? ብሔራዊ ክልላዊ መዝሙሮቹ የተደረሱበትን ፖለቲካዊ፣ ታሪካዊና ማኅበራዊ እውነታ ምን ያኽል አንጸባርቀዋል? በብሔራውያን ክልላውያን ሕገ መንግሥታት ስለሕዝብ መዝሙሮች የተደነገጉት ይዘቶች በሕዝብ መዝሙሮቻቸው እንዴት ተንጸባረቁ? በብሔራውያን ክልላውያን የሕዝብ መዝሙሮች አማካይነት በወጣቶች አዕምሮ እንዲሰርፁ የተደረጉትን ርዕዮተ ዓለሞች ብሔራዊና ሀገራዊ ጠቀሜታ ምን ያኽል ነው? የሚሉት ናቸው፡፡

ጥናቱ፣ በተጠቀሱት ብሔራውያን ክልላውያን የሕዝብ መዝሙሮች ላይ ማተኰሩ የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ የብሔራውያን ክልላውያን መዝሙራቱ ታሪክ ምን እንደሚመስል ለመገንዘብ፣ የብሔራውያን ክልላውያን መዝሙራቱን ተግባርና አገልግሎት ለመረዳት በተለይም የብሔራዊ ማንነትን ለመገንባት (national identity building and strengthening) ያላቸውን ሚና፣ (በብሔራውያን ክልላውያን የሕዝብ መዝሙሮች አማካይነት በወጣቶች አዕምሮ እንዲሰርፁ የተደረጉትን ርዕዮተ ዓለሞች ለመረዳት ያስችላል፡፡) ሀገራዊ አንድነትን ለማጠናከርና ለማጎልበት ያላቸውን ጠቀሜታ፣ እንዲሁም ብሔራዊ ክልላዊ መዝሙራቱ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ብሔራዊ መዝሙር ጋር እንዴት ተጣጥመው አገልግሎት እንደሚሰጡና በየሕገ መንግሥታቸው የሕዝብ መዝሙሮቻቸው እንዲንጸባረቁ የተደነገጉት ይዘቶች እንዴት

እንደተንጸባረቁ ለመረዳት ያስችላል፡፡ እንዲሁም፣ ወደ ፊት ለሚደረጉ ተመሳሳይ ጥናቶች መነሻነት ያገለግል፡፡

የዚኽ ጥናት የመረጃ ምንጮች ጥናቱ ትኩረት ያደረገባቸው ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ሕገ መንንግሥቶች፣ የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የሕዝብ መዝሙሮች፣ ዐዋጆች፣ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱን የሚመሩት የፖለቲካ ድርጅቶች የፖለቲካ ፕሮግራሞችና በራሪ ጽሑፎች፣ የታሪክ ሰነዶች፣ መጽሔቶችና ጋዜጦች ናቸው፡፡

የትግራይ፣ የሶማሌና የኦሮሚያ ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት የሕዝብ መዝሙሮችን በመረጃነት ለመጠቀም የተቻለው ቋንቋዎቹን በሚችሉ ሰዎች ወደ ዐማርኛ በማስተርጐም ነው፡፡ በትርጉም ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን ክፍተት በማሰብ በሌሎች የየቋንቋዎቹ ተናጋሪዎች ትርጉማቸው እንዲመረመር ተደርጓል፡፡ በመገኛ ቋንቋዎቹ የተገለጸውን ይዘት ለመረዳት የሚችሉትን አንባቢዎች በማሰብና የመረጃዎቹን ትክክለኛነት ለመግለጽ በመገኛ ቋንቋዎቹ የተጻፉትን በማስቀደምና ትርጉማቸውን ከጎን በማስቀመጥ ተተንትነዋል፡፡ ትንተናው በአብዛኛው ትርጉምን መሠረት በማድረጉ ቅርጻቸውን መመርመር አልተቻለም፡፡ በመዝሙሮቹ የተንጸባረቁት ይዘቶች የተተነተኑት የሕዝብ መዝሙሮቹን ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ዐውዶች መሠረት በማድረግ ነው፡፡

ይኽ ጥናት በአራት ንዑሳን ርእሶች የተከፋፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል መግቢያ ሲኾን በዚኽም የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ ዓላማ፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎችና የጥናቱ ጠቀሜታ ተገልጿል፡፡ በኹለተኛው ንዑስ ርዕስ ብሔራዊ ክልላዊ መዝሙር በማውጣት የማይገለገሉ ዐምሥት ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት በየሕገ መንግሥታቸው ስለ ብሔራዊ መዝሙር የደነገጉትን ለመመርመር ጥረት ተደርጓል፡፡ በሦስተኛው ንዑስ ርዕስ፣ ብሔራዊ ክልላዊ መዝሙር በማውጣት የሚገለገሉ አራት ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት በየሕገ መንግሥታቸው ስለ ብሔራዊ መዝሙር የደነገጓቸውንና በየብሔራዊ ክልላዊ መዝሙሮቻቸው ያንፀባረቋቸውን ይዘቶች ለማነጻጸር ተመርምረዋል፤ ተተንትነዋል፡፡ በአራተኛው ንዑስ ርዕስ የጥናቱ ማጠቃለያ ቀርቧል፡፡

## ፪) ብሔራዊ ክልላዊ መዝሙሮቻቸውን በዐዋጅ ያልደነገጉ ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ሕገ መንግሥት ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት የየራሳቸውን የክልል መዝሙር የማውጣት ሥልጣን እንዳላቸው በግልጽ አልተደነገገም፡፡ ኾኖም፣ የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ ፶፪ ንዑስ አንቀጽ ፩ "በሕገ መንግሥቱ ለፌዴራሉ መንግሥት በተለይ ወይም ለፌዴራሉ መንግሥትና ለክልሎች በጋራ በግልጽ ያልተሰጠ ሥልጣን የክልል ሥልጣን ይሆናል፡፡" በማለት ይደነግጋል፡፡ ይኽንን ሕገ መንግሥታዊ መብት ተጠቅመው፣ ዘጠኙም ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት በየሕገ መንግሥታቸው የየራሳቸው ብሔራዊ ክልላዊ መዝሙር እንደሚኖራቸውና በመዝሙሮቻቸው የሚያንጸባርቋቸውን ይዘቶች ደንግገዋል፡፡

ከዘጠኙ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ዐምሥቱ (አፋር፣ የሐረሪ ሕዝብ፣ ደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ የጋምቤላ ሕዝቦችና የቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት) የብሔራዊ ክልላዊ መዝሙር እንደሚኖራቸውና በይዘታቸውም የሚያንፀባርቋቸውን ደንግገዋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከላይ የተጠቀሱት ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት መዝሙሮቻቸውን በማውጣት አይገለጉሉም፡፡ በዚኽ ንዑስ ርእስ የምንመለከተውም በብሔራዊ ክልላዊ መዝሙሮቻቸው እንዲያንፀባረቁ የደነገጉትን ብቻ ነው፡፡ ይኽን መመርመር ያስፈለገበት ምክንያት፣ የተጠቀሱት ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት በየብሔራዊ ክልላዊ መዝሙሮቻቸው ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ ለመኖር ያላቸውን እምነት፣ "የክልሉ መሥራች አይደሉም" ስለሚባሉ ሕዝቦች ፖለቲካዊና ኢኰኖሚያዊ ተሳትፎ፣ ቋንቋቸውንና ባህላቸውን ስለማሳደግ እንዲሁም በታሪካቸው ስለመኲራትና ስለመንከባከብ የደነገጉትን ለመገንዘብ ስለሚያስችል ነው፡፡

ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታቱ በየሕገ መንግሥታቸው የየራሳቸው መዝሙር እንደሚኖራቸውና በየመዝሙሮቻቸውም እንዲያንጸባርቁ የደነገጉዋቸው ይዘቶች ተመሳሳይነትምና ልዩነትም አላቸው፡፡ ይኽንንም፣ እያንዳንዳቸው በየሕገ መንግሥታቸው የደነገጉትን በመጥቀስ እንመለከታለን፡፡ በቅድሚያ በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት የተደነገገውን እንመልከት፡፡

የተሻሻለውን የቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት ለማጽደቅ በወጣው ዐዋጅ ቁጥር 31/1995 አንቀጽ 5 "የክልሉ ሕዝብ መዝሙር" በሚል ንዑስ ርእስ ተደንግጓል፡፡ ድንጋጌውም፣ "የቤኒሻንጉል- ጉሙዝ ክልል የራሱ የሆነ ብሔራዊ መዝሙር[3] ይኖረዋል፡፡ የክልሉ መዝሙር የሕገ መንግሥቱን ዓላማዎችና የክልሉን ሕዝቦች በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ አብሮ ለመኖር ያላቸውን እምነትና የወደፊት የጋራ እድላቸውን የሚያንፀባርቅ ሆኖ በህግ ይወሰናል፡፡" የሚል ነው (አጽንኦት የተጨመረ)፡፡ በድንጋጌው መሠረት እንደሚቻለው "የክልሉ ሕዝብ መዝሙር"/"የክልሉ ብሔራዊ መዝሙር" የክልሉን ሕገ መንግሥት ዓላማዎች ማንፀባረቅ ዋናውና የመጀመሪያው ነው፡፡ እንደ ተገለጸው የቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት ዓላማዎች፣ በክልላዊ መንግሥቱ የሕግ የበላይነትን ማስፈን፣ ኢኰኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገትን ማፋጠን፣ ክልላዊ መንግሥቱን ያቋቋሙትን ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን ቋንቋና ባህል በማሳደግ ማንነታቸውን ማስከበር፣ ታግለውና መስዋዕትነት ከፍለው ያገኟቸውን ዲሞክራሲና ሰላም በዘላቂነት ማረጋገጥ የሚሉት መኾናቸው በብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ ተገልጿል፡፡

በብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ እንደተገለጸው የየራሳቸው መልክዓ ምድራዊ አሠፋፈር ያላቸው የክልሉ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ለረጅም ዘመን በተለያዩ መልኰችና ደረጃዎች ተሳስረው በመቆየታቸው በጋራ ባፈሯቸው እሴቶች ላይ በመመሥረትና

---

[3] መጀመሪያ የክልሉ ሕዝብ መዝሙር ቀጥሎ ደግሞ ብሔራዊ መዝሙር በማለት መጥራት ወጥ የቋንቋ አጠቃቀም ወይም አጠራር አይደለም፡፡ ከዚኽም በላይ የክልሉን መሥራቾችና ባለቤቶች "ብሔረሰቦችና ሕዝቦች" ሌላ ጊዜ ደግሞ "ሕዝቦች" "ብሔረሰቦች" በማለት ይጠራል፡፡ ለምሳሌ በክልላዊ መንግሥቱ ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ "እኛ የቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልል ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በጋራ በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ ተመሥርተን በአቋቋምነው ክልላችን.... እኛ የበርታ፣ የጉሙዝ፣ የሽናሻ፣ የማኦና የኮሞ ብሔረሰቦች..." በማለት ይጠራል (አጽንኦት የተጨመረ)፡፡

እሴቶቹን በማጎልበት ወደ ተሻለ የዕድገት ጎዳና እንደሚያመሩ ፅኑ እምነት አላቸው፡፡ “የክልሉ ሕዝብ መዝሙር” ይዘትም ይኸንን ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱን የመሠረቱት ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን እምነት ማንፀባረቅ መኾን እንደሚገባው ተደንግጓል፡፡ አብሮ የመኖር እምነቱ ትኩረት፣ በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት መሥራችና ባለቤት ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መካከል ነው፡፡ ይኸንንም “የቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፪ “በክልሉ ውስጥ የሚኖሩ ሕዝቦች የሚታወቁ ቢሆንም የክልሉ ባለቤት ብሔር፣ ብሔረሰቦች በርታ፣ ጉሙዝ፣ ሽናሻ፣ ማኦና ኰሞ ናቸው” በማለት የተደነገገው ያስረዳል፡፡ ይኸ ድንጋጌ በክልላዊ መንግሥቱ ውስጥ ለሚኖሩ ከሌላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መጡ ለሚባሉት በሕገ መንግሥታቸው አንቀጽ 2 “በክልሉ ውስጥ የሚኖሩ ሌሎች ሕዝቦች የሚታወቁ ቢሆንም” በማለት ዕውቅና ይሰጣል፡፡ ዕውቅና የተሰጣቸው “ሕዝቦች” በስም ካለመገለጻቸውም በላይ የክልሉ ባለቤቶች እንደኾኑ አይደነግግም፡፡ በዚኹ አንቀጽም “የክልሉ ባለቤት ብሔር፣ ብሔረሰቦች በርታ፣ ጉሙዝ፣ ሽናሻ፣ ማኦና ኮሞ” መኾናቸው በግልጽ መደንገጉ ለሌሎች በክልሉ ለሚኖሩት ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ዕውቅና አለመስጠቱን ያስረዳል፡፡

በቤኒሻጉል-ጉመዝ ክልላዊ መንግሥት ከሚኖሩትና በስም ካልተጠሩት ሕዝቦች መካከል የዐማራና የኦሮሞ ብሔሮች አባላት ከበርታና ከጉሙዝ ብሔረ ሰቦች ቀጥለው ከፍተኛ ቁጥር አላቸው (Central Statistical Agency, 2007)፡፡ በቁጥር የሚያንሱትን የሺናሻ፣ የማኦና የኰሞ ብሔር-ብሔረሰቦችን በስም በመጥራት የክልሉ ባለቤቶች እንደኾኑ ሲደነግግ የዐማራ፣ የኦሮሞና ሌሎችም በክልሉ የሚኖሩ “ሕዝቦች” በክልሉ ውስጥ ሰለ መኖራቸው ብቻ ዕውቅና ይሰጣል፡፡ የሕዝብ መዝሙሩ “የክልሉ ሕዝቦች በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ ለመኖር ያላቸውን እምነት የሚያንጸባርቅ እንዲኾን” የሚለው ድንጋጌ ትኩረት የክልሉ ባለቤት በኾኑት ብሔር-ብሔረሰቦች ነው፡፡ የቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልል ብሔር-ብሔረሰቦች በክልሉ ውስጥ ከሚኖሩ ሌሎች “ሕዝቦች” (ዐማራ፣ ኦሮሞ መዘተ.) የተለየ መብት እንዳላቸው በአንቀጽ ፴፱ ከንዑስ አንቀጽ ፩ እስከ ፯ ተደንግጓል፡፡

የቤንሻንጉል-ጉሙዝ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራሳቸውን ብሔራዊ ማንነት የመጠበቅና የማስከበር፣ ቅርሳቸውንና ታሪካቸውን የመንከባከብና የማበልፀግ፣ በቋንቋቸው የመጠቀም፣ ቋንቋቸውን የማሳደግ፣ ባህላቸውን የመግለጽ፣ የማዳበርና የማስፋት መብት አላቸው በማለት በአንቀጽ ፴፱(፩) ተደንግጓል፡፡ በራሳቸው መልክዓ ምድራዊ ክልል ውስጥ የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው የመጨረስ፣ ራስን በራስ የማስተዳደር እንዲሁም በፌደራሉ መንግሥት በነፃነት፣ አድሎ በሌለበት ተገቢና ፍትሐዊ ውክልና የማግኘትና የመሳተፍ መብት አላቸው (አንቀጽ ፴፱ (፪))፡፡ በአንቀጽ (፴፱) (፫) አንደተደነገገው ራስን በራስ የማስተዳደር መብት፣ ሕዝቡ በሰፈረበት መልክዓ ምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋም በፌዴራላዊ መንግሥቱ አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት አላቸው፡፡ ሕገ መንግሥቱ ለክልሉ ባለቤት ብሔር- ብሔረሰቦች በማንኛውም ጊዜ የራሳቸውን ክልል የማቋቋም መብት ይሰጣል (አንቀጽ ፴፱ (፯))፡፡ እነዚኽ የተጠቀሱት መብቶች በክልሉ ለመኖራቸው ዕውቅና ለተሰጣቸው “ሕዝቦች“ አልተሰጡም፡፡ ሕገ መንግሥቱ በክልሉ ለመኖራቸው ዕውቅና የሰጣቸውን “ሕዝቦች” የክልሉ ባለቤት ከኾኑት ያገላል (discriminate ያደርጋል)፡፡ ይኸም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ

ዲሞክራሲዊ ረፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፴፫ ንዑስ አንቀጽ ፪ ላይ "ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የኢትዮጵያ ዜግነት በሕግ የሚያስገኘውን መብት፣ ጥበቃና ጥቅም የማግኘት መብት አለው፡፡" በማለት የተደነገገውን ይቃረናል፡፡ የዜግነት መብትን መገደብም የኢትዮጵያን ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የበላይነት ይቃረናል፤ አብሮ በመኖርና በመሥራት አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረ ሰብ ለመገንባትም አያስችልም፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፳፭ ላይ የተደነገገውን የእኩልነት መብት ይጻረራል፡፡

የክልሉ ሕዝብ/ብሔራዊ መዝሙር የክልሉን ብሔረሰቦች የወደፊት የጋራ እድላቸውን የሚያንፀባርቅ እንዲኾን ተደንግጓል፡፡ ይኸም የሕግ የበላይነትን በማስፈን፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገትን በማፋጠን፣ ቋንቋን በማሳደግ፣ ባህልን በመንከባከብ፣ ማንነትን በማስከበር፣ ዲሞክራሲን በማስፈንና ሰላምን በማረጋገጥ ወደፊት የጋራ እድላቸው ብሩህ መኾኑን ማንፀባረቅ ማለት ነው፡፡

ይሁን እንጂ፣ "የክልሉ ሕዝብ/ብሔራዊ መዝሙር" የክልሉ ሕዝቦች በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን እምነት እንዲያንጸባርቅ የተደበገገው ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ረፐብሊክ መሥራች ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ጋር ማለትን አይገልጽም፡፡ የክልሉ "የሕዝብ/ብሔራዊ መዝሙር" በወጣቶች አእምሮ የሚያሰርፀው ስለ ክልሉ መሥራችና ባለቤት ብሔረሰቦች ይኾናል፡፡ ይኸም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኖሩትን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች አቅርበው እንዳይመለከቱ የጋራ ማንነት በአጠቃላይ ኢትዮጵያዊነትን እንዲገነዘቡ አያደርግም፡፡

የተሻሻለውን የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት ለማጽደቅ የወጣው ዐዋጅ ቁጥር ፳፯/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፣ "የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል የራሱ የሆነ ብሔራዊ መዝሙር ይኖረዋል፡፡ የክልሉ መዝሙር የሕገ-መንግስቱ(ን?) ዓላማዎችና የክልሉ[ን] ሕዝቦች [በ]ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ ለመኖር ያላቸውን እምነት እንዲሁም የወደፊት የጋራ ዕድላቸውን የሚያንፀባርቅ ሆኖ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡" በማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ከደነገገው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ በጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት የክልሉ ሕዝቦች በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ ለመኖር ያላቸውን እምነት በማለት የገለጸው ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱን የመሠረቱትን ዐምሥት ብሔረሰቦችን ነው፡፡ ይኸውም፣ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፵፮ ንዑስ አንቀጽ ፩ እንደ ተደነገገው የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መሥራች አባላት፣ ፩) የአኙዋ ብሔረሰብ፣ ፪) የኑዌር ብሔረሰብ፣ ፫) የመዠንግር ብሔረሰብ፣ ፬) የኦፖ ብሔረሰብና ፭) የኮሞ ብሔረሰብ ናቸው፡፡ እነዚኽ የክልሉ መሥራች አባላት እኩል መብትና ሥልጣን እንዳላቸው በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፪ ተደንጓል፡፡ እንዲሁም በአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ ፫ "በእያንዳንዱ የብሔረሰብ ዞን በራሱ አስተዳደር ውስጥ የሚገኙ ሌሎች አናሳ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የየራሳቸውን ቀበሌዎች በራስ የማስተዳደር መብት ይጠብቃል፤ በክልልና በዞን በቀጥታ የመወከል መብትም ይጨምራል፡፡" በማለት ብሔራዊ ክልሉን ላልመሠረቱት ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደርና በክልሉና በዞን የመወከል መብት ይፈቅዳል ሕገ መንግሥታዊ መብት ይሰጣል፡፡ ይኽ መብት በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ሕዝቦች ሕገ መንግሥት የክልሉ ባለቤቶች አይደሉም ለተባሉ "ሕዝቦች" አልተሰጠም፡፡

ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ሕገ መንግሥት ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያን ከመሠረቱት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ ለመኖር ያለውን እምነት እንዳልደነገገ ኹሉ የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ ሕገ መንግሥት አልደነገገም፡፡ የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሚኖሩ ወጣቶች በየትምህርት ቤቶቹ እየዘመሩ የሚያድጉት በክልላቸው ስለ ሚኖሩት ብሔረሰቦች ብቻ ነው፡፡ ይኸም የአንድነት ግንዛቤአቸው ዝቅተኛ እንዲኾን ያደርገዋል፡፡ ይኽ መኾኑም የአንድነት ሥነ ልቡና ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ የሕዝብ መዝሙሩ በዘማሪዎቹ አእምሮ አንድነትንና ብሔራዊ ስሜትን አያሰርጽም፡፡

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት በተሻሻለው ሕገ-መንግሥት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 46/1997 አንቀጽ 4 ስለ ክልሉ መዝሙር ይደነግጋል፡፡ ድንጋጌውም፣ "የሐረሪ ክልል ህዝብ የረጅም ዘመን የጀግንነትና የፍትህ ታሪክ እንዲሁም የተገኘውን ድል የሚያሳይና ለተሻለ ኑሮ ያለውን ምኞት የሚያንፀባርቅ የራሱ መዝሙር ይኖረዋል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡" የሚል ነው፡፡

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊመንግሥት ሕገ መንግሥት የሕዝብ መዝሙሩ፣ ለክልሉ ሕዝብ ረጅም የጀግንነት ታሪክ እንዲያንፀባርቅ መደንገጉ ትክክልና ተገቢ ነው፡፡ ይኸም የክልሉ ወጣቶች ለታሪካቸው ትኩረት እንዲሰጡና የራሳቸውን ታሪካዊ ኃላፊነት ለመወጣት እንዲያስቡና እንዲተጉ ያደርጋል፡፡ ነገር ግን፣ በክልሉ መዝሙር እንዲንፀባረቅ የተባለው ታሪክ እውነታው ላይ ካልተመሠረተ በትውልዱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር በሚኖረው ግንኙነትም አሉታዊ ውጤት ያመጣል፡፡ በሐረሪ ሕዝብ ክልል ሕገ መንግሥት የተገለጸው በተማሪዎች የታሪክ መማሪያ መጻሕፍት ተካትቶ እንዲማሩበት ከቀረበ ትክክለኛውን የታሪክ እውነታ አያሳውቅም፡፡ በክልሉ ሕገ መንግሥት መግቢያ ስለ ታሪክ የተገለጸው የሚከተለው ነው፡፡

የሐረሪ ሕዝብ የረጅም ዘመን የጀግንነት ታሪክ ትኩረት ያደረገው ከ፲፰፻፹፯ ዓ. ም. "የነፍጠኛው ሥርዓት" ባደረገበት ወረራ ላይ ነው፡፡ "የሐረሪ ሕዝብ ምንም እንኳ በምዕተ ዓመታት ለሚቆጠር ዘመን ራሱን በራሱ ያስተዳድር፣ በራሱ ታሪክ፣ ወግና ባህል ይኰራ የነበረ ቢኾንም በ፲፰፻፹፯ ዓ. ም. [በሐረሪ ሕዝብ] ላይ በተደረገበት ወረራ በነፍጠኛው ሥርዓት ሥር ከመውደቁም በላይ ይኽንን ሥርዓት ለማስወገድ በተለያዩ ጊዜያት ባደረገው ንቅናቄና ትግል ምክንያት ለግርፋት፣ ለእሥራትና ብሎም ለስደት..." ተዳርጓል (የሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት፣ አዋጅ ቁጥር ፵፮/፲፱፻፺፯ መግቢያ፣ ገጽ ፬)፡፡ ከተጠቀሰው ዓመተ ምሕረት በፊት የሐረሪ ሕዝብ ለምዕተ ዓመታት ራሱን በራሱ ያስተዳድር እንደ ነበር ተገልጿል፡፡ ይኽንን በሕገ መንግሥቱ የተገለጸውን ታሪክ ብንቀበል እንኳ ራሱን በራሱ ሲያስተዳድር ከቅርብ ወይም ከሩቅ የመጣ ጠላት አላጋጠመውም ማለት አይቻልም፡፡ ሐረር "እ.ኤ.አ. በ1875 ዓ. ም. በከዲቭ እስማኤል ገዥነት በረዑፍ ፓሻ አዝማችነት በግብጾች ቁጥጥር ሥር ውላ ነበር፡፡" ከተማዋ ከግብጾች አገዛዝ ነጻ የወጣችው ከዐሥር ዓመታት በኋላ እ.ኤ.አ. በ1885 ነው (ይድነቃቸው ከበደና ኢሳያስ አየለ፣ 2007፤ 122- 123)፡፡ "ሐረር በልዩ ልዩ ምክንያቶች እና በተለያዩ ወቅቶች በጊዜው ከነበሩ

የኢትዮጵያ ነገሥታት ጋር የተለያዩ ጦርነቶችን አድርጋለች፡፡"4 (ይድነቃቸው ከበደና ኢሳያስ አየለ፣ 2007፤ 123) የሐረር ሕዝብ በቅርቡ ይኖሩ ከነበሩ ኦሮሞዎችና ሶማሌዎች ጋር ያሳለፈው ታሪክ የሰላም ብቻ ነበር ማለትም አይቻልም፡፡ በ16ኛው ክፍለ ዘመን ብዙ ዓመታት በፈጀ የግንባታ ክንውን የሐረርን ከተማ ዙሪያ በግንብ ማጠር ያስፈለገበት ምክንያት "ነፍጠኛውን ሥርዓት" ለመከላከል ወይም የሐረርን ከተማ ለማሳመር አልነበረም፡፡ የጀጎልን ግንብ መገንባት ያስፈለገበት ምክንያት በሐረር ከተማ ይኖር የነበረውን የሐረሪ ሕዝብ ከጥቃት ለመታደግ ነበር፡፡ በዘመኑ በነበሩት የጦር መሣሪያዎች ግንቡን ጥሶ ከተማዋን ለማጥቃት የሚያስችሉ አልነበሩም፡፡ በግንቡ ዙርያ በመስፈር ጠላትን በንቃት የመከታተል እና የመመከት ኃላፊነት የነበረው ልዩ ጦር እንዲሁም በዐምሥቱ በር እና በግንቡ ዙሪያ የተሠሩት 12 ማማዎች ለከተማዋ ደህንነት እና ፀጥታ ወሳኝ ሚና ነበራቸው፡፡" (ይድነቃቸው ከበደና ኢሳያስ አየለ፣ 2007፤ 124)፡፡ በምሥራቅና በሰሜን ኢትዮዮጵያ የውጭ ኀይሎች በሰነዘሩት ጥቃት የሐረሪ ሕዝብ የደረሰበት ችግርና የጣሊያን ቅኝ ገዢዎችና የግብፅ ተስፋፊዎች በጀጎል ነዋሪዎች ላይ ያደረሱትን ጥቃት ይኸንንም ለመከላከል የተደረገውን የጀግንነት ተግባር የዘነጋ ነው፡፡ በሐረሪ ሕዝብ ክልል መንግሥት ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ የተገለጸው ታሪክ ዓላማ "የነፍጠኛውን ሥርዓት" ማውገዝና ማጥላላት በመኾኑ የክልሉ ሕዝብ ያለፈበትን ትክክለኛ የታሪክ ገጽታ አይገልጽም፡፡ ለፖለቲካ ግብ ማሳኪያ ታስቦ የተጻፈ ታሪክ በመኾኑ ከወቅታዊ ስሜት መግለጫነት ያለፈ ተግባር የለውም፡፡ ትክክለኛ ያልኾነውን የሕዝቡን ታሪክ ጽፎ ትውልዱ እንዲያውቀው ማድረግና በክልሉ መዝሙር እንዲንፀባረቅ ለማድረግ መደንገግ ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ ለመኖር የሚኖረውን እምነት ይጎዳል፡፡ አብሮ የመኖር እምነት ፍላጎት በሚያሳየው ሕዝብ ብቻ ግብ አይመታም፡፡ በፍላጎት ተቀባዩ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ሲኖረው ጭምር ነው ግብ የሚመታው፡፡

የሐረሪ ሕዝብ ክልል መዝሙር የክልሉን ሕዝብ የረጅም ዘመን የፍትሕ ታሪክም እንዲያንፀባርቅ ተደንግጓል፡፡ "የሐረሪ ሕዝብ ራሱን በራሱ ያስተዳድር ነበር" በተባለበት ዘመን የፍትሕ ሥርዓቱ ምን ይመስል እንደ ነበር ማስረጃ ማግኘት ባይቻልም፣ ሕዝቡ ችግሮቹን የሚፈታበት ባህላዊ የፍትሕ ተቋም እንደነበረው ይታመናል፡፡ ዛሬ አገልግሎት የሚሰጠው ባህላዊ የፍትሕ ተቋምም ከሕዝቡ ጋር ለረጅም ዘመን አብሮ የዘለቀ ነውና (ይድነቃቸው ከበደና ኢሳያስ አየለ፣ 2007)፡፡ በኅብረተ ሰቡ ተቀባይነት ያለውን ባህላዊ የፍትሕ ሥርዓት በክልሉ መዝሙር ትኩረት መስጠት በራስ ባህል ለመኩራት ያስችላል፡፡

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ ሕገ መንግሥት በክልሉ መዝሙር የሐረሪ ሕዝብ ያገኘውን ድል የሚያሳይ እንዲኾን ይደነግጋል፡፡ ድንጋጌው የሐረሪ ሕዝብ ያገኘው ድል ምንድን ነው? ያገኘውስ መቼ ነው? የሚሉት ጥያቄዎች እንዲነሡ ያደርጋል፡፡ በሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ እንደተገለጸው፣ የሐረሪ ሕዝብ ለምዕተ ዓመታት ራሱን በራሱ ያስዳድርና በራሱ ታሪክ፣ ወግና ባህልም ይኰራ የበረ ቢኾንም፣ ሐረሪ በ፲፰፻፹፯ ዓ. ም. በተደረገበት ወረራ

[4] ሐረሪ "ወደ አምስት ጦርነቶችን አስተናግዳለች፡፡ የመጀመሪያው ጦርነት በ14ኛው ክፍለ ዘመን በአፄ አምደጽዮንና ሳይቲን መካከል የተደረገ ነው፡፡ 2ኛው ደግሞ፣ በአፄ ያዕ[ቆ]ብና በአሚር ማህቱዝ መካከል የተደረገ ነው፡፡ 3ኛው በኢማም መሐመድ ወይም ግራኝ መሐመድ በመባል በሚታወቀውና በአፄ ልብነ ድንግል መካከል የተደረገው ጦርነት ነው፡፡ 4ኛው በአሚር ኑርና በአፄ ገላውዲዮስ መካከል የተደረገ ነበር፡፡ ከ320 ዓመታት በኋላ በ1887 ዓ. ም. በአሚር አብዱላሂና በአፄ ምኒልክ መካከል የተደረገው 5ኘው ጦርነት ነው፡፡" (ይድነቃቸው ከበደና ኢሳያስ አየለ፣ 2007፤ 123)

"በነፍጠኛው ሥርዓት ሥር ወደቀ፡፡" ይኸንን ለማስወገድም በተለያዩ ጊዜያት "ከሥርዓቱ ጋር ትንቅንቅና ትግል" ማድረጉ "ለግርፋት፣ ለእሥራትና ለስደት" ዳረገው፡፡ የሐረሪ ሕዝብ "ሲደርስበት የነበረውን ኢኰኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ጭቆና፣ ጫናና ተፅዕኖ ለማስወገድ በተለያየ ስልት፣ መልክና ቦታ ሲታገል ቆይቶ" በ1983 ዓ. ም. በማያዳግም ኹኔታ ሥርዓቱ ተለወጠ፡፡ ስለኾነም፣ የክልሉ መዝሙር እንዲያሳይ የተባለው ድል በ1983 ዓ. ም. በኢትዮጵያ የተደረገውን የሥልጣን ለውጥ ብቻ ነው፡፡ ይኸ ደግሞ የሐረሪንም ኾነ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትክክለኛ ታሪክ አይገልጽም፡፡ የመዝሙሩ ትኩረትም በወቅታዊ ፖለቲካ ላይ እንዲያተኩር የሚያደርግ ትክክለኛውን የሕዝቡን የጀግንነት ታሪክ የማይነግር ነው፡፡ በወጣቶች አእምሮ የሚያሰርጸው ታሪክ የተሟላ አይደርገውም፡፡ እንዲኸ ባለ ወቅታዊ (topical) ጉዳይ ላይ ማተኮሩም ፖለቲካው ሲለወጥ የክልሉ ሕዝብ መዝሙር የመለወጥ እድሉ ሰፊ ነው፡፡

የሐረሪ ሕዝብ ክልል ሕዝብ ለተሻለ ኑሮ ያለው ምኞት በክልሉ መዝሙር እንዲንጸባረቅ ተደንግጓል፡፡ የሐረሪ ሕዝብ ክልል ሕዝብ ለተሻለ ኑሮ እንዲበቃ በክልሉ ሕዝብ መዝሙር የተንፀባረቀው እውን የሚኾነው በሕገ መንግሥቱ መግቢያ ላይ እንደ ተገለጸው በክልሉ ውስጥ ዘላቂ ሰላምና ዋስትና ያለው ዲሞክራሲ ሲሰፍን፣ የግለሰብ፣ የብሔር፣ የብሔረሰብና የሕዝብ መሠረታዊ መብቶች ሲከበሩ፣ ከታሪክ የተወረሰውን የተዛባ አመለካከትና ግንኙነት "በማረምና በማስተካከል፣ መልካም አስተዳደርና የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ሥርዓት በመገንባት" ነው፡፡ ስለኾነም፣ የክልሉ መዝሙር ሕዝቡ ለተሻለ ኑሮ ያለውን ምኞት ማንፀባረቁ ለምኞቱ መሳካትና ለሕይወቱ ብሩኅ መኾን የሚያስችለውን እንዲያስብና ለስኬቱም እንዲተጋ ያደርጋል፡፡ በእርግጥ በሐረሪ ክልል ሕዝብ እንዲሳኩ የተባሉት ነገሮች በኢትዮጵያ ሕዝብ በጠቅላላ መተግበራቸው የግድ ነው፡፡ ይኹን እንጂ፣ የሐረሪ ክልል ከሐረሪ ሕዝብ ቁጥር በላይ የኾነውን አማራ ያገለለ ነው፡፡

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት በሕገ መንግሥቱ ስለ ክልሉ መዝሙር በደነገገበት አንቀጽ የክልሉን ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ ለመኖር ያለውን እምነት እንዲያንጸባርቅ አልደነገገም፡፡ የክልሉ መዝሙር ከኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ ስለ መኖር የማያንፀባርቅ ኾኖ ከተዘጋጀ የብሔራዊ ክልሉ ወጣቶች በየትምህርት ቤቶቹ እየዘመሩ የሚያድጉት በክልላቸው ከሚኖረው ሕዝብ "የኛ" ስለሚሉት ብቻ ይኾናል፡፡ ይኸም ስለ አንደነት የሚኖራቸውን ግንዛቤ ዝቅተኛ እንዲኾን ያደርገዋል፡፡ በአንድነት ሥነ ልቡናቸው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ የሕዝብ መዝሙሩም በዘማሪዎቹ አእምሮ አንድነትንና ብሔራዊ ስሜትን አያሰርጽም፡፡

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፬ "የአፋር ብሔራዊ ክልል መዝሙር የሕገ መንግሥቱን ዓላማዎች፣ የሕዝቡን ጀግንነት ታሪኩን የክልሉ ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን እምነት እንዲሁም የክልሉን ሕዝብ ባህል እድገትና ብሩኅ ተስፋ የሚያንፀባርቅ ሆኖ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡" በማለት ይደነግጋል፡፡ ይኸንን ድንጋጌ ለመረዳት በድንጋጌው ትኩረት የተደረገባቸውን ዋና ዋና ሐሳቦች ቀጥለን እንመረምራለን፡፡

በአንቀጽ ፬ እንደ ተደነገገው "የአፋር ብሔራዊ ክልል መዝሙር " እንዲያንፀባርቅ ከተደነገጉት መካከል የብሔራዊ ክልሉን ሕገ መንግሥት ዓላማዎች ማንጸባረቅ የሚለው ይጠቀሳል፡፡ የሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች በክልሉ ሕዝብ ዕድገት ላይ የደረሱትን አሉታዊ ተፅዕኖዎች ማስወገድ፣ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ማስከበር፣ በኢትዮጵያ የግለሰብና የቡድን (የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች) መብቶች እንዲከበሩ አስተዋጽኦ ማድረግ፣ የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል የተከበረባትና የሕግ የበላይነት የነገሠባት ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያን መገንባት፣ የጋራ ዕድገትን ማፋጠንና አንድ የጋራ ኢኮኖሚያዊ ማኅበረሰብ ማነፅ የሚሉት በሕገ መንግሥቱ መግቢያ ላይ ተገልጿል፡፡ እነዚኽና ሌሎች ዓላማዎች በሕገ መንግሥቱ ከአንጽ 99 እስከ አንቀጽ 104 ተደንግገዋል፡፡ ዓላማዎቹም፡- ፖለቲካ ነክ፣ ኢኮኖሚ ነክ፣ ማኅበራዊ፣ ባህል ነክና የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ ዓላማዎች ናቸው፡፡ በተጠቀሱት ዓላማዎች ምን ምን እንደሚካተት ተዘርዝሯል፡፡

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መዝሙር የሕዝቡን የጀግንነት ታሪክ ማንጸባረቅ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ እንደ ተገለጸው የሕዝቡ የጀግንነት ታሪክ "ያለፉትን የኢትዮጵያ ጨቋኝ ሥርዐቶች ለመደምሰስ ወደር የሌለው መስዋዕትነት" መክፈሉ ነው፡፡ መስዋዕትነት ከከፈለባቸው "ምክንያቶች አንዱና ዋናው ኹሉም ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸው የተከበሩ ሕዝቦች በሕገ መንግሥትና በሱ ብቻ የምትመራ ዲሞክራሲያዊት ሀገር እንድትሆን በማለት…ነው"፡፡ ጥቅስ መረዳት እንደሚቻለው የአፋር ሕዝብ የጀግንነት ታሪክ የተመሠረተው በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩት ጨቋኝ ሥርዐቶች ያደርሱት የነበረውን የአስተዳደር በደል ለማስወገድ በተደረገ ትግል የተፈጠረ ነው፡፡ የአፋር ሕዝብ የአስተዳደር በደል አልደረሰበትም፤ አልታገለም ማለት አይቻልም፡፡ ይሁን እንጂ፣ የጀግንነት ታሪኩ በዚኽ ላይ ብቻ የተመሠረተ ነው ማለት ስህተት ነው፡፡ ይኽ ግንዛቤ የአፋርን ሕዝብ የጀግንነት ታሪክ በትክክል አይገልጽም፡፡ ምክንያቱም፣ የውጪ ወራሪዎች በኢትዮጵያ ላይ የከፈቱትን ጥቃት ለመከላከል በተከፈለው መስዋዕትነትና በተገኘው ድል የአፋር ሕዝብ ድርሻ ከፍተኛ እንደ ነበረው አይገልጽም፡፡ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት ስለ ክልሉ ሕዝብ የጀግንነት ታሪክ የገለጸው ኢትዮጵያውያን የውጪ ወራሪን በመከልከል ኢትዮጵያ በባዕድ ሳትገዛ ነፃነቷ ተከብሮ እንድትኖር በከፈሉት መስዋዕት የአፋር ሕዝብ የነበረውን አስተዋጽኦ ግንዛቤ አላስገባም፡፡ የጀግንነት ታሪክ በተለያዩ ጊዜያት የውጪ ወራሪዎች ኢትዮጵያን ለማጥቃት የከፈቱዋቸውን ጥቃቶች ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በመኾን በተከፈለ መስዋዕትነት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ስለ ኾነም የአፋር ሕዝብ የጀግንነት ታሪክ "ብሔራዊ ጭቆናን" ለማስወገድ በተደረገ ትግል ብቻ ገድቦ በመዘመሩ ማካተት በተዛባ ታሪክ ላይ መመሥረትና ውጤቱን ማዛባት ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩ ጨቋኝ ሥርዐቶችን መታገል የጀመረው ከመቼ ጀምሮ እንደ ነበር አያስረዳም፡፡

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መዝሙር "የክልሉ ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ስርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን እምነት" እንዲያንፀባርቅ የመደንገጉ ምክንያት፣ "በአብዛኛው የሀገራችን ብሔረሰቦች[ና] ህዝቦች ላይ ይፈጸም የነበረው… አንገፍጋፊ ጭቆና በማያዳግም ሁኔታ መታረም እንዳለበት በማመን" ነው (የተሻሻለው የአፋር ብሔራዊ

ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት፣ 28/1994 መግቢያ)፡፡ ከዚኽም በላይ፣ በኢትዮጵያ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ይከበራሉ፤ የሕግ የበላይነት ይሰፍናል፣ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ተከብሯል፣ አንድ የኢኰኖሚ ማኅበረሰብ ለመፍጠር የሚያስችል ምቹ ኹኔታ ተፈጥሯል ተብሎ መታመኑን ከክልሉ ሕገ መንግሥት መግቢያ መረዳት ይቻላል፡፡ በክልሉ ብሔራዊ መዝሙር የክልሉ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አብሮ ለመኖር ያለውን እምነት ማንፀባረቁ ተገቢ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ በተዛባ ታሪክ ላይ መመሥረት የለበትም፡፡ በክልሉ ሕገ መንግሥት በአብዛኛዎቹ ብሔረሰብቦና ሕዝቦች ላይ ጭቆና ነበር የሚለው አገላለጽ አንድም፣ ሥርዓቱ ጭቆና የማይፈጽምባቸው ብሔሮች፣ ብሔረ ሰቦችና ሐዝቦች ነበሩ ማለት ነው፡፡ አንድም፣ ሌላውን የሚጨቁን/ኑ ብሔር/ሮች፣ ብሔረ ሰብ/ቦችና ሕዝብ/ቦች ነበር/ሩ ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ሌላውን የሚጨቁን ብሔር ወይም ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ አልነበረም፡፡ ይኽ ዓይንቱ የተሳሳተ ግንዛቤ በብሔራዊ ክልሉ መዝሙር እንዲንፀባረቅ መደንገጉ እውነታውን የማይገልጽ በመኾኑ ስህተት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብሮ ለመኖር የሚያስችል ሥርዓት ለመፍጠር በሚደረገው ጥረት ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ ያደርጋል፡፡

የክልሉ መዝሙር "የክልሉን ሕዝብ ባህል ዕድገት" እንዲያንፀባርቅ የሚለውን ድንጋጌ ለመረዳት አስቸጋሪ ነው፡፡ የባህል ዕድገት በክልሉ ብሔራዊ መዝሙር እንዴት ይንፀባረቃል? ለሚለው ጥያቄ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ የባህል ዕድገት የሚለው ያደገና ያላደገ ባህል የሚል እሳቤ/ግንዛቤ ስለሚፈጥር በክልሉ ብሔራዊ መዝሙሩ ዕድገቱ እንዲንፀባረቅ የሚለው ድንጋጌ ለመተግበር ያስቸግራል፡፡ ዕድገት ኺደትን ስለሚገልጽ ከየት ጀምሮ እስከ የት ያለው ዕድገት? የት ላይ የደረሰው? ዕድገቱን ወይም ለውጡ ተመዝግቦ ይገኛል ወይ? የሚሉት ጥያቄዎች መመለስ አስቸጋሪ ስለሚኾን በክልሉ መዝሙር እንዲንፀባረቅ ማድረግ አስቸጋሪ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ በአንቀጽ 36 (1) የአፋር ሕዝብ "የራሱን ብሔራዊ ማንነት የመጠበቅና የማስከበር፣ ቅርሱንና ታሪኩን የመንከባከብና የማበልፀግ የማሳደግ፣ ባህሉንና ቋንቋውን የመግለፅ የማዳበርና የማስፋፋት መብት አለው፡፡" በማለት የተደነገገውን መሠረት በማድረግ በክልሉ መዝሙር እንዲንፀባረቅ ማድረግ ተገቢነት አለው፡፡ በተጨማሪም በአንቀጽ 103 ባህል ነክ ዓላማዎች በሚለው ሥር የተደነገጉትን ንዑሳን ዓላማዎች በክልሉ ማንፀባረቅ ይቻላል፡፡ በክልሉ መዝሙር ሊንፀባረቁ የሚችሉት ባህል ነክ ዓላማዎች በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ድጋፍና ርዳታ የማድረግ ኃላፊነት የሚጠበቁና የሚኀለብቱ መኾናቸው በሕገ መንግሥቱ የሚከተሉት ንዑሳነ አንቀጾች ተደንግገዋል፡፡ በአንቀጽ 103 (1) የክልሉ መንግሥት መሠረታዊ መብቶችንና ሰብአዊ ክብርን፣ ዲሞክራሲንና ሕገ መንግሥቱን የማይቃረኑ ባህሎችና ልማዶች በእኩልነት እንዲኀለብቱና እንዲያድጉ የመርዳት ኃላፊነት አለበት፡፡ በአንቀጽ 102 (2) "በክልሉ የሚገኙትን የያንጉዲራሳና የአዋሽ ፓርኮችን የፌዴራሉ መንግሥት ከሚያደርገው ጥበቃ በተጨማሪ የክልሉ መንግሥትና ህዝብ የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው፡፡" በአንቀጽ 103 (3) ኪነጥበብን፣ ሳይንስንና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት፣ ወጣቱን ትውልድ የመንከባከብ፣ በተሟላ ሥነ ምግባር የማነፅ፣ ከሱስ ነፃ የሆነና በአካልም ሆነ በአእምሮ ጠንክሮ ኃላፊነቱን የሚሸከም አገሩን የሚወድ እና ለወገኑ የሚቆረቆር፣ በራሱ የሚተማመን ዜጋ ኾኖ እንዲያድግ ጥረት የማድረግ (አንቀጽ 103 (4))፣ የክልሉ የሥራ ቋንቋ ለኾነው የአፈርኛ ቋንቋ ዕድገት ልዩ ትኩረት የመስጠት (አንቀጽ 103 (5))፣

የክልሉን የአርኪኦሎጂ ግኝቶች የታሪክ ቅርሶችን የመጠበቅ ኃፊነት መንግሥት አለበት (አንቀጽ 103(6)) የሚሉት ባህል ነክ ዓላማዎች በክልሉ ብሔራዊ መዝሙር እንዲንጸባረቁ መደረጉ መደረጉ ተገቢ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ የተጠቀሱትን ኹሉንም ባህል ነክ ዓላማዎች በጥቂት ስንኞች ተመጥኖ በሚቀርብ የክልል መዝሙር ማቅረብ እንደማይቻል ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

የክልሉ ብሔራዊ መዝሙር የክልሉን ሕዝብ የወደፊት ዕድገትና ሕይወት በብሩህ ተስፋ ላይ የተመሠረተ መኾኑን እንዲያንጸባርቅ ይደነግጋል፡፡ ብሩኅ ተስፋ በአእምሮ ግልጽ ኾኖ የሚታይ፣ ይገኛል፣ ይፈጸማል፣ ይኾናል፣ ይደረጋል ተብሎ የሚጠበቅ ምኞት ነው፡፡ ይኸም መንግሥት የሕዝባቸው የወደፊት የጋራ ዕድል ብሩኅ መኾኑን ብሔራዊ ክልሉ በሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ ተገልጿል፡፡ የሕዝቡ የወደፊት ዕድገትና ብሩኅ ተስፋም "...ኢትዮጵያ ሀገራችን የግለሰብ መብቶችና ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል የተከበሩባት አጠቃላይ የሕግ የበላይነት የነገሠባት ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ረፑብሊክ መሆንዋ የጋራ ዕድገትን ለማፋጠንና አንድ የጋራ ኢኰኖሚያዊ ማኅበረ ሰብ ለማነፅ ያለውን ጠቀሜታ በመገንዘብ፤" ነው በማለት ተገልጿል፡፡ ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው የሕዝቡ ዕድገትና ብሩኅ ተስፋ የተመሠረተው በኢትዮጵያ ውስጥ "የሕግ የበላይነት ተረጋግጧል" ተብሎ በታመኑ ነው፡፡ የሕግ የበላይነት በመረጋገጡም የግለሰቦች መብት ተከብሯል፤ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን መብት ተረጋግጧል፤ ይኸ መብት "አልተከበረልንም" የሚሉ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ተገንጥለው የራሳቸውን መንግሥት የማቋቋም ሕገ መንግሥታዊ መብት እንደ አለው በክልሉ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 36 (4) ተደንግጓል፡፡ በኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት በመኖሩም ከሌሎች ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጋር አንድ የኢኰኖሚ ማኅበረ ሰብ መገንባት ጠቃሚ መኾኑ ታምኖበታል፡፡ የክልሉ ብሔራዊ መዝሙር የሕዝቡን የወደፊት ዕድገትና ብሩኅ ተስፋ እንዲያንፀባርቅ መደረጉ ትውልዱ ተስፋ እንዲኖረው ወደፊት የሚደርስበትን ዕድገት የሕግ የበላይነት እንደሚሰፍን በማመን ሀገሩን እንዲወድና ራሱም ለሥራ እንዲተጋ፣ ለሕግ እንዲገዛ ያደርጋል፡፡

"የተሻሻለው የ፲፱፻፺ ዓ. ም. የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሕገ መንግሥት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፲፱፻፺" አንቀጽ ፬ "የክልሉ መዝሙር የሕገ መንግሥቱን ዓላማዎች የክልሉ ሕዝቦች ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲ ሥርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን ዕምነት እንዲሁም የክልሉን ሕዝብ የወደፊት የጋራ ዕድል የሚያንፀባርቅ ሆኖ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡" በማለት ይደነግጋል፡፡

በሕገ መንግሥቱ መግቢያ ላይ እንደ ተገለጸው የክልሉ ሕገ መንግሥት ዓላማዎች በርካታ ናቸው፡፡ ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

እኛ የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፡-

> በጋራ በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ ተመስርተን ባቋቋምነው ክልላችን የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን፣ ኢኰኖሚና ማኅበራዊ እድገታችን እንዲፋጣን የራሳችንን ዕድል በራስ የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን፣ ቋንቋችንን ባህላችንና እንድነታችንን ይበልጥ ለማጠናከር፣ ማንነታችን ተከብሮ በትግላችንና በከፈልነው መስዋዕትነት የተገኘውን ዲሞክራሲና ሰላም ዘላቂነትን ለማረጋገጥ፤

በክልላችን ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የግለሰብ፣ የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና ሕዝቦች መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች መከበራቸውን፣ የጾታ እኩልነት መረጋገጡን፣ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶች ያለአንዳች ልዩነት በእኩልነት እንዲራመዱ ጽኑ እምነታችን በመሆን፤

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራሳችን የሆነ አኩሪ ባህልና፣ የራሳችን መልክዓ ምድራዊ አሰፋፈር ያለን፣ በተለያዩ መልኰችና ግንኙነት ደረጃዎች ተሳስረን አብረን የምንኖርባት ክልላችን በመሆኗ፤ ያፈራነው የጋራ ጥቅምና አመለካከት አለን ብለን ስለምናምን፤

ቀጣዩ የጋራ እድገታችን መመሥረት ያለበት ካለፈው ጨቋኝ ሥርዓት የወረስነውን የተዛባ ግንኙነት በማረምና የጋራ ጥቅማችንን በማሳደግ ላይ መሆን ስላለበት፤

ከዚኽ በላይ የተገለጹትን የክልሉ ሕገ መንግሥት ዓላማዎች ብዙ በመኾናቸው በክልሉ መዝሙር እንዲንጸባረቁ ለማድረግ አይቻልም፡፡ የክልሉ መዝሙር ባሕርይ አጭርና የተወሰኑ በመኾኑ ከብዙ ይዘቶች በጣም አስፈላጊ ናቸው የሚባሉትን መምረጥና መወሰን አስፈላጊ ነው፡፡ ከክልሉ ሕገ መንግሥት ዓላማዎች በተጨማሪ “የክልሉ ሕዝቦች ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲ ሥርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን ዕምነት እንዲሁም የክልሉን ሕዝብ የወደፊት የጋራ ዕድል” የክልሉ መዝሙር እንዲያንፀበርቅ ተደንግጓል፡፡ እነዚኽ ይዘቶች በሌሎቹ ክልላዊ መዝምሮች እንዲንፀባረቁ በተባሉበት ቦታ ተብራርቷል፡፡

የራሳቸው የትግራይ፣ የዐማራ፣ የኦሮሚያና የሶማሌ ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት በየራሳቸው ሕገ መንግሥት ስለ ክልል ሕዝብ መዝሙቻቸው የደነገጓቸውንና በሕዝብ መዝሙሮቻቸው የተንፀባረቁትን ይዘቶች ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

## ፫) የአራቱ ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት መዝሙሮች

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መዝሙር የክልሉ ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን እምነት እንዲያንጸባርቅ በክልሉ ሕገ መንግሥት አልተደነገገም፡፡ ይኽም የብሔራዊ ክልሉ ወጣቶች በየትምህርት ቤቶቹ የሚዘምሩት የኛ ስለሚሉት ስለ ኦሮሞ ሕዝብ ብቻ ይኾናል፡፡ ይኽም ስለ አንድነት የሚኖራቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ እንዲኾን ያደርጋል፡፡ ይኽ መኾኑም የአንድነት ሥነ ልቡና ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ የሕዝብ መዝሙር ዓላማ በዘማሪዎቹ አእምሮ አንድነትንና ብሔራዊ ስሜትን ማስረጽ መኾን ይገባዋል፡፡ የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት መሥራች ብሔሮችን አንድነት የማያንጸባርቅ መኾኑ ስለ አንድነት እንዲታሰብ አያደርግም፡፡ የክልሉን መንግሥት ትኩረትና ፍላጎት ለመረዳት አያስችልም፡፡ የሕዝብ መዝሙሩም የሚጠበቅበትን ተግባር እንዲያሳካ የሚያደርግ አይደለም፡፡ አልፎ ተርፎም መዝሙሩ ልዩነትን ይሰብካል፡፡ ከሌሎች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ሕዝቦች ጋር አብሮ መኖርን አያንፀባርቅም ስለ አንድነትም እንዲታሰብ አያደርግም፡፡ ይኽም አንድነትን ያላላል፡፡

የየብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታቱ መዝሙሮች በየብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታቱ የሚኖሩትን ሕዝቦች የወደፊት የጋራ ዕድል የሚያንጸባርቁ እንዲኾኑ በየሕገ መንግሥታቸው

ደንግገዋል፡፡ በተጠቀሱት ብሔራውያን ክልላውያን መንግሥታት የሕዝብ መዝሙሮች እንዲንጸባርቅ የተደነገገው ይዘት የየሕዝቦቹ የወደፊት ሕይወት የተሻለ እንዲኾን ይመኛል፡፡ ምኞት ደግሞ የተሻለ ኑሮ ለማግኘት መከጀልን፣ መፈለግንና መጓጓትን ይገልጻል፡፡ ዛሬ ያለው ነባራዊ ኹኔታ የነገውን የሕዝቦች ሕይወት ብሩኅነት ለመተንበይ አላስቻለም፤ ወይም አስተማማኝነት የለውም ማለት ነው፡፡ ቀጥለን የየብሔራዊ ክልላቸውን መዝሙር አዘጋጅተው የሚገለገሉትን እንመረምራለን፡፡

### ፫. ፩) የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መዝሙር

የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ በትግል ጊዜ ለቅስቀሳ ይጠቀምበትና ይዘምረው የነበረውን መዝሙር በትምህርት ቤቶች እንዲዘመር አድርጓል፡፡ መዝሙሩም የተደረሰው ብሔራዊ ክልላዊ ክልላዊ መንግሥቱ ከመቋቋሙና ሕገ መንግሥቱ ከመጽደቁ፣ እንዲኹም ከመታወጁ በፊት ነው፡፡ የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መዝሙር የትግሉን ከባድነትና አስቸጋሪነት በመግለጽ ማናቸውንም ዓይነት መስዋዕትነት በመክፈል ትግሉን ዳር ስለማድረስ የተጋድሎ ሓርነት ትግራይ ታጋዮች ያላቸውን ቁርጠኝነት ይገልጻል፡፡ መዝሙሩም ከአራቱም ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የሕዝብ መዝሙሮች በቁጥር የሚበልጡ ስንኞች አሉት፡፡ ዝርዝሩን የብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት ስለ ሕዝብ መዝሙር የተደነገገውን በማስቀደም እንመለከታለን፡፡

ተሻሽሎ የወጣውን የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥትን ለማጽደቅ በወጣው ዐዋጅ ቁጥር 45/1994 አንቀጽ 4 "የትግራይ ብሔራዊ ክልል መዝሙር የሕገ መንግሥቱን ዓላማዎች፣ የክልሉ ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር በዲሞክራሲ ስርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን እምነት፣ እንዲሁም የክልሉን ህዝብ ባህል፣ የትግል ታሪክ፣ አንድነትና ብሩህ ተስፋ የሚያንፀበርቅ ይሆናል፤ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፡፡" በማለት ይደነግጋል (አጽንኦት የተጨመረ)፡፡ በዚኽ ድንጋጌ "ህዝብ" የሚለው ቃል ኹለት ጊዜ፣ "ህዝቦች" የሚለው ደግሞ አንድ ጊዜ ተጠቅሰዋል፡፡ "ህዝብ" የሚለው ቃል ፖለቲካዊ ትርጉሙን ለመረዳት በሕገ መንግሥቱ የተጠቀሰበትን ዐውድ መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡ "የክልሉ ህዝብ" በሚለው ሐረግ ቃሉ የሚጠራው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ህልውና አለን ብለው የሚያምኑና የስነ ልቦና አንድነት ያላቸው እንዲሁም በአብዛኛው በተያያዘ መልከዓ የሚኖሩትን በጠቅላላ ነው (አንቀጽ 39 (6))፡፡ ይኸው ቃል ተሻሽሎ በወጣው የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት ማፅደቂያ ዐዋጅ ቁጥር 45/1994 አንቀጽ 39 "የትግራይ ብሐራዊ ክልላዊ ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት" እንዳላቸው በሚደነግገው አንቀጽ "ህዝቦች" ተብለው በብዙ ቁጥር መጠራታቸውን እናነባለን፡፡ "ህዝቦች" የተባሉትም በትግራይ ብሔራዊ ክልል የሚገኙ የትግራይ ብሔር፣ የኢሮብና የኩናማ ብሔረሰቦች መኾናቸው በዚኹ አንቀጽ ተመልክቷል፡፡ ስለኾነም፣ በተጠቀሰው ድንጋጌ "ህዝብ" የሚለው ቃል የሚጠራው በአንቀጽ 39 የተገለጹትን የተለያየ ቋንቋና ባህል ያላቸውን ብሔር፣ ብሔረሰቦች ነው፡፡

በተጠቀሰው ድንጋጌ "ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች" በሚለው ሐረግ "ህዝቦች" የሚለው ብዙ ቁጥር አመለካች ቃል የሚጠራው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁጥር ፩/፲፱፻፹፯ መግቢያ ላይ "የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች" በማለት የተጠሩትን ነው፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት መግቢያ በተጨማሪም በአንቀጽ ፴፱ (፩ - ፭) በተደነገጉት አንቀጾች የተጠሩት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ተብለው ነው፡፡ እነዚኽ መጠሪያዎች የተሰጧቸው ኅብረተ ሰቦች ያላቸው ባህርይ5 ልዩነት አንዱን ከሌላው ለመለየት የሚያስችል ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ የለም፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የተሰጣቸውን መጠሪያ በመተው "ህዝቦች" ብሎ መጥራት መጠሪያው አጥብቀው ከሚፈልጉ የፖለቲካ ሰዎች ጋር አለመግባባትን ሊያስከትል ይችላል፡፡ "እኛ ብሔር ነን" ወይም "ብሔረሰብ ነን" ብለው የሚያምኑ የፖለቲካ ድርጅት አባላት እንደ ስድብም ሊቆጥሩ ይችላሉ፡፡ ችግሩ ሊፈጠር የቻለው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ልዩነታቸው ምን እንደኾነ ተለይቶ ባለመቀመጡ በብሔራውያን ክልላውያን ሕግጋተ መንግሥታት ስህተቱ ተደገመ፡፡

የትግራይ ብሔራዊ ክልል መዝሙር የሕገ መንግሥቱን ዓላማዎች ማንፀባረቅ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ የሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች በሕገ መንግሥቱ መግቢያ እንደ ተገለጸው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥልጣንና ኃላፊነት ብቻ የሚተገበሩና ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር በመተባበር የሚተገበሩ ናቸው፡፡ በብሔራዊ ክልሉ ሥልጣንና ኃላፊነት የሚተገበሩት ዓላማዎች፣ የትግራይን ብሔራዊ ክልላዊ "ህዝቦች" ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያፈኑትን፣ ለድኽነትና ኋላ ቀርነት የዳረጉትን የተዛቡ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች ማስወገድ፣ በብሐራዊ ክልሉ ተንሰራፍቶ የሚገኘውን ድኽነትንና ኋላ ቀርነትን ማስወገድ፣ የትግራይ ብሔራዊ ክልል ሕዝብ ለኢኮኖሚ ዕድገት፣ ለዘላቂ ሰላምና ለጠንካራ ዲሞክራሲ እንዲበቃ ማስቻል የሚሉት ናቸው፡፡ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር በመተባበር የሚተገበሩት የሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች ደግሞ የኹሉንም ሕዝቦች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ማስከበር፣ ኢትዮጵያ በሕገ መንግሥት ብቻ እንድትመራ ማድረግ፣ "የግለሰብ መብቶችና የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል የተከበረበት በአጠቃላይ የሕግ የበላይነት የነገሠበት ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ረፐብሊክ መንግሥትን ማጠናከር፤ ማጎልበት፤ የጋራ ዕድገትን ማፋጠንና አንድ የጋራ ኢኮኖሚያዊ ማኅበረ ሰብ መገንባት" በማለት የተገጹት ናቸው፡፡

በብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት ምዕራፍ ዐሥር ከአንቀጽ 98 እስከ 102 የተደነገጉት የሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች ፖለቲካ ነክ፣ ኢኮኖሚ ነክ፣ ማኅበራዊ ነክ፣ ባህል ነክና የአካባቢ ነክ ዓላማዎች በማለት ተደንግገዋል፡፡ እነዚኽ ዓላማዎች እያንዳንዳቸው በርካታ ንዑሳነ አንቀጾች

---

[5] በአንቀጽ ፴፱ (፭) "በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ "ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ" ማለት ከዚህ ቀጥሎ የተገለጸውን ባህርይ የሚያሳይ ማኅበረሰብ ነው፡፡ ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑ፣ የሥነ ልቦና አንድነት ያላቸውና ባብዛኛው በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ ናቸው፡፡" በማለት ከተደነገገው አንዱን ከሌላው ለመለየት የሚያስችል ባህርይ አለመደንገጉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

አሏቸው፡፡ ዓላማዎችን መተግበርም የትግራይ ብሔራዊ ክልል መንግሥት ኃላፊነት መኾኑ ተድንግጓል፡፡

የትግራይ ብሔራዊ ክልል መዝሙር የክልሉ ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን እምነት የሚያንፀባርቅ እንዲኾን ተደንግጓል፡፡ ይኽ እምነት በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት መግቢያ "የሃገራችን ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በ[ባ]ካሄዱት አኩሪ ተጋድሎ አድሃሪውና አፋኙ ስርዓት በሚያስተማምን ሁኔታ ተደምስሶ ኢትዮጵያ ሃገራችን የግለሰብ መብቶችና የብሄር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ሙብት እስከመገንጠል የተከበሩበት፣ በአጠቃላይ የህግ የበላይነት የነገሰበት ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ረፐብሊክ መሆንዋ የጋራ ዕድገትን ለማፋጠንና አንድ የጋራ ኢኮኖሚያዊ ማሕረሰብ ለመገንባት ያለው[ን] ጠቀሜታ በመገንዘብ" ነው፡፡

አንድም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁጥር ፩/፲ ፱፻፹፯ መግቢያ ላይ የሚመሠረት ነው፡፡

እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ሰላም ዋስትና ያለው ዲሞክራሲ እንዲሰፍን ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገታችን እንዲፋጠን፣ የራሳችንን ዕድል በራሳችን የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን፣ በነፃ፣ ፍላጎታችን፣ በሕግ የበላይነት እና በራሳችን ፈቃድ ላይ የተመሰረተ አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ በጋራ ለመገንባት ቆርጠን በመነሳት፣

ይህን ዓላማችን ከግብ ለማድረስ፣ የግለሰብና የብሔር/ብሔረሰብ መሰረታዊ መብቶች መከበራቸው፣ የፆታ እኩልነት መረጋገጡ፣ ባሕሎችና ሃይማኖቶች ካለ አንዳች ልዩነት እንዲራመዱ የማድረጉ አስፈላጊነት ጽኑ እምነታችን በመሆኑ፣

ኢትዮጵያ ሀገራችን የየራሳችን አኩሪ ባህል ያለን ፣ የየራሳችን መልክዓ ምድር አሰፋፈር የነበረንና ያለን፣ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በተለያዩ መስኮችና የግንኙነት ደረጃዎች ተሳስረን አብረን የኖርንባትና የምንኖርባት ሀገር በመሆንዋ፣ ያፈራነው የጋራ ጥቅምና አመለካከት አለን ብለን ሰላምናምን፤

መጪው የጋራ ዕድላችን መመስረት ያለበት ከታሪካችን የወረስነውን የተዛባ ግንኙነት በማረምና የጋራ ጥቅማችን በማሳደግ ላይ መሆኑን በመቀበል፡፡

ጥቅማችንን፣ መብታችንንና ነፃነታችንን በጋራ እና በተደጋጋፊነት ለማሳደግ አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ የመገንባቱን አስፈላጊነት በማመን፤

በትግላችንና በከፈልነው መስዋዕትነት የተገኘውን ዴሞክራሲና ሰላም ዘላቂነቱን ለማረጋገጥ፤

የሚከተሉት ደግሞ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ የተገለጹና በተለያዩ አንቀጾች የተደነገጉ ናቸው፡፡ "ሁሉም ህዝቦች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸው የተከበሩ፣ በህገ መንግሥትና በሱ ብቻ የምትመራ ሃገር እንድትሆን በማመን፣" "በአብዛኛው የሀገራችን ብሄር ብሄረሰቦች ህዝቦች ላይ ይፈፀም በነበረው አንገፍጋፊ ጭቆና ተጎጂ ሆነን መቆየታችን በማያዳግም ሁኔታ መታረም እንዳለበት በማመን፣"

"ኢትዮጵያ ሃገራችን የግለሰብ መብቶችና የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል የተከበሩበት፣ በአጠቃላይ የህግ የበላይነት የነገሰበት ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ረፑብሊክ መሆንዋ የጋራ ዕድገትን ለማፋጠንና አንድ የጋራ ዕድገትን ለማፋጠንና አንድ የጋራ ኢኮኖሚያዊ ማሕበረሰብ ለመገንባት ያለው ጠቀሜታ በመገንዘብ፣ እኛ በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የምንገኝ ህዝቦች ለፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት፣ ለዘላቂ ሰላምና ጠንካራ ዲሞክራሲ የምንበቃው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት መሰረት ያደረገ፣ ከብሄራዊ ክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተዛመደና የዚህ ክልል ህዝቦች የተከበሩበትና ሐገ መንግስታዊ መብቶች ሳይሸራረፉ ስራ ላይ ለማዋል የሚያስችለን የራሳችን ሕገ መንግስት ሲኖረን መሆኑን በሚገባ በማመን፣"

የብሔራዊ ክልሉ መዝሙር የትግራይን ብሔራዊ ክልላዊ ሕዝብ ባህል የሚያንፀበርቅ እንዲኾንም በሕገ መንግሥቱ ተደንግጓል፡፡ ይኽ ድንጋጌ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፴፱ (፩) የትግራይ ብሔር፣ የኢሮብና የኩናማ ብሔረሰቦች እያንዳንዳቸው የራሳቸውን ማንነት የመጠበቅና የማክበር፣ ቅርሳቸውንና ታሪካቸውን የመንከባከብና የማበልጸቅ እንዲሁም በቋንቋቸው የመጠቀም፣ ቋንቋቸውን የማሳደግ፣ ባህላቸውን የመግለጽ፣ የማዳበርና የማስፋፋት መብት አላቸው የሚለውን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የባህል ክፍል የኾነው ቋንቋ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንገሥት ዘንድ እኩል እውቅና እንደሚኖራቸው በአንቀጽ ፫ (፩) ተደንግጓል፡፡ ቋንቋቸው እውቅና የተሰጣቸው የትግራይ ብሔር፣ የኢሮብና የኩናማ ብሔረሰቦች[6] ይሁኑ እንጂ፣ የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሥራ ቋንቋ ትግርኛ (አንቀጽ ፫ (፪)) በመኾነ የኢሮብና የኩናማ ብሔረ ሰቦች የብሔራዊ ክልሉን የሥራ ቋንቋ ትግርኛን መማርና መናገር ይጠበቅባቸዋል፡፡

በብሔራዊ ክልሉ መዝሙር የሚንፀባርቁት ባህል ነክ ዓላማዎች በአንቀጽ 101 ባህል ነክ ዓላማዎች በማለት ተደንግገዋል፡፡ ድንጋጌዎቹም፡- "መንግሥት መሠረታዊ መብቶችና ሰብዓዊ ክብርን እንዲሁም ለዲሞክራሲው ሕገ መንግስት የማይቃረኑ ባህሎችና ልማዶች በእኩልነት እንዲጎለብቱና እንዲያድጉ የመርዳት ሃላፊነት አለበት" (አንቀጽ 101 (1))፡፡ "የተፈጥሮ ሀብቶችንና የታሪክ ቅርሶችን መጠበቅ የመንግሥትና የሁሉም የክልሉ ነዋሪዎች ግዴታ ነው" (አንቀጽ 101 (2))፡፡ "መንግስት አቅም በፈቀደ መጠን ኪነጥበብን፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ግዴታ አለባቸው" (አንቀጽ 101 (3)) የሚሉ ናቸው፡፡

የትግራይ ሕዝብ የትግል ታሪክ በብሔራዊ ክልሉ መዝሙር እንዲፀባረቅ ተደንግጓል፡፡ ይኸው የሕዝቡ የትግል ታሪክም በብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት መግቢያ "የትግራይ ሕዝብ ያለፉት ጨቋኝ ስርዓቶችን ለመደምሰስ ወደር የሌለው መስዋዕትነት" ከፍሏል በማለት ተገልጿል፡፡ ያለፉት ጨቋኝ ሥርዓቶች የሚለው አገላለጽ የትግራይ ሕዝብ ትግል የዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ፣ የቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥታትንና የወታደራዊ አስተዳደር ደርግን እንደ ነበር

[6] በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥታዊ ዕውቅና ከተሰጣቸው ከኢሮብና ከኩናማ ብሔረሰቦች ቁጥር የዐማራ ብሔር አባላት ቁጥር ይበልጣል፡፡ ይሁን እንጂ፣ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት ዕውቅና አልተሰጠውም፡፡ በቋንቋው ለመማርና ለመዳኘት፣ ባህሉን ለመግለጽና ለመንከባከብ፣ በታሪኩ ለመኩራት፣ ራሱን በራሱ ለማስተዳደር፣ ለመመረጥና በብሔራዊ ክልሉ መንገሥት አስተዳደር ለመወከል የምችልበት መብት አልተሰጠውም፡፡

ከታሪካችን እንረዳለን፡፡ ዐፄ ዮሐንስ 4ኛ በ1881 ዓ.ም. መተማ ላይ ከሞቱ በኋላ ሥልጣነ መንግሥቱን ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ መውረሳቸው ያስከፋቸው የትግራይ መሳፍንት በተለያዩ ጊዜያት ያምጹ ነበር፡፡ በተለይም የዐፄ ዮሐንስ 4ኛ ሥልጣነ መንግሥት ሕጋዊ ወራሽ "እኛ ነን" ይሉ በነበሩት ራስ መንገሻ ዮሐንስ ይመራ በነበረው ተቃውሞ ከጠቅላይ ግዛቱ አርሶ አደር የተወሰነው ወዶም ኾነ ተገዶ ተባባሪ ነበር፡፡ በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥትም ከጠቅላይ ግዛቱ መሳፍንት በማዕከላዊው መንግሥት የሚከፉ ነበሩ፡፡ በ1928 ዓ. ም. ደጃዝማች ጉግሳ ኃይለ ሥላሴ ከኢጣሊያ ጎን ተሰልፈው ትግርኛ ተናጋሪዎችን አሰልፈው ኢትዮጵያውያን ዐርበኞችን የመውጋታቸው ምክንያት በማዕከላዊው የኢትዮጵያ መንግሥት "ተገፍቻለኹ" በሚል ነው፡፡ የትግራይ ሕዝብ በቀጣት ከፍተኛ ገንዘብ እንዲከፍል ተደርጓል፤ የገበሬው መሬት እየተነጠቀ ለመንግሥት ታማኞች ተከፋፍሏል፤ በኢጣሊያ ጊዜ ይከፍለው ከነበረው ግብር ዐምሥት እጥፍ የበለጠ እንዲከፍል ተደረጓል፣ ማዕከላዊ መንግሥትን በማጠናከር ስም የጠቅላይ ግዛቱ የሥልጣን ወራሾችሥልጣን በመንጠቅ ለሸዋ ገዥ መደብ መስጠታቸውን በመቃወም ወያኔ በሚል ስም የተደራጁ ገበሬዎች በማዕከላዊና በደቡባዊ ትግርይ ዐመጹ፡፡ በ1943 (እ. አ. አ.) የእንግሊዝ መቀሌን ጨምሮ በተለያዩ በቶታዎች ሮያል አየር ኃይል ከአየር ወደ መሬት በወረወራቸው ቦንቦች አመፁ ተገታ (Aregawi Berhe, 2004: 572)፡፡ የቀዳማይ ወያኔን ፈለግ የተከተሉ በተለያዩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ይማሩ የነበሩ የጠቅላይ ግዛቱ ተወላጅ ተማሪዎች ወደ ጫካ በመግባት የካተት 11 ቀን 1967 ዓ. ም. የቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት መታገል ጀመሩ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ትግላቸውን በጀመሩ በጥቂት ቀናት ውስጥ የቀዳማ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ሥልጣኑን በወታደራዊ መኮንኖች ተነጠቀ፡፡ የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር የሥልጣን ለውጥ እንጂ የሥርዓት ለውጥ አልተደረገም በማለት የኢትዮጵያ ወታደራዊ መንግሥትን በሽምቅ ውጊያ መፋለሙን ቀጠለ፡፡ ከኤርትራ ነጻ አውጪ ግንባርና በኋላም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ ጋር በመተባበር እስከ 1983 ዓ. ም. በዘለቀ ጦርነት ወደ ሥልጣን መጣ፡፡

በትግራይ ብሔራዊ ክልል መንግሥት ሕገ መንግሥት መግቢያ "መላ የሀገራችን ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ባካሄዱት አኩሪ ተጋድሎ አድሃሪውና አፋኙ ስርአት በሚያስተማምን ሁኔታ" መደምሰሱ ተገልጿል፡፡ ይኽ የተባለበት ምክንያት፣ አንድም የትግራይ ነጻ አውጭ ግንባር የተለያየ ባህል፣ የተለያየ ቋንቋ፣ የተለያየ ሥነ ልቦና ወዘተ. ከነበራቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ አባላት ጋር ግንባር ፈጥሮ በመታገሉ ነው፡፡ አንድም፣ የተለያዩ ብሔሮችን ነጻ ለማውጣት ይታገሉ ከነበሩ ለምሳሌ፣ የሲዳማ አርነት ንቅናቄ (ሲአን)፣ የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ግንባር (ኦብነግ) የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) ጋር ግንባር በመፍጠሩ፣ አንድም፣ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ይፈጽም በነበረው ጥፋት የተከፉ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለውጥ በመፈለጉ ምክንያት የሽምቅ ውጊያ ያካኼዱ የነበሩትን ኃይሎች በቀጥታም ኾነ በተዘዋዋሪ መንገድ በመደገፉ ነው፡፡ ይኸም ኾኖ፣ ኹሉም ኢትዮጵያዊ ለውጡን ለማምጣት እኩል ተሳትፎ ነበራቸው የሚለው ፖለቲካዊ አገላለጽ ነው፡፡

መዝሙሩ የትግራይ ሕዝቦችን የትግል ታሪክ እንዲያንፀባርቅ የሚለው ወቅታዊ ጉዳይ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ የትግራይ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የሚጋራው አኩሪ ታሪክ እንዳለው ቢታወቅም፣ በመዝሙሩ እንዲንፀባረቅ አልተደነገገም፡፡ ይኸም በክልሉ መዝሙር እንዲነፀባረቅ የተባለው ታሪክ ትውልዱ የባቶቹን ታሪክ ለማውቅ የማያነሣሣ፣ የሀገር ሉዓላዊነትን

ለመጠበቅ የተከፈለውን መስዋዕትነት የማይነግር፣ በዶጋሊና በዐድዋ የተገኘውን ድል የማያስታውስ፣ ማይጨው ላይ የተከፈለውን መስዋዕትነትና የዐምሥቱን ዓመት የዐርበኝነት ተጋድሎ ለትውልድ የማይነግር ነው፡፡ በመዝሙሩ እንዲንፀባረቅ የተባለው ታሪክ ትውልዱ ትሕነግ ከ1967 እስከ 1983 ያደረገውን ትግል ብቻ እንዲያስብ፣ እንዲገነዘብ፣ እንዲረዳ፣ እንዲያደንቅ ታስቦ የተደረገ ነው፡፡

በመዝሙሩ እንዲንፀባረቅ የተባለው የትግ ታሪክ ከማን ጋር የተሠራ ነው? ለሕዝቡስ ምን አስገኘ? ለሚሉት ጥያቄዎች የሚሰጠው መልስ አሉታዊነቱ ያመዝን ነው፡፡ ትሕነግ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግን የወጋው ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ይዋጋ ከነበረው የኤርትራ ነጻነት ግንባር ጋር በመተባበር ነው፡፡ ትሕነግ ኤርትራ በመግባት ከኤርትራ ነጻነት ግንባር ጎን ተሰልፎ የኢትዮጵያን ሠራዊት ወግቷል፡፡ የትግራይ ሕዝብ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ይዋጋ የነበረውን ሕዝባዊ ሓርነት ኤርትራ በመደገፍ ለስኬቱ መስዋዕትነት መክፈል በሰከነ አእምሮ ሲታሰብ ትውልድን የሚያኮራ ታሪክ ሳይኾን የሚያሳፍርና የሚያስወቅስ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የተለያዩ ቦታዎች በተደረጉ ውጊያዎች የኤርትራ ነጻነት ግንባር መካናይዝድ ኃይልን ማሰለፍ፣ አዲስ አበባንም መቆጣጠር የትግል ታሪክ የተባለው ከኢትዮጵያ ጥቅም ተጻራሪ ኃይል ጋር የነበረውን መተባበር ያስረዳል፡፡

ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል (ለመነጠል) ይዋጋ ከነበረው ሕዝባዊ ሓርነት ኤርትራ ግንባር ጋር መተባበርም ራስ አሉላ አባ ነጋ ዶጋሊ ላይ በጣሊያን ጦር ያስመዘገቡትን ታሪካዊ ድል መጻረር ነው፡፡ ራስ አሉላ የተዋጉለትን ዓላማ የሚጻረር ተግባር ፈጽሞ፣ ለራስ አሉላ ሐውልት መሥራትና የመቀሌን አውሮፕላን ማረፊያ በእሳቸው ስም መጥራት የታሪክ ተቃርኖ መፈጸም ነው፡፡

በብሔራዊ ክልሉ መዝሙር እንዲነፀባረቅ የተባለው የትግል ታሪክ ለትግራይ ብሔራዊ ክልል "ህዝቦች" በተለይ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በጠቅላላ ምን አስገኘ? ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ይፈጽም የነበረውን ግድያና እስራት ለማስወገዱ በማስቻሉ የሚመሰገን ተግባር እብዳከናወነ ይታመናል፡፡ ይሁን እንጂ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ አስተዳደር ቋንቋ መሠረት ባደረገ የፌዴራል አስተዳደር በመዋቅርና በማንነት ላይ የሚያተኩር የፖለቲካ ሥርዓት እንዲራመድ በግንባር ቀደምነት በመምራቱ የትግራይን "ህዝቦች"ም ኾነ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለክፍፍልና ለመፈናቀል፣ ለግጭትና ለሞት ዳረገ፡፡ ስለኾነም የትግራይ "ህዝቦች" የትግል ታሪክ በብሔራዊ ክልሉ መዝሙር እንዲንፀባረቅ መደረጉ ትውልዱ በአርአያነት የሚከተለው ሳይኾን የሚተወውና የሚያስወግደው ነው፡፡

የትግራይ ብሔራዊ ክልል መዝሙር እንዲያንፀባርቅ በሕገ መንግሥቱ ከተደነገጉት መካከል "የክልሉን ህዝብ አንድነትና ብሩህ ተስፋ የሚያንፀበርቅ ይሆናል" የሚለው ይጠቀሳል፡፡ የክልሉ "ህዝብ" አንድነት በብሔራ ክልሉ መዝሙር እንዴት እንደሚንፀባረቅ ግልጽ አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ፣ በክልሉም ኾነ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት እንዲነግሥ ከተደረገ፣ በክልሉ የሚኖሩት የትግራይ ብሔር፣ የኢሮብና የኩሙዝ ብሔረሰቦች የየራሳቸውን ማንነት መጠበቅና ማስከበር ከቻሉ፣ ቅርሳቸውንና ታሪካቸውን መንከባከብና ማበልጸግ፣ እንዲሁም በቋንቋቸው የመጠቀም፣ ቋንቋቸውን የማሳደግ፣ ባህላቸውን መግለጽ፣

ማዳበርና ማስፋፋት ከቻሉ፤ ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር ከቻሉ፣ የመምረጥና የመመረጥ መብታቸው ከተከበረ የክልሉ "የህዝቦች አንድነት" ይጎለብታል፡፡

በመዝሙሩ የህዝቡ ብሩህ ተስፋ እንዲንፀባረቅ በማለት በብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት የተደነገገው ሐሳብ በሕገ መንግሥቱ መግቢያ "ሁሉም ህዝቦች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ተከበሩ፤ በህግ መንግስትና በሱ ብቻ የምትመራ ሃገር እንድትሆን በማመን፤" "የክልሉ ህዝቦች የተከበሩበትና ሕገ መንግስታዊ መብቶች ሳይሸራረፉ ሥራ ላይ መዋል መቻላቸውን በማመን" በማለት ተገልጸዋል፡፡ በብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት በተለያዩ አንቀጾችም ተደንግገዋል፡፡ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፡፡

በብሔራዊ ክልሉ መዝሙር እንዲንፀባረቁ የተደነገጉትን፣ የሚያንፀባርቅ በዐዋጅ የጸደቀና ስለ አጠቃቀሙ ዝርዝር መመሪያ የወጣለት መዝሙር ማግኘት አልተቻለም፡፡ በአንጻሩ በብሔራዊ ክልሉ ለረጅም ጊዜ አገልግሎት የሰጠ መዝሙር እንዳለ ይታወቃል፡፡ ይኸ መዝሙር የተደረሰው ሕወሓት ደርግን (በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥትን) አሸንፎ ሥልጣን ከመያዙ በፊት ነው፡፡ መዝሙሩ መቼና ማን እንደደረሰው ባይታወቅም ደርግን ከሥልጣን ለማስወገድ ባደረገው ጦርነት ለቅስቀሳ ያገለገለ ነው፡፡ ደርግ ከሥልጣን ከተወገደ በኋላም በትግሉ ጊዜ ለቅስቀሳ ያገለግል የነበረው መዝሙር አገልግሎት መስጠቱን ቀጥሎ በብሔራዊ ክልሉ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ጧት ጧት የሕወሓት ዓርማ የነበረው የክልሉ ሰንደቅ ዓላማ ሲሰቀልና በብሔራዊ ክልሉ አንዳንድ ዝግጅቶች ላይም ሲዘመር ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ፣ መዝሙሩ በዐዋጅ አልጸደቀም፣ መመሪያም አልወጣለትም፡፡ የዚኸ የመዝሙር ይዘት ምን እንደኾነ ለመረዳት በትግርኛ የተጻፈውን በማስቀደም የዐማርኛውን ትርጉም እንመለከታለን፡፡

<u>መስመር እዩ ሓይልና</u>[7]

ዘይንድይቦ ጎቦ ዘይንሰግሮ ሩባ

*መንጉሕ...* ፍፁም ወይ ከ የለን

መስመርዩ ሓይልና ህዝቢ'ዩ ሓይልና

ወይ ከ ኣይንምብርከኽን

ሃሩር ፀሓይ ነዳድ ህቦብላ ማይ በረድ

ማይ ማይ ትበል ነብሲ ኣብ ጀቕጀቕ ንረግረግ

ደንጎላ ንትርኣስ በዓቲ ይኹን ቤትና

ለይትን ቀትርን ጉዕዞ ንድከም ይጥመየና፡፡

መስመር'ዩ ሓይልና ህዝቢ'ዩ ሓይልና ወይከ ኣይንሰዓርን

መስመር'ዩ ሓይልና ህዝቢ'ዩ ሓይልና ወይከ ኣይንሰዓርን

ዘይንድይቦ ጎቦ ዘይንሰግሮ ሩባ

ፍፁም ወይ ከ የለን

---

መምርሒ ስርዓት ትምህርቲ ፓነል ኤስቴቲክስ ጥንካረ ኣካልን (መዳለዊ)፤ ትምህርቲ ኤስቴቲክስን ጥንካረ ኣካልን መምርሒ ንመምህር 1ይ ክፍሊ፣ 1995፤ X፡፡

መስመር'ዩ ሓይልና ህዝቢ'ዩ ሓይልና
ወይ'ከ ኣይንብርከኽን
    ንከበብ በዛብእ መሬት ትፅበበና
    ኣብ ስጋና ይቀርቀር ኣስናን ፀላእትና
    ስጋና ንኣሞራ ደምና ውሕጅ ይኹን
    ኣዕፅምትና ይድቀቕ ሕሩጭ ኮይኑ ይበተን
መስመር'ዩ ሓይልና ህዝቢ'ዩ ሓይልና ከባታት ፀላኢ ክንፍንፅሖ ኢና (2)
ዘይንድይቦ ጎቦ ዘይንሰግሮ ሩባ
ፍፁም ወይ ከ የለን
መስመር'ዩ ሓይልና ህዝቢ'ዩ ሓይልና
ወይ ከ ኣይንብርከኽን
    ናይ መድሓርሓርቲ ጋዝ ፋሽሽታዊ ንዳድ
    ሚልዮን ቁምቡላታት ኣብ ቅድሜና ይንጎድ
    መስዋእትን መቑሰልትን ከሳራታት ንኽፈል
    ዝኽፍአ መከራ ውዲታት ይፍተልተል፡፡
መስመር'ዩ ሓይልና ህዝቢ'ዩ ሓይልና ከባታት ፀላኢ ክንፍንፅሖ ኢና (2)

የመዝሙሩ የዐማርኛ ትርጉም ቀጥሎ የቀረበው ነው፡፡

<u>መስመራችን ኀይላችን</u>

'ማንወጣው ተራራ፣ 'ማንሻገረው ወንዝ
ፍጹም የትም የለም!
ዓላማ ግባችን፣ ሕዝብ ነው ኃይላችን፣ ከቶ አንሸነፍም!

የፀሐዩዋ ንዳድ፣ የበረዶ ወጀብ፣ ይዝነብ ከላያችን
በጥም እንቃጠል፣ ረግረግ ይያዘን
ደንጊያን እንንተራስ፣ ዋሻ ቤት ይኹነን
በሌት ተቀን ጉዞ፣ እንድከም ይራበን፡፡

ዓላማ ግባችን፣ ሕዝብ ነው ኃይላችን፣ ከቶ አንሸነፍም!
ዓላማ ግባችን፣ሕዝብ ነው ኃይላችን፣ ከቶ አንሸነፍም!

'ማንወጣው ተራራ፣ 'ማንሻገረው ወንዝ
ፍጹም የትም የለም!
ዓላማ ግባችን፣ ሕዝብ ነው ኃይላችን፣ ከቶ አንሸነፍም!

በጅቦች ተከበን፣ መውጫ መግቢያ እንጣ
የጠላታችን ጥርስ፣ ከሥጋችን ይግባ፣ እንደሾኽ ጋሬጣ
ሥጋችን ላሞራ፣ ደማችን ወንዝ ይኹን
አጥንታችን ይድቀቅ፣ በነፋስ ይበተን
መስመር ነው ኃይላችን፣ የጠላት ከበባን ፣ መኻሉን ሰንጥቀን
አይቀር ማለፋችን!

'ማንወጣው ተራራ፣ 'ማንሻገረው ወንዝ
ፍጹም የትም የለም!
ዓላማ ግባችን፣ ሕዝብ ነው ኃይላችን፣ ከቶ አንሸነፍም!

የአድሃሪያን ጋዝ፣ ፋሺስታዊ ንዳድ፣ ሺ ተሚልዮን ፈንጂ፣
ይፈንዳ ከኛ ፊት
እንከፈል ኪሣራ፡- ሞት፣ ቁስለት፣ እንግልት
የከፋ መከራ፣ ሤራም ይጥፋ፣ ይሙት
መስመር ነው ኃይላችን፣ የጠላት ከበባን ፣ መኻሉን ሰንጥቀን አይቀር
ማለፋችን! (2)

መዝሙሩ የተነገረው "እኛ" በሚል አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር አመልካች ተውላጠ ስም ነው፡፡ "እኛ" የሚለው የድርጅቱን አባላት ነው፡፡ በመዝሙሩ "ሕዝባችን ኃይላችን" በማለት ተደጋግሞ የተጠራው ደግሞ የትግራይ ሕዝብ ነው፡፡ "ሕዝባችን" የሚለው የእኛ ሕዝብ ማለትን ይገልጻል፡፡ ይኽም፣ አንድም፣ የሕዝቡ ባለቤት የፖለቲካ ድርጅቱ (ሕወሓት) ነው፡፡ በባለቤትነቱም ሕዝቡን እንደፈለገ ያዘዋል፤ ያሰማረዋል፤ በአጭሩ የፖለቲካ ድርጅቱ አዛዥ፣ ሕዝቡ ደግሞ ታዛዥና ትእዛዝ ተቀባይ ነው ማለት ነው፡፡ እንድም፣ ሕዝቡ የፖለቲካ ድርጅቱ

አጋር ነው ማለት ነው፡፡ በአጋርነቱም የፖለቲካ ድርጅቱ ትብብር ሲጠይቀው ይተባበራል፤ ሕዝቡ የፖለቲካ ድርጅቱ ትእዛዝ የመቀበል ግዴታ የለበትም ማለት ነው፡፡

የሕዝብ መዝሙሩ ዋና መልእክት ሕወሓት በትግሉ ኺደት የሚያጋጥሙትን የተለያዩ መሰናክሎች አልፈን፣ ጠላታችንን አሸንፈን ዓላማችንን እናሳካለን የሚል ነው፡፡ በመዝሙሩ ተፈጥሮ በአሉታዊነትና በአዎንታዊነት ተገልጹዋል፡፡ ስለ ተፈጥሮ በዝቶ የተነገረው አሉታዊነቱ ነው፡፡ ይኸውም፣ ለትግል የተሰለፉት ሰዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ተራሮችና ወንዞች ፈተናዎች ሆነውባቸዋል፡፡ ኹኖም፣ በትግሉ የተሰለፉትን ያጋጠሟቸውን ተራሮች ኹሉ በመውጣትና ወንዞችን በማቋረጥ የትግሉን ዓላማ እንደሚያሳኩ ያላቸውን እምነት መዝሙሩ ይገልጻል፡፡ የፀሐይ ሙቀት ቢያቃጥላቸውም ውሃ ጥም ቢያጋጥማቸውም፣ በበረዶ ቢደበደቡም፣ ከሰማይ በሚወርደው ዶፍ ለብርድ ቢጋለጡም፣ በረግረግ ቢዋጡም ዓላማቸውን ለማሳካት ከሚያደርጉት ጎዞ አለመገታታቸውን የተፈጥሮ ገጽታዎች የሚደርሱባቸውን ችግሮች ተቋቁመው ዓላማቸውን ለማሳካት መቁረጣቸውን መዝሙሩ ያስረዳል፡፡

በተለያዩ ቦታዎች ከሚገኙ የትግሉ አጋሮች ጋር ለመገናኘት፣ ሕዝብን ለማደራጀት፣ በጠላት ላይ ጥቃት ለመሰንዘር፣ ከጠላት ጥቃት ለመሸሽ ወዘተረፈ ሌሊት በጨለማ፣ ቀን በብርሃን እንቅስቃሴ ማድረግና መጓዝ ትግሉ የሚጠይቀው ተግባር ነው፡፡ ጉዞው ረጅምና የማያቋርጥ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ የተሟላ ስንቅ ሳይኖር ሌት ተቀን በሚደረግ ጉዞ መራብ መጠማት ይኖራል፡፡ ይኽን ዓይነት የትግል ገጠመኝ "በሌት ተቀን ጉዞ እንድከም ይራበን" የሚለው ስንኝ ይገልጻል፡፡

በትግሉ የሚደረገው እንቅስቃሴ ራስን ከአውሬ ጥቃት ለመከላከል የሚያስችል መሣሪያ ሳይያዝ በተናጠልና ሰው በማይኖርበት አካባቢ የሚደረግ ይኾናል፡፡ ሌሊት በጨለማ ወይም በጨረቃ በተናጠል በሚደረግ ጉዞ ጥቃት ሊያደርሱ የሚችሉ የዱር አውሬዎች ያጋጥማሉ፡፡ ጥቃት ከሚያደርሱት የዱር አውሬዎች መካከል በመዝሙሩ የተጠቀሰው ጅብ ነው፡፡ ታጋዮች በጅቦች ከበባ መግቢያ መውጪያ ቢያጡም ዓላማቸውን ግብ ለመምታት ከሚያደርጉት ጉዞ ወይም የትግል እንቅስቃሴ ወደ ኋላ እንደማይሉ "በጅቦች ተከበን፣ መውጪያ መግቢያ እንጣ" የሚለው ስንኝ ያስረዳል፡፡

በመዝሙሩ እንደ ተገለጸው ተፈጥሮ የትግል መሰናክል ብቻ ሳይሆን አጋር ነው፡፡ ምቹ ትራስ በማይገኝበት የትግል ቦታ ድንጋይን መንተራስ ይኖራል፡፡ መጠለያ በሌለበት የተፈጥሮ ዋሻን እንደ ቤት በመጠቀም ራስን ከብርድ፣ ከዝናብ፣ ከጠላት እይታ መሰወር ያስችላል፡፡ ይኽንንም "ድንጊያን ተንተርሰን፣ ዋሻ ቤት ይሁነን" በሚለው ስንኝ የተገለጽው ሐሳብ ያስረዳል፡፡

መዝሙሩ ጠላት ሊያደርስ የሚችለውን ጥቃት በመዘርዘር ዓለማቸውን ለማሳካት ከሚያደርጉት ጎዞ እንደማይገቱ ይገልጻል፡፡ "የጠላታችን ጥርስ ከሥጋችን ይግባ እንደሾህ ጋሬጣ" የሚለው ስንኝ በትግሉ በተሳተፉት ላይ ከሚደርሱት ጥቃቶች አንዱ ነው፡፡ እንዲኽ ዓይነቱ ጥቃት እንዴት ሊደርስ ይችላል? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፡፡ የተቃዋሚና የመንግሥት ኃይሎች በጦር መሣሪያ ከመጠቃቃት አልፈው የጨበጣ ውጊያ ሊገጥሙ ይችላሉ፡፡ በጨበጣ ውጊያም፣ በተገኘው መሣሪያ ይጠቃቃሉ፡፡ በሳንጃ መወጋጋት፣ በሰደፍ መመታታት፣ በድንጋይ መወጋገር፣ በቡጢ መናረት፣ በጥርስ መነካከስ፣ ተጠመዛዞ መጣጣል ወዘተረፈ ሊፈጸም ይችላል፡፡

በመዝሙሩ የተገለጸው በጥርስ ንክሻ የመጠቃት እውነትነት አለው የሚባለው በተጠቀሰው ምክንያት ነው፡፡

ትግሉን ወግነው በተሰለፉትና ሕወሓት በጠላትነት በፈረጃቸው የኢትዮጵያ ሠራዊት አባላት መካከል በሚደረገው የጦር መሣሪያ ትግል ሞትና ቁስለት ያጋጥማል፡፡ ደም እንደጎርፍ ይወርዳል፡፡ በመንግሥት ጥይት ለቆሰለ ርዳታ ለመስጠት፣ የሞተን የተቃዋሚ ወገን አስከሬን ለማንሣት፣ የማይቻልበት ኹኔታ ይፈጠራል፡፡ ከጠላት በደረሰ ጥቃት የሞተን ታጋይ አስከሬን ማንሣት በማይቻልበት ጊዜ የሚችን አስከሬን ሥጋውን አሞራና የዱር አውሬ ሊበላው ይችላል፡፡ በቀላል ወይም በጠንካራ የህክምና ርዳታ መዳን ይችል የነበረ ቁስለኛ ለሞት ይዳረጋል፡፡ ከዚኽም ሌላ፣ በጠላት ጥይት ወይም ፈንጂ አጥንቱ የሚከሰከስና የሚሰባበር ይኖራል፡፡ ይኽን ደርጊት መዝሙሩ፡-

ሥጋችን ላሞራ፣ ደማችን ወንዝ ይሁን፣
አጥንታችን ይድቀቅ፣ በነፋስ ይበተን፡፡

በማለት ይገልጸዋል፡፡

"ፋሺስቱ ደርግ" ከሰማይ በሚያዘንበው ቦንብ፣ በሚያፈነዳው ፈንጂ ሞት፣ ቁስለትና እንግልት በታጋዮቹ ላይ ቢደርስብንም በሽንፈት አንበረከክም፤ ዓላማችን ዳር ለማድረስ በጠራ መስመራችን እየተመራን ሕዝባችንን ከጎናችን አሰልፈን የጠላትን ከበባ ሰንጥቀን ወደ ዓለምነው ግብ እንደርሳለን የሚል መልእክት ተገለጿል፡፡

ከዚኽ በላይ እንደተገለጸው የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መዝሙር የሚገልጸው በሕወሓትና በደርግ መካከል የሚካኼደው ጦርነት በመካኼድ ላይ መኾኑንን ነው፡፡ መዝሙሩን በየትምህርት ቤቶቻቸው የሚዘምሩትን ተማሪዎችም ለትግል፣ ለመስዋዕትነት የሚጋብዝ ነው፡፡ ከዚኽም በላይ በብሔራዊ ሕገ መንግሥቱ መዝሙሩ እንዲያንጸባርቅ የተደነገጉትን ነጥቦች አልገለጸም፤ ወይም በሥራ ላይ የሚገኘውን መዝሙር አጽድቆ አላለፈም፡፡

### ፫. ፪) የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መዝሙር

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት በአንቀፅ ፩ "የአማራ ብሔራዊ ክልል የራሱ መዝሙር ይኖረዋል፡፡ የብሔራዊ ክልሉ መዝሙር የሕገ-መንግሥቱን ዓላማዎች፣ የክልሉ ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ ለመኖር ያለውን እምነት እና የክልሉን ሕዝብ የወደፊት የጋራ ዕድል የሚያንፀባርቅ ሆኖ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡" በማለት ይደነግጋል፡፡ የብሔራዊ ክልሉ መዝሙር የሚያንፀባርቃቸው የሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ሕገ መንግሥት በመግቢያውና በሕገ መንግሥቱ ከአንቀጽ 108 እስከ አንቀጽ 113 በተደነገጉት አንቀጾችና ንዑስ አንቀጾች ተደንግገዋል፡፡ በሕገ መንግሥቱ መግቢያ ላይ የተገለጸውም፣ በተለያዩ አንቀጾችና ንዑስ እንቀጾች የተደነገጉት የሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ ሕገ መንግሥት ከተደነገገው ጋር ተመሳሳይ በመኾኑ በዚኽ ክፍል ደግሞ ማስረዳት አስፈላጊ አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ፣ የአማራ ብሔራዊ ክልል መዝሙር የሕዝቡን የትግል ታሪክ በመዝሙሩ እዲንጸባረቅ አልተደነገገም፡፡

የክልሉ ህዝብ መዝሙር አጠቃላይ ዝግጅት የተከናወነው ክልሉ በአቋቋመው አምስት አባላት ያሉት አስተባባሪ ኰሚቴ ነው፡፡ የዝግጅት ሥራውም ሶስት ዓብይ ምዕራፎችን ያለፈ ሲሆን የመጀመሪያው ምዕራፍ ለመዝሙር የሚሆነውን ግጥም የማዘጋጀት ስራ ነው፡፡ ሁለተኛው ምዕራፍ ለተመረጠው ግጥም ዜማ የማዘጋጀት ስራ ሲሆን የመጨረሻው ምዕራፍ ደግሞ ለግጥሙ የተመረጠውን ዜማ ደረጃውን በጠበቀ አ[ኦ]ርኬስትራና ስቱድዮ እንደገና ተስተካክሎ እንዲቀረጽ ማድረግ ነው፡፡

በመጀመሪያው ምዕራፍ የዝግጅት ኰሚቴው በመዝሙር ግጥም ውድድር ማስታወቂያ ካሰባሰባቸው ግጥሞች መስፈርቱን ያሟሉ ብሎ በደረጃ መርጦ ያቀረባቸውን ሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴው ለ3ኛው መደበኛ ጉባኤ አቅርቦ ም/ቤቱ እንዲመክርበትና ውሳኔ እንዲሰጥበት አድርጓል፡፡[8] (የአማራ ብሔራዊ ክልል መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ 1985 - 1992፤ 13)

"የብሔራዊ ክልሉ 3ኛው መደበኛ ጉባዔ በሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ግጥሙ በኰሚቴው ተስተካክሎ ከቀረበ በኋላ ኰሚቴው ወደ ቀጣዩ የዜማ ዝግጅት ስራ እንዲሸጋገር ሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴው በሰጠው ውሳኔ መሠረት ወደ ቀጣዩ ሥራ ተሸጋግሯል፡፡"

"በመጨረሻም የክልሉ ህዝብ መዝሙር ግጥም እንዲሆን በክልሉ ስአኰ [ስራ አስፈጻሚ ኰሚቴ] የተመረጠው ግጥም"ቀጥሎ የተጠቀሰው ነው፡፡ የሕዝብ መዝሙሩ ስምንት ስንኞች ያሉት ሲኾን ከአራቱም ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የሕዝብ መዝሙሮች በስንኝ ብዛት ያንሳል፡፡

የታታሪ ሕዝቦች - የታሪክ ማኅድር፣
የአኩሪ ባህል አምባ - የድንግል አፈር፡፡

የሕዝቦችሽ ተስፋ - ለሚ ክልላችን፣

በሰላም በፍትሕ - በልማት ጉዟችን፣

ተባብረን በሥራ - እንገነባሻለን፡፡

የአማራነትን ክብር - ደማቅ አርማ ይዘን፣

ከሌሎች ሕዝቦች ጋር - እኩል ተከባብረን፣

በፍቅር በአንድነት - አብረን እንዘልቃለን፡፡

[8] በአስተባባሪ ኮሚቴው ተመርጠው ውሳኔ ከቀረቡ አራት የመዝሙር ግጥሞች መካከል አንደኛ የነበረውና ምክር ቤቱ ከማሻሻያ ሐሣቦች ጋር የመረጠው መዝሙር የሚከተለው ነው፡፡

ባህል ታሪካችን - ሃብታችን የሰፋ፣
በሥራ እናድጋለን - አለን ብሩህ ተስፋ፡፡
ሰላም እኩልነት - አንድነትን ይዞ፣
በጀግኖች ደም ፈክቷል - የድላችን ጉዞ፡፡
በአኩሪው ተጋድሏችን - ታሪክ ልንሰራ፣
ከሁሉም ህዝቦች ጋር - ቆመናል በጋራ፡፡
የአማራነትን ክብር - ደማቅ አርማ ይዘን፣
ከሌሎች ሕዝቦች ጋር - አብረን እንኖራለን፡፡

"ኮሚቴው የአጠቃላይ ዝግጅቱ 2ኛ ምዕራፍ የሆነውን ለተመረጠው የመዝሙር ግጥም ዜማ የማዘጋጀት ሥራ የጀመረው ባወጣው የዜማ ውድድር ማስታወቂያ መሠረት የዜማ ሥራዎችን በማሰባሰብ ነው፡፡ የዜማ ሥራዎቹን ካሰባሰበም በኋላ በአገራችን በአሁኑ ሰዓት ካሉት ጥቂት እውቅ የዜማና የሙዚቃ ቅንብር ባለሙያዎች በሁለቱ (አቶ ሙላቱ አስታጥቄ) ድጋፍና የውሳኔ መነሻ ሀሳብ በመታገዝ በካሴት ወይም በድምፅ ተቀርፀውና በኖታ በፅሑፍ ተዘጋጅተው ከቀረቡት ሥራዎች ውስጥ የተሻለ ያሉትን ዜማ... መርጠዋል፡፡" (የአማራ ብሔራዊ ክልል መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ 1985 - 1992፤ 15)

የመዝሙሩ ዝግጅት ኺደት 2ኛ ምዕራፍ ከተጠናቀቀ በኋላ ግጥሙንና የተመረጠውን ዜማ በአንድነት አዋሕዶ ሥራ ላይ ለመዋል የሚያበቃውን ቅርፅ እንዲይዝ ለማድረግ፣ አስፈላጊው ማስተካከያ ተደርጎለት "ደረጃውን በጠበቀ ኦርኬስትራና ስቱዲዮ ተቀርጾ የመጨረሻ መልኩን ይዞ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡" (የአማራ ብሔራዊ ክልል መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ 1985 - 1992፤ 17) መዝሙሩም "በክልሉ ውስጥ ከነሐሴ 1989 ዓ. ም. ጀምሮ በይፋ ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡" (የአማራ ብሔራዊ ክልል መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ 1985-1992፤ 18) ይሁን እንጂ፣ የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሕዝብ መዝሙር በዐዋጅ አልጸደቀም፡፡

የመጀመሪያዎቹ ኹለት ስንኞች ብሔራዊ ክልሉ ያሉትን ሀብቶች ይዘረዝራሉ፡፡ በሀብትነት የተቆጠሩትም፣ የክልሉ ሕዝቦች፣ የክልሉ ታሪክ፣ ባህልና ድንግል መሬት ናቸው፡፡ የክልሉ ሕዝቦች ለሥራ ትጋት፣ ጥረትና ተፍጨርጫሪነት እንዳላቸው ታታሪ በሚለው ቅጽል የተገለጹት በብሔራዊ ክልሉ የሚኖሩት ሕዝቦች፣ ለሥራ፣ ለዕድገት፣ ለለውጥ የሚተጉ መኾናቸውን መዝሙሩ ይገልጻል፡፡ ይኽም በራስ የመተማመን ባህል እንዲዳብር፣ ለውጥ፣ ዕድገት የሚመጣው ተግቶ በመሥራት መኾኑን ያሳውቃል፤ ይቀሰቅሳል፤ ያስተምራል፡፡

መዝሙሩ በክልሉ የተለያዩ ሕዝቦች የሚኖሩበትና የታሪክም ማኅደር መኾኑን ይገልጻል፡ ፡ ታሪክ በጊዜ ቅደም ተከተል የተፈጸመ፣ ያለፈ የሕዝብ(ቦች)ን፣ የመንግሥታትን፣ የመሪዎችን ድርጊትና ሁኔታ የሚዘረዝርና በጽሑፍ የሚገለጽን ወይም በቃል የሚነገርን ወይም በዐይን የሚታይንና በእጅ የሚዳሰስን ሥነ ቅርፅ፣ ኪነ ሕንፃ፣ ሥነ ሥዕልና ሥነ ጽሑፍ የሚገልጽ ነው፡፡ ማኅደር የሚለው ቃል ዐውዳዊ ፍቺም በብሔራዊ ክልሉ የተለያዩ ታሪኮችና የታሪክ ማስረጃዎች መኖራቸውን ያስረዳል፡፡ ታሪኮቹና የታሪክ ማስረጃዎችም በክልሉ የሚኖሩት የኹሉም ሕዝቦች መኾኑን "የታታሪ ሕዝቦች" የሚለው የመጀመሪያው ሐረግ ይነግራል፡፡ በጽሑፍ የሰፈረውና በቃል የሚነገረው ታሪክ ትውልድ እንዲኮራበት ያደርጋል፤ በዐይን የሚታየው፣ በእጅ የሚዳሰሰው ኪነ ሕንፃ፣ ሥነ ሥዕል፣ ሥነ ቅርፅ፣ ሥነ ጽሑፍ ወዘተረፈ በታሪክነቱ የትውልድ ኩራትንና በራስ የመተማመን ግንዛቤን ያዳብራል፡፡ በቱሪስት መስህብነቱ ደግሞ፣ የገቢ ምንጭ በመኾን እንደሚያገለግል እንዲታወቅ ዕድል ይፈጥራል፡፡

"የአኩሪ ባህል አምባ" በሚለው ሐረግ "አኩሪ" የሚለው ቅጽል "ባህል ዐምባ" የሚለውን ስማዊ ሐርግ ይገልጻል፡፡ በግጥሙ ውስጥ ባለው ዐውዳዊ አገልግሎት፣ ባህል[9] የሚለው ቃል የክልሉ ሕዝቦች የየራሳቸው የአኗኗር ዘዴ፣ የጋብቻ ሥርዓት፣ ወግ፣ ልማድ፣

[9]ባህል የሚለው ቃል ሰፊ ጽንሰ ሐሳብን የሚገልጽ ከመኾኑም በላይ በተለያዩ የባህል ባለ ሙያዎች ስምምነት ላይ የተደረሰበት ብያኔም አልተሰጠውም፡፡ በሀገራችንም የተለያዩ ኅብረተ ሰቦችን ባህል በማጥናት የተሰጠ ብያኔ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ስለሆነም፣ በዚኽ ጥናት ባህል የሚለውን ቃል ለመረዳት የተሞከረው በድስታ ተክለ ወልድ (፲፱፻፷፪) እና በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል (፲፱፻፺፫) መዛግብተ ቃላት የተሰጡትን ፍችዎች መነሻ በማድረግ ነው፡፡ ይኽም ኾኖ፣ ለቃሉ መፍቻ ተብለው የተደረደሩት ቃላት ተጨማሪ ፍች የሚጠይቁ ናቸው፡፡

ትውፊት፣ ደንብ፣ ፎክሎር ወዘተረፈ አላቸው ማለትን ይገልጻል፡፡ ዐምባ የሚለው አንድም በአንድ አካባቢ መሰባሰብን ይገልጻል፡፡ በእነዚኽ ፍችዎች መሠረትም፣ "ባህል ዐምባ" የሚለው ስማዊ ሐረግ የተለያዩ ባህሎች የሚገኙበት ክፍለ ሀገር (ክልል) ማለት ነው፡፡ ክፍለ ሀገሩም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነው፡፡ የባህል ሀብት ያለው ሕዝብ በማንነቱ ይኰራል፤ የባህል ሀብቱም የቱሪስት መስህብ በመኾን የገቢ ምንጭ ያስገኛል፡፡ በማንነቱ የሚኰራና መኩራት የሚችል ማንነት ያለው ሕዝብ እንዳለ ይገልጻል፡፡ የክልሉ "ሕዝቦች" አኩሪ የባህል ባለቤቶች መኾናቸውን በሕዝብ መዝሙሩ መግለጽም ሥነ ልቦናዊ ጠቀሜታ አለው፡፡

በመዝሙሩ በብሔራዊ ክልሉ ሀብትነት የተቆጠረው "ድንግል አፈር" የሚለው ገና ያልተበላና ያልተሟጠጠ ለግብርና ሥራ፣ ለከብት እርባታና ለማዕድን ቁፋሮ የሚያገለግል መሬት ባለቤለትነትን ይገልጻል፡፡ እንዲሁም፣ ድንግል መሬት በደን የተሸፈነ በመኾኑ፣ ለዱር እንስሳትና ለአእዋፋት መጠለያ ይኾናል፡፡ የማየነጥፍ ውሃ መኖሩንም ያመከታል፡፡ የድንግል መሬት ባለቤት መኾንም የኢኰኖሚ ዕድገት ለማምጣት የሚያስችል ሀብት መኖርን ያስረዳል፡፡ የሀገር ሀብት መኖርን መረዳትና ማመንም በራስ መተማመንን ያጎለብታል፡፡ የኑሮ ተስፋም ይፈጥራል፡፡ ይኽ እምነት መኖሩንም "የሕዝቦችሽ ተስፋ - ለሟ ክልላችን" የሚለው ስንኝ ያስረዳል፡፡ የክልሉ ሕዝቦች ተስፋ እንዲመሠረት የተደረገውም በክልሉ ለምነትና በውስጧ ባሉ ሰው ሠራሽና ገና ባልተበሉ የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ነው፡፡

በሕዝብ መዝሙሩ የብሔራዊ ክልሉ ሕዝቦች ተስፋ እንዲመሠረት የተደረገው አንድም፣ ሰላም በሰፈነበት፣ ፍትሕ በነገሠበት ኹኔታ የልማት ሥራ በማከናወን ላይ ነው፡፡ ይኽም፣ ሰላምም ፍትሕም በመዳበር ኺደት ላይ መኾናቸውንና የልማት ጉዞውም ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ዕድገት የሚደረግ የለውጥ እንቅስቃሴ ነው፡፡ አንድም፣ የብሔራዊ ክልሉ ሕዝቦች የወደፊት ተስፋ የተመሠረተው ሕዝቦቿ ተባብረው፣ አንድ ኾነው ብሔራዊ ክልላቸው እንዲበለፅግና እንዲለማ በማድረግ ነው፡፡ በብሔራዊ ክልሉ የሚመጣው ለውጥ፣ ዕድገት፣ ብልጽግናና ልማት ዋነኛ ጥቅም ለክልሉ ሕዝቦች ነው፡፡ የብሔራዊ ክልሉ ሕዝቦች በሌሎች ብሔራዊ ክልሎች ከሚኖሩ ሕዝቦች ጋር በእኩልነት መተባበር፣ በፍቅር ላይ የተመሠረተ አንድነት ኖሯቸው አብረው እንደሚኖሩ የክልሉ መዝሙር ይገልጻል፡፡

ሕዝቦች የሚለው ብዙ ቁጥር አመልካች ቃል በቋንቋ፣ በባህል፣ በመልካ ምድራዊ አሠፋፈር፣ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የተለያዩ ሕዝቦችን ይገልጻል፡፡ በብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ እኛ የአማራ ክልል ሕዝቦች ማለቱም በአንቀጽ 5 (1) "በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ቋንቋዎች በመንግሥት ዘንድ እኩል እውቅና ይኖራቸዋል፡፡" በማለት የተደነገገው በክልሉ ውስጥ ለሚኖሩ ከዐማርኛ ውጭ የኾኑ ቋንቋዎችን ለሚናገሩ ብሔረሰቦች የተሰጠውን እውቅና ያስረዳል፡፡ የብሔራዊ ክልሉ የበላይ ሥልጣን ባለቤቶች የየራሳቸው ቋንቋ ያላቸው ብሔረሰቦች መኾናቸው በብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 "የአማራ ክልል ሕዝቦች የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ የበላይ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸው፡፡" በማለት ተደንግጓል፡፡ ሕገ መንግሥቱ ይኽን ሥልጣን የሰጣቸው ሕዝቦችም የራሳቸው የዞን አስተዳደር የተሰጣቸውን የዋግ ኅምራ፣ የአዊና የከምሴ ኦሮሞ ዞኖች አስተዳደሮችን እንዲሁም፣ በተለያየ የዞን አስተዳደር የተከፈለውን የአማራ ሕዝብ ነው፡፡ እነዚኽ ሕዝቦችም የራሳቸው ቋንቋ፣ የራሳቸው ባህል፣ የራሳቸው የመኖሪያ አካባቢ ወይም አሰፋፈር የራሳቸው ማንነት፣ የራሳቸው ታሪክ (?) የአላቸው

ናቸው፡፡ ስለኾነም፣ የብሔራዊ ክልሉ መዝሙር በክልሉ ለሚኖሩ ሕዝቦች ኹሉ ዕውቅና ይሰጣል፡፡ ነገር ግን፣ በሕገ መንግሥት ዕውቅና ከተሰጣቸውና የራሳቸው የዞን አስተዳደር ካላቸው ብሔረሰቦች ሌላ በብሔራዊ ክልሉ ሌሎች ሕዝቦችም ይኖራሉ፡፡ በብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት በስም ያልተጠራው የአርጎባ ሕዝብ የልዩ ወረዳ አስተዳደር ተሰጥቶታል፡፡ በቅርቡም ለቅማንት ሕዝብ የራስ አስተዳደር ዕውቅና ተሰቷል፡፡ ነገር ግን፣ በሕዝብ መዝሙሩ ስድስተኛ መስመር የተገለጸው ሐሳብ በክልሉ ከአማራ ውጭ ያሉ ሕዝቦችን መኖር የማይገልጽ ወይም ቢኖሩም የራሳቸውን ማንነት እንዲተው የሚቀሰቅስ ነው፡፡ ስንኙ "የአማራነትን ክብር - ደማቅ አርማ ይዘን፣" የሚለው ስንኝ በክልሉ የሚኖሩ ኹሉም ሕዝቦች የአማራን ክብርና አርማ በመያዝ በሌሎች ክልሎች ከሚኖሩ ሕዝቦች ጋር ትብብርና አንድነት መፍጠር እንደሚገባቸው ይቀሰቅሳል፡ ፡ በብሔራዊ ክልሉ የሚኖሩ ሕዝቦች የራሳቸውን ማንነት በመተው የአማራነትን ልእልና፣ ገናናነት፣ ታዋቂነት እንዲያስቀድሙ ወይም እንዲይዙ ይጠይቃል፡፡ ከብሔራዊ ክልሉ ውጭ ከሚኖሩ የተለያዩ ሕዝቦች ጋር የሚያደርጉት የትብብር ግንኙነት፣ የሚመሠርቱት አንድነት የአማራነትን ክብር ይዘው፣ የአማራነትን ክብር መለያቸው፣ መታወቂያቸው፣ ደማቅ አርማቸው አድርገው መኾኑን የክልሉ መዝሙር ይገልጻል፡፡ በዚኽም፣ መዝሙሩ በአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግሥት ዕውቅና የተሰጣቸውንና በስም ያልተጠሩትን ሕዝቦች ማንነት ትቷል ወይም ዘንግቷል፡፡

በብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት የብሔራዊ ክልሉ መዝሙር የክልሉ ሕዝቦች የጀግንነት ታሪክ እንዲያንጸባርቅ አልተደነገገም፡፡ የክልሉ ሕዝቦች በረጅም ዘመን ታሪካቸው ሀገራቸውን ከወራሪ ጠላት ተከላክለውና ጠብቀው ያቆዩ መኾናቸው በክልሉ መዝሙር መንፀባረቁ፣ ወጣቱ ትውልድ የአባቶቹን የጀግንነት ታሪክ እንዲያደንቅ ለማድረግ የሚያስችል ስሜት ለመፍጠር ያስችላል፡፡ እናም በክልሉ መዝሙር የክልሉ ሕዝቦች ታሪክ እንዲንጸባረቅ አለመደንገጉ ሕገ መንግሥታዊ ክፍተት ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ በክልሉ መዝሙር የመጀመሪያ ስንኝ "የታታሪ ሕዝቦች - የታሪክ ማኅድር" በማለት የተገለጸው የክልሉ ሕዝቦቹ የታሪክ ባለሀብቶች መኾናቸውን ይገልጻል፡፡ የታሪክ ማኅድርነታቸው በቀጥታ ጀግንነታቸውን አይገልጽም፡፡ ታሪክ ሚለው ቃል የሚገልጸው በክልሉ የሚገኙትን የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣ የጎንደር አብያተ መንግሥታትና አብያተ ክርስቲያናት መኾኑን የክልሉን አርማ ለመወሰን የወጣው መመሪያ ያስረዳል፡፡

የዐማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት መዝሙሩ ስለ ታሪክ ወይም ስለዐማራ ሕዝብ የጀግንነት ታሪክ እንዲንጸባረቅ አልደነገገም፡፡ በብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት ስለ ክልሉ ሕዝብ መዝሙር በሚደነግገውና፣ በሕዝብ መዝሙሩም በብሔራዊ ክልሉ ስለሚኖሩ ብሔረሰቦችም ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ፣ በሕዝብ ዝሙሩ ስለ ዐማራ ሕዝብና በክልሉ ስለ ሚኖሩ ብሔረሰቦች የተገለጸው ተቃርኖ ይስተዋልበታል፡፡ በአንድ በኩል በብሔራዊ ክልሉ ዐማራ፣ ዋግ-ኅምራ፣ አዊ፣ ኦሮሞና አርጎባ እንደሚኖሩ ይገልጻል፡፡ በሌላ በኩል፣ "የክልሉ ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ ለመኖር" ግን "የአማራነትን ክብር - ደማቅ አርማ ይዘን" በማለት በክልሉ የሚኖሩ ሕዝቦችን ይዘነጋል፡፡ ከዚኽም በላይ "የዐማራነት ክብር - ደማቅ አርማ ይዘን" የሚለው ይዘን" የሚለው ከብሔራዊ ክልሉ ውጭ በሌሎች አካባቢዎች ወይም ክልሎች ስለሚኖረው የዐማራ ሕዝብ ትኩረት አይሰጥም፡፡

### ፫. ፫) የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል መንግሥት መዝሙር (Walaloo faarichaa)

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሕገ መንግሥቱ በአንጽ ፬፣ "የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የኦሮሞ ሕዝብ የረዥም ዘመን የጀግንነትና የፍትሕ ታሪክ እንዲሁም የተገኘውን ድል የሚያሳይና ለተሻለ ኑሮ ያለውን ምኞት የሚያንፀባርቅ የራሱ መዝሙር ይኖረዋል፤ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡" በማለት ይደነግጋል (የኦሮሚያ[ን] ክልላዊ መንግሥት አርማና መዝሙር ለመወሰን የወጣ ዐዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፰ አንቀጽ ፮)፡፡

የኦሮሚያ ሕዝብ መዝሙር ከዐማርኛ ትርጉሙ ጋር

Walaloo Faaruu Naanichaa akka armaangadii taha: የክልሉ መዝሙር ግጥም ከዚህ በታች እንደሰፈረው ይሆናል፡-

| | |
|---|---|
| Oromiyaa, Oromiyaa haadha seenaa | ኦሮሚያ ኦሮሚያ የትልቅ ታሪክ እናት/ባለቤት፤ |
| Handhuura Oromotaa galma sirna Gadaa | የገዳ ሥርዓት ማዕከል የኦሮሞዎች እምብርት፤ |
| Dachee heeraa seeraa haadha Caffee Odaa | የፍትሕ፣ የሕግ ምድር፣ የኦዳ ምክር ቤት የኦዳ[10] እናት፤ |
| Badhaatuu gabbattuu magarsituu hundaa | የታደልሽ፤ ለምለም፤ ሁሉን አብቃይ ምድር፡፡ |
| Xurii bara dhibbaa dhiigaan sirraa dhiqnee | የመቶ ዓመት እድፍሽን በደማችን አጠብንልሽ፤ |
| Wareegama qaaliin Alaabaa tee ol qabnee | በሕይወት መስዋዕትነት ባንዲራሽን ከፍ አደረግንልሽ፤ |
| Gammannee gammadi Bikkuu deebifannee | ቦኩውን[11] መለስነው፤ ደስ ይበልሽ ደስ ይበልሽ፡፡ |
| [Bokkuu] | |
| Nagaafi demokraasii tabaroo namummaa | ሰላምና ዲሞክራሲ ሰብአዊ ሙብት፤ |
| Misooma amansiisaa guddina hatattamaa | አስተማማኝ ልማት፣ ፈጣን ዕድገት፤ |
| Ummatootaa wajjin jaalalaafi tokkummaa | ከሕዝቦች ጋር ፍቅርና አንድነት፤ |

[10]ኦዳ የኦሮሞ አባ ገዳዎችና የሸንጎ አባሎቻቸው (ሽማግሌዎች) በልዩ ልዩ ማኅበራዊ ችግሮች ላይ ለመምከርለመፍታት የሚሰበሰቡበት ጥላ ያለው ትልቅ ዛፍ፡፡

[11]ቦኩ፡- በእጅ የሚያዝ በትረ ሥልጣን፡፡

| | |
|---|---|
| Wabii jireenyaatiif goone kaayoo cimaa | የኑሮአችን ዋስትና አድርገናል ጽኑ ዓላማ፡፡ |
| Irree gamteeffannee kaanee nu abdadhu | ክንዳችን አስተባብረን ተነስተናል ተማመኚብን፤ |
| Oromiyaa lalisi dagaagii jiraadhhu. | ኦሮሚያ ለምልሚ ዕደጊ ኑሪልን፡፡ |

ይኸ መዝሙር የሚያንጸባርቀው በብሐራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፬ የተደነገጉትን አራት ይዘቶች ነው፡፡ ይዘቶቹም፣ የኦሮሞን ሕዝብ የረዥም ዘመን የጀግንነትና የፍትሕ ታሪክ፣ የኦሮሞ ሕዝብ በትግሉ ያገኘውን ድልና ለተሻለ ኑሮ ያለውን ምኞት ማንፀባረቅ የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚኽ ይዘቶች እያንዳንዳቸው በብሔራዊ ክልሉ መዝሙር በየትኞቹ ስንኞች እንደተንፀባረቁ እንመለከታለን፡፡ የተንፀባረቁትን ይዘቶቹ የምንመለከተው በብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት በተገለጹበት ቅደም ተከተል ይኾናል፡፡ በመጀመሪያ "የኦሮሞ ሕዝብ የረጅም ዘመን የጀግንነት ታሪክ" የሚለው ይዘት በመዝሙሩ የተንፀባረቀው በትርጉሙ በአራተኛው፣ በዐምሥተኛውና በስድስተኛው ስንኞች ነው፡፡ "የመቶ ዓመት እድፍ (ጉድፍ)፤ በደም አጠብንልሽ" በሚለው ስንኝ ለመቶ ዓመታት በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ተጭኖ የነበረን የጭቆና ቀንበር ልጆቿ እንደ ተቤዡ ይገልጻል፡፡ የኦሮሞ ልጆች ደማቸውን አፍስሰውና ራሳቸውን ሰውተው (ቤዛ አድርገው) ሕዝቡን መታደጋቸው የጀግንነት ታሪካቸው ማስረጃ ነው፡፡ በሕገ መንግሥቱ "የኦሮሞን ሕዝብ የረዥም ዘመን የጀግንነት ታሪክ" በማለት የተደነገገው በብሔራዊ ክልሉ መዝሙር በመቶ ዓመት የተገደበ የጀግንነት ታሪክ ነው፡፡ መዝሙሩ የኦሮሞን ሕዝብ የጀግንነት ታሪክ በመቶ ዓመት[12] መገደቡ ከዚያ በፊት ምን እንደ ነበር እንድንጠይቅ ያደርጋል፡፡

"በመስዋዕትነት ሰንደቅሽን ከፍ አድርገን" በሚለው ስንኝ የተገለጸው ይዘትም ከኦሮሞ ሕዝብ የጀግንነት ታሪክ ጋር ቀጥታ ግንኙነት አለው፡፡ መስዋእትነት ለሕይወት ሳይሳሱ ለአገር፣ ለወገን፣ ለነፃነት፣ ለዓላማና ለእምነት ራስን አሳልፎ መስጠትን ይገልጻል፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ መስዋእትነት የከፈለው የነፃነቱ መገለጫ የኾነውን ትእምርት ከፍ አድርጎ ለማውለብለብ ነው፡፡ ሰንደቅ የባንዲራ መስቀያ ዘንግ ቢሆንም በመዝሙሩ ባለው ዐውዳዊ አጠቃቀም ሰንደቁንና ሰንደቅ ዓላማውን ይቀላቅላል፡፡ ሰንደቅ ዓላማው ሳይኖር ዘንጉ የነጻነት መለያ ምልክት ሊኾን አይችልምና፡፡ ቦኩ በኦሮሞ ኅብረተ ሰብ ዘንድ የሥልጣን ርክክብ ሲደረግ የሥልጣን ጊዜውን የጨረሰው አዲስ ለተመረጠው አባ ገዳ የሚሰጠው በትረ መንግሥት ነው፡፡ ይኽንን ባህላዊ የፍትሕ ሥርዓት የኦሮሞ ሕዝብ ለመቶ ዓመታት እንዳይገለገልበት ተደርጎ የነበረውን መስዋዕትነት በመክፈል እንዲመለስ ተደርጓል ማለት ነው፡፡ ለዚኽም የጀግንነት ተግባር ፈጽመዋል ማለት ይቻላል፡፡ በመዝሙሩ ኦሮሚያ ተገድዳ እንድትተው የተደረገችውን ቦኩን በማስመለሷ "ተፈሥሒ" ተብላለች፣ በኃይላቸውና በትግላቸው መስዋእትነት ከፍለው በማስመለሳቸው ነው፡፡

የኦሮሞ ሕዝብ የረዥም ጊዜ የፍትሕ ታሪክ ያለው መሆኑ በብሔራዊ ክልሉ መዝሙሩ ተንጸባርቋል፡፡ የመዝሙሩ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ስንኞች ኦሮሚያ ፍትሕ የሚበየንባት ምድር መሆኗ ተገልጿል፡፡ ኦዳ ፍትሕ ይሰጣሉ፣ ያለ አድሎ ይፈርዳሉ፤ በእኩልነት ሕዝቡን ያስተዳድራሉ የሚባሉት አባ ገዳና ሸንጎአቸው የሚሰበሰቡበት ዛፍ ነው፡፡ በኦሮሚያ ፍትሕ የሚሰጡ

[12] "የኦሮሚያ ጉድፍ የመቶ ዓመት ዕድሜ" የተባለው ዐፄ ምኒልክ ወደ አካባቢው በመዝመት ያስገበሩበትን ጊዜ መነሻ ያደረገ ይመስላል፡፡

ሸማግሌዎች የሚሰበሰቡት፣ አባ ገዳውና ሸንጓቸው የሚያስችሉበት፣ ስለ አካባቢ ስለ ሀገር ጉዳይ የሚመከረው ትልቅ ዛፍ ጥላ ሥር በመሰብሰብ ነው፡፡ ዛፉ በኦሮምኛ ኦዳ ሲባል፣ በራሱም የፍትሕ የሥርዓት ትእምርት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ የኦሮሚያ ሸማግሌዎች ፍትሕ ለመስጠት፣ ስለ ሀገር ጉዳይ ጉባኤ የሚቀመጡበት ትልቁ ዛፍ- ኦዳ የፍትሕ መሳሪያ ተደርጎ በመዝሙሩ ተገልጿል፡፡

እስከ አኹን እንደተገለጸው የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መዝሙር የኦሮሞ ሕዝብ በትግሉ ያገኘውን ድል ይገልጻል፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ በትግሉ ላዩ ላይ የተጫነውን ጭቆና (እድፍ የሚገልጸው ይኽንኑ ነው) አስወግዷል፡፡ በዛፍ ጥላ ሥር የሚከናወነውን የፍትሕ ሥርዓትና የሥርዓቱ መገለጫ የሆነውን ኦዳ በትግሉ አስመልሷል፡፡ የነፃነት ምልክቱ የሆነውን ሰንደቅ ዓላማውን ከፍ አድረጎ ለማውለብለብ የቻለው ታግሎና ድል አድርጎ ነው፡፡ እንደዚሁም፣ የተነጠቀውን በትረ- መንግሥቱን ያስመለሰው ታግሎ በማሸነፍ ነው፡፡

የኦሮሞ ሕዝብ ለተሻለ ኑሮ ያለውን ምኞት መዝሙሩ ያንፀባርቃል፡፡ ኦሮሚያ ለምለምና ሁሉንም ዓይነት ሰብል የምታበቅል መሆኗ፣ እድገትን በተፋጠነ መንገድ ለማምጣት ታስችላለች ብሎ እንዲያስብ ያደርጋል፡፡ ሕዝቡ ክንዱን አስተባብሮ ለልማት መነሣቱ፣ ዕድገትን ለማምጣት ያስችላል የሚል ተስፋ ይፈጥራል፡፡ ከዚኽም በላይ፣ ሰላም የሰፈነበት፣ ዲሞክራሲ የነገሠበትና ሰብአዊ መብት የተከበረባት ሀገር መመሥረትን የሕይወት ዋስትና ማድረግ የኦሮሚያ ሕዝብ የወደፊት ሕይወት የተሻለ ያደርገዋል ብሎ የኦሮሞ ሕዝብ ማመኑን መዝሙሩ ያንፀባርቃል፡፡ እነዚኽን ተግባሮች ዋስትና በማድረግም ከክልሉ ውጭ ከሚኖሩ ሕዝቦች ጋር ፍቅርና አንድነትን በመመሥረት ለመኖር መወሰን የሕዝቡን የወደፊት ተስፋ ይገልጻል፡፡

በዚኽ ድንጋጌ መሠረትም የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥትን አርማና መዝሙር ለመወሰን በወጣው ዐዋጅ ቁጥር ፬/፲፱[፻]፹፯ አንቀጽ ፭ የመዝሙሩ አጠቃላይ ይዘት ተደነገገ፡፡ የብሔራዊ ክልሉ መዝሙር በይዘቱም "፩. የኦሮሞን ሕዝብ የረጅም ዘመን የጀግንነት ታሪክ፣ ፪. ክሕዝቡ ጋር የቆየውን የሕግና የፍትሕ ታሪክ፣ ፫. የተካሄደውን የጀግንነትና የመስዋዕትነት ትግልና የተገኘውን ድል፣ ፬. ሕዝቡ ለተሻለ ኑሮ ያለውን ምኞት፡፡" የሚሉትን አራት ጉዳዮች እንደሚያንፀባርቅ ተደንግጓል፡፡ የክልሉ መዝሙር በይዘቱ እንዲያንፀባርቅ በሕገ መንግሥቱ የተደነገገው የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥትን አርማና መዝሙር ለመወሰን በወጣው ዐዋጅ ላይ በተመሳሳይ ተደንግጓል፡፡ 13 ስንኞች ያሉት የመዝሙሩ ግጥም ዐዋጅ ቁጥር ፬/፲፱[፻]፹፯ አንቀጽ ፮ ተደንግጓል (መዝሙሩን በመጥቀስ ይዘቱን ወደ ፊት እንመከታለን)፡፡ ማንኛውም ሰው ወይም አካል የክልሉን አርማና መዝሙር የማክበር ግዴታ እንዳለበት በአንቀጽ ፯፣ ዐዋጁ ከህዳር ፱ ቀን ፲፱[፻]፹፯ ጀምሮ የፀና መኾኑ ተደንግጓል፡፡ የጀግንነቱም ታሪክ ከኦሮሞ ሕዝብ ውጭ ከሆነ ሌላ ኃይል ጋር የተደረገ ትግልን ይገልጻል፡፡ "ረዥም" የሚለው ቅጽል የሚገልጸውን የዘመን ርዝመት በትክክል ለመረዳት የሚያስችል ማስረጃ ከሕገ መንግሥቱ ወይም ሕገ መንግሥቱን ያጸደቀው የፖለቲካ ድርጅት ከሚቀበለው ታሪክ ማስረጃ መጥቀስ አስፈላጊ ነው፡፡ ኹለተኛ፣ መዝሙሩ የኦሮሚያ ሕዝብ በጀግንነቱ አንድን በስም ያልተገለጸ የውጭ ኃይል በማሸነፍ ያገኘውን ድል ማሳየት አለበት፡፡ ይኽንን ሐሳብ በግልጽ ለመረዳት የኦሮሞ ሕዝብ በረዥም የጀግንነት ታሪኩ ማንን አሸነፈ? መቼ አሸነፈ? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ድሉ፣ የኦሮሞ ሕዝብ በአንድ የፖለቲካ ድርጅት የበላይነት(?) በመመራት ራሱን በራሱ ማስተዳደር(?)፣ በራሱ ቋንቋ

መማር፣ የፍትሕ ሥራ ማካኼድ ከጀመረበት ከ1983 ዓ.ም. ይጀምራል ከተባለ ድል አድራጊውም ተሸናፊውም ይታወቃሉ፡፡ ድል አድራጊው ኦሕዴድ (ከኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች ጋር)፣ ተሸናፊው ደግሞ "የኅበረተ ሰባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ኢትዮጵያ መንግሥት" (ደርግ) ሲኾን፣ የድሉ ጊዜም ግንቦት 1983 ዓ. ም. ነው፡፡ እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ የኦሮሞ ሕዝብ የጀግንነት ታሪክ ረዥም ነው እየተባለ በ1982 ዓ .ም. ከተመሠረተው የኦሕዴድ የትግል ታሪክ ጋር እንዴት ይጣጣማል(?) ለዚህ መልስ ኦሕዴድ የትግሉን ዱላ ተቀብሎ ለድል አበቃው የሚል መልስ መስጠት ይቻላል፡፡ ነገር ግን፣ የትግሉን ዱላ ባቀበለውና በተቀበለው መካከል ያለው ግንኙነት የጋራ ድልን በማጣጣም ላይ የተመሠረተ ነው ወይ (?) የሚለው ጥያቄ ትግል መነሻ በራሱ የፍትሕ እንዲሁም የጀግንነት ተግባር በመፈጸም የተገኘውን ድል ማሳየት አለበት፡፡ የብሔራዊ ክልሉ መዝሙር የሚያሳየው ሦስተኛ ጉዳይ የኦሮሞን ሕዝብ ረዥም የፍትሕ ታሪክ ነው፡፡ ይኽ የፍትሕ ታሪክ የኦሮሞ ሕዝብ እርስ በእርሱ ባለው ግንኙነት አድሎ የሌለበት፣ ባሕላዊ የሕግ የባላይነት የነገሠበት፣ በኅብረተ ሰቡ ውስጥ የሚፈጠር ችግር በመልካም ሁኔታ የሚፈታበት ከኅብረተ ሰቡ የፈለቀና ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣ ሕግ መኖሩን ይገልጻል፡፡ አራተኛ፣ መዝሙሩ የኦሮሞ ሕዝብ ለተሻለ ኑሮ ያለውን ምኞት የሚያንጸባርቅ መሆን እንዳለበት ሕገ መንግሥቱ ይደነግጋል፡፡ ይኽም ጠላቱን በጀግንነቱ ድል ያደረገና ረዥም የፍትሕ ታሪክ ያለው ሕዝብ ከሚገኝበት የኑሮ ደረጃ ወደ ተሻለው ለመሸጋገር ፍላጎት፣ ጉጉትና ክጀላ ያለው መሆኑን ይገልጻል፡፡ ይኽ ምኞት የኦሮሞ ሕዝብ በምን ዓይነት የኑሮ ደረጃ ላይ ይገኛል? የተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ ለመድረስ ከምኞት በዘለለ ምን ምን ሥራዎች፣ በምን ገንዘብ፣ በእንዴት ያለ ባለሙያ መሠራት አለባቸው? በምን ጊዜ? መቼና እንዴት? የሚሉትን ጥያቄዎች እንዲነሡ የሚጋብዝ ነው፡፡

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሕዝብ መዝሙሩን በዐዋጅ መደንገጉ፣ ከሌሎች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የሕዝብ መዝሙሮች የሕግ ማቀፍ አሰጣጥ የተለየ ያደርገዋል፡፡ ሌሎቹ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የየክልላቸውን የሕዝብ መዝሙር እንዲዘመር ያደረጉት በመመሪያ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ የዐማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ይኽንኑ አድርጓል፡፡ በዐዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፫ የኦሮሚያን ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አርማና መዝሙር ተወሰነ፡፡ የክልሉን አርማና መዝሙር በዐዋጅ መወሰን ያስፈለገበት ምክንያት በዐዋጁ መቅድም(?) እንደተደነገገው "የሕዝቡን ታሪክ፣ ባህል፣ አንድነት፣ እኩልነትና ፍላጎት በሚገልጽ መልክ አርማውንና መዝሙሩን መቅረጽ በማስፈለጉ" ነው፡፡ ዐዋጁ በአንቀጽ ፬ የአርማውን ትርጓሜ፣ እንደዚሁም በአንቀጽ ፫ የብሔራዊ ክልሉን የሕዝብ መዝሙር አጠቃላይ ይዘት ይደነግጋል፡፡ በዚኹ በዐምስተኛው አንቀጽ የብሔራዊ ክልሉ የሕዝብ መዝሙር እንዲያንጸባርቃቸው የተደነገጉት ይዘቶች በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፬ ከተደነገጉት ይዘቶች ጋር ሲነጻጸሩ መጠነኛ ልዩነት ይታይባቸዋል፡፡ ለምሳሌ፣ የብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት የሕዝብ መዝሙሩ የኦሮሞን ሕዝብ የፍትሕ ታሪክ እንዲያንጸባርቅ በሚል ሲደነግግ፣ የብሔራዊ ክልሉን አርማና መዝሙር ለመወሰን በወጣው ዐዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፫ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ ፪ "ከሕዝቡ ጋር የቆየውን የሕግና የፍትሕ ታሪክ ማንጸባረቅ" በማለት ይደነግጋል፡፡ የብሔራዊ ክልሉን አርማና መዝሙር ለመወሰን በወጣው ዐዋጅ "የሕግ" የሚል ቃል ታክሎ ተደንግጓል፡፡ እንደዚሁም ሕገ መንግሥቱ "የኦሮሞ ሕዝብ ያገኘውን ድል ማንጸባረቅ" እንዳለበት ሲደነግግ፣ ዐዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፫ አንቀጽ ፫ ንዑስ

አንቀጽ ፫ "የተካሄደውን የጀግንነትና የመስዋዕትነት ትግልና የተገኘውን ድል" ማንጸባረቅ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ድልን በሚመለከት በሕገ መንግሥቱና በዐዋጁ ላይ የተገለጹት ይዘቶች ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ድልን ለማግኘት መስዋዕትነት መክፈልና የጀግንነት ተግባር መፈጸም በብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥትና የክልሉን አርማና መዝሙር ለመወሰን በወጣው ዐዋጅ ላይም ተገልጿል፡፡ በሕገ መንግሥቱ የኦሮሞ ሕዝብ ባገኘው ድል ላይ ሲያተኩር፣ የኦሮሚያን ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አርማና መዝሙር ለመወሰን በወጣው ዐዋጅ ግን ድሉን ለማግኘት የተከፈለውን መስዋዕትነትና የተፈጸመውን የጀግንነት ተግባር ይገልጻል፡፡ ድል ውጤት ሲኾን መስዋዕትነት መክፈልና የጀግንነት ተግባር መፈጸም ለድል የሚያበቁ ተግባሮች ናቸው፡፡ ይኽም ኾኖ "የተካሄደውን የጀግንነትና የመስዋዕትነት ትግልና የተገኘውን ድል" የሚለው ዐረፍተ ነገር በጀግንነት የተካኼደውን ትግል፣ የተከፈለውን መስዋዕትነትና የተገኘውን ድል ተብሎ ቢገለጽ የተሻለ ነበር፡፡

በዐዋጅ ቁጥር ፴/፲፱፻፹፰ አንቀጽ ፮ ላይ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሕዝብ መዝሙር ግጥም በላቲን ፊደል ተጽፎ ይነበባል፡፡ ይኸው የሕዝብ መዝሙር ዐሥራ ሦስት ስንኞች አሉት፡፡ የሕዝብ መዝሙሩ የዐማርኛ ወይም የእንግሊዝኛ ትርጉም በዐዋጁ ላይ ስለአልተሰጠ ይዘቱን ለመረዳት የዐማርኛ ትርጉም እንዲሰጠው ማድረግ ግድ ይላል፡፡ ማንኛውም ሰው ወይም አካል የሕዝብ መዝሙሩን የማክበር ግዴታ ያለበት መኾኑ በዐዋጅ ቁጥር ፴/፲፱፻፹፰ አንቀጽ ፯ ላይ ተደንግጓል፡፡ የሕዝብ መዝሙሩን አጠቃቀም በተመለከተ ደንብ የማውጣት ሥልጣን የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥራ አስፈጻሚ መኾኑ በዚኹ ዐዋጅ አንቀጽ ፰ ላይ ተደንግጓል፡፡ ኾኖም፣ እስከ ዛሬ ድረስ የክልሉን የሕዝብ መዝሙር አጠቃቀም የሚወስን ደንብ አልወጣም፡፡ በዚህም ምክንያት የክልሉ የሕዝብ መዝሙር በክልሉ በሚገኙ ትምህርት ቤቶችም ኾነ በሌሎች አጋጣሚዎች ላይ እንዴት እንደሚዘመር በዐዋጅ አልተደነገገም፤ ደንብም አልወጣም፤ አገልግሎት ግን ይሰጣል፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ብሔራዊ መዝሙርና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሕዝብ መዝሙር በትምህርት ቤቶች የሚዘመሩት ኹለቱ መዝሙሮች ስለአጠቃቀማቸው የወጣ ደንብ ሳይኖር ነው፡፡ ብሔራዊ መዝሙሩና የክልሉ የሕዝብ መዝሙሮች ስለአጠቃቀማቸው የወጣ ደንብ ባይኖርም በየትምህርት ቤቶቹ ይዘመራሉ፡፡ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ወደ ክፍል ከመግባታቸው በፊት በመጀመሪያ የኢትዮጵያን ብሔራዊ የሕዝብ መዝሙር ቀጥሎ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሕዝብ መዝሙር በካሴት እንዲዘመሩ ይደረጋል፡፡

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ ሕገ መንግሥት የክልሉ የሕዝብ መዝሙር የኦሮሞን ሕዝብ ረጅም የጀግንነትና የፍትሕ ታሪክ እንዲያንጸባርቅ ይደነግጋል፡፡ እነዚኽን የታሪክ ገጽታዎች በኹለት ክፍሎ መመልከት ይቻላል፡፡ በመጀመሪያ የኦሮሞን ሕዝብ ረጅም የጀግንነት ታሪክ ምንነት ለመረዳት በብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ የተገለጸውን እንመለከታን፡፡

በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት መግቢያ የኦሮሞ ሕዝብ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቹን ያጣበትን፣ በተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ዕድገቱ የተገታበትን ሥርዓት ከሌሎች ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጋር በመኾን አሸናፊ የኾነበት የታሪክ ምዕራፍ ተገልጹዋል፡፡ ይኽ የታሪክ ምዕራፍ የዐፄ ምኒልክ ጦር (የኦሮሞ ሕዝብ ወደሚኖርበት

ከዘመተበት) ከ፲፱ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ይጀምራል፡፡ በዚኽ ስሌት መሠረት የኦሮሞ ሕዝብ የረጅም ዘመን ታሪክ ከመቶ ዓመት አይበልጥም ማለት ነው፡፡ እንደ ሕገ መንግሥቱ አገላለጽ ከሆነ የኦሮሞ ሕዝብ የጀግንነት ታሪክም በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ተጀምሮ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር ሥልጣን እስከ ያዘበት ፲፱፻፹፫ ዓመተ ምሕረት ይዘልቃል፡፡ በዚኽ ጊዜ ለኦሮሞ ሕዝብ የተከፈለው መሥዋዕትነትና የተሠራው ጀብዱ የኦሮሞን ሕዝብ ረጅም የጀግንነት ታሪክ ይገልጻል ተብሎ መታመኑን በሕገ መንግሥቱ ከተደነገገው መረዳት ይቻላል፡፡ የጀግንነት ታሪክ የተሠራው በሀገር ውስጥ የነበረውን የተዛባ ሥርዓት ለመለወጥ በተደረገ ትግል ነው፡፡

ይኽ የታሪክ ግንዛቤ ቢያንስ ኹለት ሕጸጾች አሉበት፡፡ አንደኛው፣ ዛሬ የኦሮሞ ሕዝብ በሚገኝበት ቦታ ተስፋፍቶ የሚገኘው ከ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በተለያዩ ጊዚያት የተለያዩ ብሔሮችንና ብሔረሰቦችን በጦርነት በማሸነፍ እንደነበር አልተገለጸም፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ ከደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ እስከ ሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የተስፋፋው፣ ወደ ደቡብ፣ ወደ ምዕራብ፣ ወደ መሃልና ወደ ሰሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያ የዘለቀው ጦርነት ሳያደርግ፣ የሰላም ቄጤማ እየረገጠ አልነበረም፡፡ በተስፋፋባቸው ቦታዎች ላይ ከነበሩት ሕዝቦች ጋር ተዋግቶ በማሸነፍ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በመሸነፍ፣ እንደገናም በማሸነፍ ነበር፡፡ ይኽ ታሪክ አሉታዊ ገጽታው የበዛ ቢኾንም ስለኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ ሲነገር ተደምሮ መቅረብ ይገባዋል፡፡ በዚኽ የታሪክ ኺደት የኦሮሞ ሕዝብ ብቻ ሳይኾን የቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብም ያለፈበት ኺደት ነውና፡፡ ስለኦሮሞ ሕዝብም ታሪክ ሲነገር በርካታ ክንዋኔዎችና ጊዜያቶች መገለጽ ይገባቸዋል፡፡

በጎንደር ዘመነ መንግሥት (፲፭፻፵፭-፲፯፻፷፯) ከመጀመሪያዎቹ ዓመታት እስከ መጨረሻዎቹ የኦሮሞ ሕዝብ ተወላጆች የፖለቲካ ተሳትፎ ከፍተኛ ነበር፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ በአንድ በኩል ከዐፄ ሠርጸ ድንግል (በጎንደር ዘመነ መንግሥት የመጀመሪያው ንጉሥ) ጦር ጋር ተዋግቷል (ሥርግው ገላው፣ ፳፻፪)፡፡ በሌላ በኩል፣ የዐፄ ሠርጸ ድንግልን ጦር በመደገፍና እስከ ኤርትራ በመዝመት የባሕረ ነጋሽ ይስሃቅን ጦር ወግቷል፤ በጎንደር በወገራና አካባቢው ንጉሡ ከፈላሻዎች ጋር ባደረጉት ጦርነት ከዐፄ ሠርጸ ድንግል ጎን ተሰልፈው ተዋግተዋል (ዓለሙ ኃይሌ፣ ፳፻፭)፡፡ ከዐፄ ሠርጸ ድንግል ሞት በኋላ በተለያዩ ጊዜያት በጎንደር የነገሡትን የተለያዩ ነገሥታት ደግፈዋል፤ ከተቃዋሚዎቻቸው ጎን ተሰልፎ ተዋግቷል፡፡ ዐፄ ሱስንዮስ ወደ ሥልጣን እንዲወጡ የኦሮሞ ሕዝብ ከፍተኛ ድጋፍ አድርጓል፡፡ በሌላ በኩል፣ ከዐፄ ሱስንዮስ ጦር ጋር ተዋግቷል (ዓለሙ ኃይሌ ፤ ፳፻፭)፡፡ ይኸው ንጉሥን የመደገፍና የመቃወም ተግባር በጎንድር ዘመነ መንግሥት ሙሉውን ዘመን የዘለቀ ነበር፡፡ ዐፄ ኢዩዋስ የእናታቸውን ዘመዶች ኦሮሞዎችን በብዛት ወደ ጎንደር ቤተመንሥት በማምጣት ሥልጣን በመሥጠታቸው በከተማው ውስጥ የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪው ቁጥር ከፍተኛ ኾኖ ነበር፡፡

ከጎንደር ዘመነ መንግሥት መዳከም በኋላም ዘመነ መሳፍንት እየተባለ በሚጠራው የኢትዮጵያ ታሪክ መቀመጫቸውን በዋናነት ደብረ ታቦር አድርገው የሰሜኑን የሀገራችን ክፍል ከ፹ ዓመት በላይ የመሩት የየጁ ኦሮሞዎች ነበሩ (Shiferaw Bekele, 1990)፡፡ እነሱም ሥልጣናቸውን ለማደላደል ከአካባቢው መሳፍንት ጋር የጋብቻ ዝምድና ከመመሥረታቸው በተጨማሪ የሚቃወሟቸውን ወግተው በማሸነፍ ሥልጣናቸውን አደላድለዋል፡፡ ይኽ ድርጊታቸውም በዘመኑ ጀግንነት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ የተሸነፉባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡

በሽንፈቱም መስዋዕትነት ከፍለውበታል፤ የጀግንነት ተግባር ፈጽመውበታል፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ የጀግንነት ታሪክ "በዐፄ ምኒልክ አዝማችነት፣ በራስ ጉበና ዳጬ ፊታውራሪነት በሕዝባችን ላይ በመዝመት ራሳችን በራሳችን እንዳናስተዳድር፣ የመሬታችን ባለቤትና የምርታችን ተጠቃሚ እንዳንኾን ተደርገናል" በማለት በመደጋገም የሚነገረው ታሪክ የኦሮሞን ሕዝብ የረጅም ዘመን ታሪክ አንዱ ገጽታ እንጂ የኹሉንም ዘመን አይገልጽም፡፡ የኦሮሞን ሕዝብ ታሪክ በ፲፱ኛው ክፍለ ዘመን የተፈጸመን "ጭቆና" ብቻ መሠረት በማድረግ መናገር ታሪኩን የተሟላ አያደርገውም፡፡ ከኹሉም በላይ በሕዝብ መዝሙር የሚገለጸው ታሪክ በጥንቃቄ መወሰን ያስፈልጋል፡፡ ታሪክ አዎንታዊና አሉታዊ ገጽታዎች አሉት፡፡ አሉታዊ ገጽታ ከሚባሉት አንዱ በሀገር ውስጥ የደረሰ ጭቆና ሊኾን ይችላል፡፡ ይኽ በጊዜያዊነት የሚታይና የሕዝቦች ዘለቄታዊ ግንኙነት ወደ ተሻለ ደረጃ የማያደርስ ነው፡፡ አዎንታዊ የሚባለው የታሪክ ገጽታ የተከታታይ ትውልዶች ብሔራዊ ማንነት የሚገነባበት፣ ዘላቂ የኾነ የታሪክ ክንዋኔ ነው፡፡ የሕዝብ መዝሙር ማንጸባረቅ የሚገባው እንዲኽ ዐይነቱን ታሪክ ነው፡፡

የኦሮምን ሕዝብ ረጅም ታሪክ የዐፄ ምኒልክን ጦር ለመከላከል ከተደረገው ጦርነት መጀመር ኹለተኛው ሕጸጽ ነው፡፡ ምክንያቱም ኦሮሞች ኢትዮጵያን ለማጥቃት የመጡትን የወጭ ጠላቶች ለመከላከል የከፈሉትን መሥዋዕትነት ግንዛቤ ያላስገባ ስለኾነ ነው፡፡ በተለያዩ ጊዜያት በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ከፍተው የነበሩትን የውጭ ወራሪዎች ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በመኾን የዐርበኝነት ተግባር የፈጸሙትንና መስዋዕትነት የከፈሉትን ኦሮሞዎች ታሪክ ወደ ጎን መተው ነው፡፡ ዐድዋ ላይ በ፲፰፻፹፰ ዓ. ም. ከጣሊያን ቅኝ ገዥ ጦር ጋር በተደረገው ጦርነት ዐፄ ምኒልክ ያስተዳድሩት በነበረው የኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ኦሮሞዎችም ጭምር ተሳትፈዋል፡፡ ዐፄ ምኒልክ፣ ወደ ዐድዋ ሲዘምቱ በመናገሻ ከተማቸው በዐዲስ አበባ አካባቢ የሚኖረው የኦሮሞ ሕዝብ የዘመቻው ተሳታፊ አልነበረም፣ አልዘመተም ብሎ መናገር አይቻልም፡፡ ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት ይኖሩ የነበሩት ብቻ ሳይኾኑ ለዐፄ ምኒልክ እንዲገብሩ የተደረጉት በወለጋ፣ በአርሲ፣ በባሌና በሐረር ከሚኖሩ ኦሮሞች በአካባቢው ገዥዎች ተመርተው በጦርነቱ ተሳትፈዋል፡፡

ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛትነት ለመያዝ ፍላጎት የነበረው የጣሊያን መንግሥት ጦር በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. ማይጨው ላይ በከፈተው ጦርነት ኹሉም ኢትዮጵያውያን፣ የኦሮሞ ሕዝብ ጭምር ተሳትፈዋል፡፡ የጣሊያን ጦር ድል አድርጎ ለ፭ ዓመታት ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛትነት ይዞ በቆየበት ጊዜ ብዙ ኢትዮጵያውያን ወደ ጫካ በመግባት የዐርበኝነት ተግባር ሲፈጽሙ የኦሮሞ ልጆችም ተሳተፈዋል፡፡ ይኽንን ታሪክ የጋራ ማድረግ ካልተቻለ የኦሮሞ ሕዝብ በኢትዮጵያ የነጻነት ታሪክ ተሳታፊ አይደለም ማለት ነው፡፡ ለኢትዮጵያ ነጻነት የተዋጉ የኦሮሞ ልጆችንም ኦሮሞዎች አይደሉም፤ ወይም ያገኙት ድል ለኦሮም ሕዝብ አልጠቀመም ማለት ነው፡፡ ስለኾነም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ ስለኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ የተገለጸው የፖለቲካ ዓላማን ለመደገፍ ሲባል የቀረበ ነው፡፡ ይኽም በመኾኑ ትክክለኛውን የኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ በትክክል አላሳየም፡፡ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሕዝብ መዝሙር እንዲኽ ዐይነቱ ታሪክ እንዲጎላ ቢደረግ የአንድነት ስሜትን ያጎለብታል፤ የኦሮሞ ሕዝብ በኢትዮጵያ ጉዳይ ተሳታፊና ወሳኝ የነበረበትን ታሪክ መንገር በተለያዩ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት በሚገኙ በትውልዶች መካከል መቀራረብንና አንድነትን ለማጎልበት ይረዳል፡፡

የኦሮሞን ሕዝብ ታሪክ ለማወቅ የምናነበው ታሪክ የተለየ ፍላጎትን ለማሳካት ተብሎ የተጻፈ መኾን የለበትም፡፡

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ ሕገ መንግሥት መዝሙሩ የኦሮሞን ሕዝብ የጀግንነትና የፍትሕ ታሪክ እንዲያንጸባርቅ ይደነግጋል፡፡ ኦሮሚያ የተመሠረተችው የሙቶ ዓመት የትግልና የመስዋዕትነት ታሪክ በማሳለፍ መኾኑን መዝሙሩ ይገልጻል፡፡ በብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት በክልሉ ስለሚኖሩ ብሔረሰቦች አልተገለጸም፡፡ መዝሙሩም በክልሉ ስለሚኖሩ ብሔረሰቦች መኖራቸውን አይገልጽም፡፡

**፫. ፬) የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መዝሙር**

የተሻሻለው የሶማሌ ክልል ሕገ መንግሥት በሥራ ላይ መዋሉን ለማሳወቅ በወጣው ዐዋጅ ቁጥር ፲፰/፲፱፻፺፬ አንቀጽ ፰ የክልሉ መዝሙር ተደንግጓል፡፡ ድንጋጌውም፣ "የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መዝሙር የሕገ መንግሥቱን ዓላማዎች፣ የሕዝቡን ታሪክ፣ ባህል፣ ቋንቋና የክልሉን ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን እምነት እንዲሁም፣ የክልሉ ሕዝብ ዕድገት ብሩኅ ተስፋ የሚያንፀባርቅ ሆኖ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡" የሚል ነው፡፡ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው ኹለተኛው የሶማሌ ሕዝብ መዝሙር የሚከተለው ነው፡፡

Heesta Calanka D.D.S.I[13]

| | |
|---|---|
| Haybadaan La Hayniyo | የነበረን ክራማን፣ |
| Calankii Hidahayaga | የኛ የሆነው ሰንደቅ ዓላማችን፣ |
| Hooyo Laga Angariyee | በናት ጡት የታነጸው ልጅ፣ |
| Haybta Naga Mideeyoow | [በናት ጡት ያደገው ልጅ]፣ |
| Hubaalkii Itoobiya | አንድ ያደረገን፣ |
| Xaqa Noo Horseedee | እውነተኛ ኢትዮጵያ፣ |
| Horyaal Nooga Dhigayoow | ፍትሕን ያስገኘች፣ |
| Hanaan Suuban Iyo Nabad | የኛ ብርሃን፣ |
| Calankii Hirgaliyee | መልካም አስተዳደርንና ሰላምን፣ |
| Heshiis Lagu Saleeyayoow | እውነት ያደረገው ሰንደቅ ዓላማችን፣ |

[13] Current Ethiopian Somali Regional State Anthem

| | |
|---|---|
| Horumar Iyo Cadaadaladi | ስምምነትን መሠረት ያደረገው ሰንደቅ ዓላማችን፣ |
| Kamaba Horeeynine | ልማትና ፍትሕ ካንተ በፊት ያልነበረው፣ |
| Calankaan Haadh Sanaynayoow | ጥላ ያደረግነው ሰንደቅ ዓላማችን፣ |
| Hoodaalihiiyow Hambalyo Kugu Salaanaye | ጥሩነትንና ደግነትን፣ |
| Astaan Hodana Noonogo | በደስታ [በ]ሰላም እንቀበልሃለን፣ |
| Waanu Kuu Han Waynoo | ሁንልን ብልጽግና፣ |
| Naftaan Kuu Huraynaa | በሰንደቅ ዓላማችን እንኰራለን፣ |
| Habeen Iyo Dharaarbaan | ሕይወታችን እንሰዋለን፣ |
| Cadow Kaa Hiraynaa | ቀንና ሌሊት ከጠላት እንጠብቅሻለን፣ |
| Hareertaada Joognaa | በዙሪያሽ ዘብ ቁመናል፡፡ |

መዝሙሩ የሚጀምረው "የነበረን ከራማን" በሚል ስንኝ ነው፡፡ በዚኽ ዐውድ ከራማ የሚለው የኢትዮጵያ በታሪክ ትልቅ ቦታ ነበራት ማለትን ነው፡፡ ይኽም የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር የነበረውን የቆየ የነፃነት ታሪክ ትስስር ይገልጻል፡፡ የኢትዮጵያ የነፃነት ምልክትና መለያ የኾነው ሰንደቅ ዓላማ የጋራ መኾኑንም መዝሙሩ ይገልጻል፡፡ በመዝሙሩ ውስጥ የኢትዮጵያ የነፃነት ምልክትና መለያ የኾነው ሰንደቅ ዓላማ በተለያየ አገልግሎቱ ዐምሥት ጊዜ ተጠርቷል፡፡ በመጀመሪያ ሰንደቅ ዓላማው የሶማሌና የቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ የነፃነት ምልክትና መለያ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ሰንደቅ ዓላማው የኢትዮጵያ የነፃነት ምልክትና መለያ ብቻ ሳይሆን በሀገር ውስጥ መልካም አስተዳደርንና ሰላምን ማስገኘቱን መዝሙሩ ይገልጻል፡፡ ይኽን ያስገኘው ሰንደቅ ዓላማ የተመሠረተው የሶማሌ ሕዝብ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ተስማምቶና ፈቅዶ ስለመሆኑ መዝሙሩ ይገልጻል፡፡ በስምምነት የተመሠረተው ሰንደቅ ዓላማም ቀድሞ ያልነበረን ልማት ለማምጣትና ፍትሕ ለማስፈን ማስቻሉና ጥላ ከለላችን ነው ብሎ ሕዝቡ እንደሚያምን መዝሙሩ ያስረዳል፡፡ ሰንደቅ ዓላማው የሕዝቡ የኩራት ምንጭ ኾኖ እንደሚያገለግል ተገልጿል፡፡ የአንድ እናት ልጆች የእናታቸውን ጡት ጠብተው እንደሚያድጉት ሁሉ ኢትዮጵያም የሶማሌን ሕዝብና ሌላውንም የኢትዮጵያ ሕዝብ አብልታና አጠጥታ በአጠቃላይ መግባ ያሳደገች መሆኑ በመዝሙሩ ተነግሯል፡፡ ኢትዮጵያ የመገበችንና ያሳደገችን በመሆኑም አንድ ነን የሚል መልእክት ያስተላልፋል፡፡ ኹሉንም ኢትዮጵያውን እኩል የምታስተናግደው እውነተኛ ኢትዮጵያ ፍትሕን በማስገኘቷ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሶማሌ ሕዝብም የሕይወት ብርሃን አገኝቷል፡፡ የሕይወት/የኑሮ ብርሃን ደስታ ተስፋ የሞላበት በደል ጭቆና የሌለበት ማለት ነው፡፡ ይኽም በመኾኑ፣ ኢትዮጵያን ዙሪያዋን ከብበው ሌሊትና ቀን ለመጠበቅና የሕይወት መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ መኾናቸው በመዝሙሩ ተገልጿል፡፡

የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕዝብ መዝሙር የክልሉን ሕዝብ ታሪክ እንዲያንጸባርቅ በሕገ መንግሥቱ ተደንግጓል፡፡ የሕዝብ መዘሙሩ የሶማሌን ሕዝብ ታሪክ የሚያንጸባርቅ እንዲኾን መደንገጉ ተገቢ ነው፡፡ የትውልድ ማንነት የሚመሠረተው የትናንትን ታሪክ መነሻ በማድረግ በመኾኑ በሕዝብ መዝሙር አማካይነት በትውልድ አእምሮ እንዲሰርጽ ማድረግ ማንነቱን የሚያውቅ ትውልድ ለመፍጠር ያስችላል፡፡ የአንድ ሕዝብ ታሪክ ሰፊ ከመኾኑም በላይ አዎንታዊና አሉታዊ ገጽታዎች ያሉት በመኾኑ ለቀጣዩ ትውልድ ጎልቶና ጠንክሮ መነገር ያለበትን መለየት አስፈላጊ ነው፡፡ ይኸም ማለት የሕዝቡ ታሪክ በአንድ በኩል፣ ሕዝቡ ያጋጠሙትን መጥፎ የታሪክ ገጽታዎች ይዘክራል፡፡ በሌላ በኩል፣ ሕዝቡ ያለፈባቸውን መልካም የታሪክ አጋጣሚዎችና ክንዋኔዎች ይዘግባል፡፡ የክልሉ ሕዝብ ከሌሎች ብሔሮችና ብሔረሰቦች ጋር ባደረጋቸው ግንኙነቶች ያጋጠሙት መልካምና መልካም ያልኾኑ ድርጊቶች የሶማሌ ሕዝብ ታሪክ አካል ናቸው፡፡ ከነዚኽ የታሪክ ገጽታዎች ለአኹኑና ለተተኪው ትውልድ በተደጋጋሚ መነገር ያለበት ለአንድነትና ለእድገት የሚጠቅመው ክፍል ነው፡፡ የውጪ ኀይሎችን በመከላከልና ነጻነትን በመጠበቅ የተደረገ ተጋድሎ ትውልድ የሚኰራበት የታሪክ ክፍል ነው፡፡ በብሔራዊ ክልሉ የሕዝብ መዝሙር ጎልቶ መነገር ካለባቸው አዎንታዊ የታሪክ ገጽታዎች አንዱ የውጭን ጠላት በመመከት የተደረገው ተጋድሎና የተከፈለው መሥዋዕት ነው፡፡

አንድ የሕዝብ መዝሙር ኹሉንም የታሪክ ገጽታዎች ማንጸባረቅ አይችልም፡፡ የሕዝብ መዝሙር የሕዝብን የጀግንነት ታሪክ በመዘከርና ጀግንነትን በመስበክ ሀገርን በሚረከበው ትውልድ አእምሮ ማስረጽ ግን ይገባዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ የክልሉ መዝሙር የሶማሌን ሕዝብ ታሪክ እንዲያንጸባርቅ ሲባል የትኛውን የታሪክ ገጽታ? መቼና የት የተከናወነውን? ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ የሶማሌ ክልል መዝሙር ማንጸባረቅ የሚገባው የታሪክ ገጽታ የትኛው መኾን እንደሚገባው አስቦ በጥንቃቄ መወሰን ደግሞ የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ ሥልጣን (?) ነው፡፡ የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት የክልሉ መዝሙር "የሕዝቡን ታሪክ ማንጸባረቅ ይገባዋል" በማለት የተደነገገውን በጥንቃቄ መተግበር፡፡

የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሕዝብ መዝሙር የሕዝቡን ባህልና ቋንቋ እንዲያንጸባርቅ በማለት የክልሉ ሕገ መንግሥት ይደነግጋል፡፡ እንደዚሁም፣ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት "የሕዝብ መዝሙሩ የክልሉን ባህል እንዲያንጸባርቅ" በማለት የክልሉ ሕገ መንግሥት ይደነግጋል፡፡ ይኸም ኾኖ በኹለቱም ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ሕገ መንግሥቶች የሕዝብ መዝሙሮቻቸው ባህላቸውን እንዲያንጸባርቁ የደነገጉት ተመሳሳይ ነው፡፡ የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሕዝብ መዝሙሩ ኹለት ጉዳዮችን ማለትም ባህልንና ቋንቋን እንዲያንጸባርቅ ሲደነግግ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሕዝብ መዝሙር ግን ባህልን ብቻ እንዲያንጸባርቅ ይደነግጋል፡፡ ባህልና ቋንቋ የአንድ ሳንቲም ኹለት ገጽታዎች ናቸውና፡፡ ባህል ተገላጭ፣ ቋንቋ ደግሞ ገላጭ ነው፡፡ በሌላ በኩል ባህል ሰፊና ብዙ ነገሮችን የሚያካትት የአንድ ሕዝብ ማንነት መገለጫ በመኾኑ ከቋንቋ ምንነት ይሰፋል፡፡ ቋንቋም የባህል አካል ነው፡፡ ይኸም ኾኖ የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መዝሙር የክልሉን ባህልና ቋንቋ እንዲያንጸባርቅ በማለት የደነገገው ለቋንቋ የተሰጠውን ትኩረት ይገልጻል፡፡

የሶማሌ ብሔራዊ ክልል መንግሥት መዝሙር የክልሉን ሕዝብ ታሪክ፣ ባህልና ቋንቋ እንዲያንጸባርቅ ሕገ መንግሥቱ ይደነግጋል፡፡ በሕገ መንግሥቱም በመዝሙሩም ከሱማሌ ብሔር ሌላ በክልሉ የሚኖሩ ብሔረሰቦች መኖራቸው አልተገጸም፡፡

## ፬) ማጠቃለያ

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትና የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መዝሙሮች የብሔራዊ ክልሎቹ ሕዝቦች ያገኙትን ድል የሚያሳዩ እንዲኾኑ በየሕገ መንግሥታቸው ደንግገዋል፡፡ ይኸም የኹለቱም ክልሎች ሕዝቦች በረጅም ዘመን የጀግንነት ታሪካቸው "በነፍጠኛው ሥርዓት" ላይ ያስመዘገቡት ድል ነው፡፡ ሌሎቹ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት በየሕዝብ መዝሙሮቻቸው እንዲንጸባረቅ ባይደነግጉም፣ የነፍጠኛውን ሥርዓት ድል ማድረጋቸውን በየሕገ መንግሥታቸው መግቢያ ላይ ገልጸዋል፡፡ በአንዳንዶቹ ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ ለምሳሌ በዐማራው ድል የተደረገው ኋላ ቀርና አፋኝ ሥርዓት መኾኑ ተገልጹዋል፡፡ በሕዝቦች ትግል ድል የኾነው የነፍጠኛው ሥርዓት፣ <u>በአንዳንዳቹ ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ ኋላ ቀርና አፋኝ ሥርዓት በመባል የተጠራው አንድን ሕዝብ በተለይም ዐማራውን</u> ወይም የዐማራውን የገዢ መደብ የሚወክል ተደርጎ ይቀርባል፡፡ ይኸም የዐማራው ብሔር ሌሎችን ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሲጨቁን የነበረ ተደርጎ እንዲታሰብ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ፣ በዐማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ <u>"በአብዛኛዎቹ የአገራችን ብሔር-ብሔረሰቦች</u> ላይ ሲፈጸም በቆየው አስከፊ ብሔራዊ ጭቆና ምክንያት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የጉዳቱ ሰለባዎች ሆነን መቆየታችን በማያዳግም ሁኔታ መታረም እንዳለበት በማመን፤" (አጽንኦት የተጨመረ) በማለት የተገለጸው በ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. ከተካኼደው የፖለቲካ ለውጥ በፊት ብሔራዊ ጭቆና ያልደረሰባቸው ብሔር- ብሔረሰቦች ነበሩ ማለትን ያስረዳል፡፡ የተሰመረበት ሐረግ የሚገልጸው በሀገራችን ብዙዎቹ ብሔር- ብሔረሰቦች ላይ አስከፊ ብሔራዊ ጭቆና ሲፈጸም መቆየቱን፣ በጥቂቶቹ ላይ ደግሞ አስከፊ የሚባል ብሔራዊ ጭቆና አለመፈጸሙን ይገልጻል፡፡ ጭቆና ያልተፈጸመባቸው ብሔር- ብሔረሰቦች የትኞቹ እንደኾኑ አልተገለጸም፡፡ ይኽ ዓይነቱ ሐሣብ የተዛባ የፖለቲካ ግንዛቤን ይገልጻል፡፡ ብሔራዊ ጭቆና የሚለው ሐሳብም እውነተኛውን የኢትዮጵያ ታሪክ አይገልጽም፡፡

የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት መሥራች ብሔራዊ ክልሎች በሕዝብ መዝሙሮቻቸው አንድነትን የማያንጸባርቁ መኾናቸው ስለ አንድነት እንዲታሰብ አያደርጉም፡፡ ትኩረታቸውና ፍላጎታቸው በራሳቸው ላይ ብቻ መኾኑ የሕዝብ መዝሙሮቻቸው የሚጠበቅባቸውን ተግባር እንዲያሳኩ አልተደረገም፡፡ የሕዝብ መዝሙሮቹ ልዩነትን አይነግሩም ከተባለም ከሌሎች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ሕዝቦች ጋር አብሮ ስለመኖር አለመስበካቸው ስለ አንድነት እንዲታሰብ አያደርጉም፡፡ ይህም አንድነትን ያላል ማለት ነው፡፡

የየብሔራዊ ክልሎቹ መዝሙሮች በየብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታቱ የሚኖሩትን ሕዝቦች የወደፊት የጋራ ዕድል የሚያንጸባርቁ እንዲኾኑ በየሕገ መንግሥታቸው ኹሉም አልደነገጉም፡፡ የሕዝቦችን የጋራ ዕድል በተመለከተ የተደነገገው ተመሳሳይነት ቢታይበትም

በጥንቃቄ ሲመረመር ግን ልዩነት ይስተዋልበታል፡፡ ለምሳሌ፣ የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሕዝብ መዝሙሮች የየክልሉ ሕዝብ ለተሻለ ኑሮ ያላቸውን ምኞት የሚያንጸባርቁ ኾነው ዝርዝራቸው በሕግ እንደሚወሰን ይደነግጋሉ፡፡ በእነዚኽ የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት የሕዝብ መዝሙሮች እንዲንጸባረቅ የተደነገገው ይዘት የየሕዝቦቹ የወደፊት ሕይወት የተሻለ እንዲኾን ይመኛል፡፡ ምኞት ደግሞ የተሻለ ኑሮ ለማግኘት መከጀልን፣ መፈለግንና መጓጓትን ይገልጻል፡፡ የወደፊቱ የሕዝቦች ሕይወት ብሩኅ ሊኾን እንደሚችል የታመነው፣ ዛሬ ያለው ነባራዊ ኹኔታ የነገውን የሕዝቦች ሕይወት ብሩኅነት ለመተንበይ በማስቻሉ ነው፡፡

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትና በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕዝብ መዝሙር አንዲንጸባረቁ የተደነገጉት ይዘቶች ተመሳሳይ ከመኾናቸውም በላይ በሌሎች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ሕዝብ መዝሙሮች እንዲንጸባረቁ ከተባሉት ይዘቶች ይበልጣሉ፡፡ በሌሎቹ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ሕዝብ መዝሙሮች እንዲንጸባረቁ የተባሉት ይዘቶች ከሦስት እስከ አራት ይደርሳሉ፡፡ የሶማሌና የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ሕዝብ መዝሙሮች እንዲያንጸባርቋቸው የተደነገጉት ይዘቶች ግን ስድስት ናቸው፡፡ ኹሉንም ይዘቶች በብሔራዊ ክልሎቹ ሕዝብ መዝሙሮች ለማንጸባረቅ አስቸጋሪ ነው፡፡ መዝሙሮቹ ረጅም እንዲኾኑ ተፅዕኖ ያደርጋል፡፡ ይኽ ደግሞ የሕዝብ መዝሙሩ ሲዘመር ረጅም ጊዜ በመውሰድ በዘማሪው ኅብረተሰብ ላይ መሰልቸትን ሊያመጣ ይችላል፡፡ በቃል ለማስታወስም ያስቸግራል፡፡

በአንድ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሕዝብ መዝሙር እንዲንጸባረቁ የተደነገጉት ይዘቶች በሌላው ክልል የሕዝብ መዝሙር እንዲንጸባረቁ ከተባሉት ይዘቶች ጋር አንድ ዐይነት ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕዝብ መዝሙር እንዲንጸባረቁ የተደነገጉት ይዘቶች፣ በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መዝሙር እንዲንጸባረቁ ከተደነገጉት ይዘቶች ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡ በኹለቱ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት መዝሙሮች እንዲንጸባረቁ በተባሉት ይዘቶች መካከል የቃል ልዩነት አንኳ አይታይም፡፡ እንደዚሁም የቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ብሔራዊ ክላለዊ መንግሥት መዝሙርና የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መዝሙር እንዲንጸባረቁ የተደነገጉት ይዘቶች አንድ ዐይነት ናቸው፡፡ በዐማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትና በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥቶች በመዝሙሮቻቸው እንዲንጸባረቁ በተደነገጉት ይዘቶች መካከል ልዩነት የለም፡፡

ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትና ከሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በስተቀር የሌሎቹ (የሰባቱ) ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ሕገ መንግሥቶች የሕዝብ መዝሙሮች የየክልላቸውን ሕገ መንግሥት ዓላማዎች እንዲያንጸባርቁ ይደነግጋሉ፡፡ የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታቱ ሕገ መንግሥቶች ዓላማዎች በየሕገ መንግሥቱ መግቢያዎች ላይ በተለያየ መንገድ ተገልጸዋል፡፡ በአንዳንዶቹ ሕገ መንግሥቶች ዓላማዎቹ በግልጽ ተመልክተዋል፡፡ ለምሳሌ፣ በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ የብሔራዊ ክልላዊ ሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች በግልጽ ተደንግገዋል፡፡ ዓላማዎቹም "እኛ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፡- በጋራ በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ ተመስርተን ባቋቋምነው ክልላችን የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን፤ [የ]ኢኮኖሚና [የ]ማኅበራዊ ዕድገታችን እንዲፋጠን የራሳችንን ዕድል በራስ የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን፣ ቋንቋችንን፣ ባህላችንና አንድነታችንን ይበልጥ

ለማጠናከር፣ ማንነታችን ተከብሮ በትግላችንና በከፈልነው መሥዋዕትነት የተገኘውን ዲሞክራሲና ሰላም ለማረጋገጥ፤" የሚሉት ናቸው፡፡ የአንዳንዶቹ ብሔራዊ ክልላዊ ሕገ መንግሥቶች መግቢያዎች ግን የሕገ መንግሥታቸውን ዓላማዎች ለመገንዘብ በሚያስችል መንገድ አልገለጹም፡፡ ይሁን እንጂ በዘጠኙም ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ሕገ መንግሥቶች የሚነበቡት ድንጋጌዎች መሠረታዊ ልዩነት የላቸውም፡፡

**መርጃ ጽሑፎች**


ሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት፣ "የሐረሪ ሕዝብ ክልል የተሻሻለው ሕገ መንግሥት ማጽደቂያ አዋጅ"፣ (*የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት ሐረር ነጋሪት ጋዜጣ፡* ፱ ዓመት፣ ቁጥር አንድ፣ አዋጅ ቁጥር ፵፮/፲፱፻፺፯ መግቢያ ገጽ ፪፡፡

ሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት፡፡ "የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት የተሻሻለው ሕገ መንግሥት"፡፡ *የሐረር ነጋሪ ጋዜጣ፡፡* ፱ኛ ዓመት፣ ቁጥር አንድ፡፡

ሶማሌ ክልል ምክር ቤት፡፡ *የተሻሻለው የሱማሌ ክልል ሕገ መንግሥት በሥራ ላይ ማዋሉን ለማሳወቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፫/፲፱፻፺፬*፡፡

መምርሒ ስርዓተ ትምህርቲ ፓነል ኤስቴቲክስ ጥንካረ አካልን (መዳለዊ) ፡፡ 1995፡፡ *ትምህርቲ ኤስቴቲክስን ጥንካረ አካልን መምርሒ ንመምህር ፲ᵉ ክፍሊ፡፡* መቐለ (ማተሚያ ቤቱ አልተገለጸም)፡፡

ብሓልዮት ቤት ምኽሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቲ ትግራይ፡፡ *ነጋሪት ጋዜጣ ትግራይ፡፡* ትግራይ ክልል ሰንደቅ አላማ ለመወሰን የወጣ ዐዋጅ ቁጥር 2/1988፡፡

ብሓልዮት ቤት ምኽሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቲ ትግራይ፡፡ *ነጋሪት ጋዜጣ ትግራይ፡፡* 10ኛ ዓመት፣ ቁጥር 2፣ ሕዳር 6 1994፣ *ተሻሽሎ የወጣውን የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር 45/1994*፡፡

ብሔራዊ መዝሙር ዝግጅት ኰሚቴ፡፡ "ለኢትዮጵያ ሽግግር መንግሥት ተወካዮች ምክር ቤት ያቀረበው ማስታወሻ"፡፡ ሰኔ ፪ ቀን ፲፱፻፹፬፡፡

ብሔራዊ የዐማራ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ፡፡ *የብሔራዊ ዐማራ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) ፕሮግራም፡* ዐዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ ፲፱፻፹፮፡፡

ቤኒሻንጉል- ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት፡፡ "የተሻሻለው ፲፱፻፺፫ ዓመተ ምሕረት የቤኒሻንጉል- ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፴፩/፲፱፻፺፫፡፡"

አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት፡፡ "አዋጅ ቁጥር ፶፱/፲፱፻፺፬ የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግሥት ማፅደቂያ አዋጅ፡፡" *የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ዝክረ ሕገ*፡፡

አማራ ብሔራዊ ክል መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ 1985 - 1992፤፡፡

አፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት፡፡ "የተሻሻለው የ፲፱፻፺፬ ዓ. ም. የአፋር ክልል ሕገ መንግሥት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፲፬/፲፱፻፺፬"፤ *የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ፡* ፫ኛ ዓመት ፣ ቁጥር ፩፣ ሰኔ ፳፰/፲፱፻፺፬፡፡

ኢትጵያ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉባዔ፣ "የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር"፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ ዐምስተኛ ዓመት ፣ ቁጥር ፩፣ ሐምሌ ፲፫ ቀን ፲፱፻፹፫፡፡

ኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤት ፳ኛ መደበኛ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፣ ግንቦት ፫ ቀን ፲፱፻፹፫፡፡

ኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤት ፴፫ኛ መደበኛ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፣ ጥር ፳፰ እና ፴ ፲፱፻፹፬፡፡

ኢትዮጵ የሽግግር መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር ፯/፲፱፻፹፬ "ብሔራዊ ክልላዊ የሽግግር መስተዳድሮች ለማቋቋም የወጣ አዋጅ፡፡"

ኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ፣ ዐዋጅ ቁጥር ፯/፲፱፻፹፬ ብሔራዊ ክልላዊ የሽግግር መስተዳድሮችን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ፤ የኢትዮጵያ የሽሽግር መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ፡

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፡፡ "የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ለማጠናከርና ሥልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር የወጣ ዐዋጅ ቁጥር ፪፻፶፩/፲፱፻፺፫፡፡" ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ፡፡

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፡፡ "የፌዴራሉ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ዐዋጅ ቁጥር ፪፻፶/፲፱፻፺፫፡፡" ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ፡፡

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፡፡ "የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ዐዋጅ ቁጥር ፩/፲፱፻፹፯፡፡" ፌዴራል ጋሪት ጋዜጣ ፡፡

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፡፡ "የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር በአዋጅ ቁጥር ፮፻፶፫/፪ሺ፪"፡፡ ፌዴራል ጋሪት ጋዜጣ፡፡

ኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት፡፡ "አዋጅ ቁጥር ፵፮/፲፱፻፺፬ የተሻሻለው የ፲፱፻፺፬ ዓ. ም. የኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግሥት ማጽደቂያ አዋጅ"፡፡ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መገለተ ኦሮሚያ፡፡

ኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት፡፡ "የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥትን አርማና መዝሙር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፹፰" [፬/፲፱፻፹፰]፡፡ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መገለተ ኦሮሚያ፡፡

ደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት፡፡ "የተሻሻለው የ፲፱፻፺፬ ዓመተ ምሕረት የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሕገ መንግሥት"፡፡ (በምን ላይ እንደታተመ አልተገለጸም፡፡)

ጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት፡፡ "የተሻሻለው ፲፱፻፺፭ ዓ. ም. የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፳፯/፲፱፻፺፭፡፡"

ይድነቃቸው ከበደና ኢሳያስ አየለ፡፡ "የሐረሪ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓትና ባህላዊ የቤተ ሰብ ሕግ"፤ የብህል ሕጎችና ተቋማት በኢትዮጵያ፣ቅጽ ፣፡፡ አዲስ አበባ፤ የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት ፣2007፣ ገጽ 122-143፡፡

Aregawi Berhe. 2008. *A Political History of the Tigray People's Liberation Front (1975-1991)፡ Revolt, Ideology and Mobilisation in Ethiopia.* Amsterdam: VRIJE UNIVERSITEIT.Central Statistical Agency. 2007.

Shiferaw Bekele. "The State in Zamana Masafent (1786-1855): An Essay in Reinterpretation"; *KASA and KASA፡ Papers on the Lives, Times and Images of Tewdros II and Yohannes IV (1855-1889.* (Edited by Taddese Beyene, Richard Pankhurst and Shiferaw Bekele) Addis Ababa University: Institute of Ethiopiaian, 1990, PP.25-68.